የጋዴኝነትን የፍቅር ገመድ
የበጠሰች ቅፅበት
ገጽ 10

የኅዳር በሽታ
እንዳይስምድብን!
ገጽ 11

ለአምራችና ሸማች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት
የተገነባው የግብይት ማዕከል
ገጽ 14

አዲስ ዘመን
83ኛ ዓመት ቁጥር 061 ኅዳር 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# «ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር በአካባቢ ጥበቃና ልማት ዙሪያ በትብብር ትሠራለች»

\- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር በአካባቢ ጥበቃና ልማት ሥራዎች ዙሪያ በትብብር እንደምትሠራ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስታወቁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በመጀመሪያው የሳዑዲ - አፍሪካ ጉባኤ ላይ ትናንት ንግግር አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሳዑዲ - አፍሪካ ጉባኤ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ (ሌጋሲ) ተነሳሽነት ከመካከለኛው ምሥራቅ የአረንጓዴ ልማት ኢኒሼቲቭ ጋር በመጣመር በትውልዱ ላይ ሰፊና አወንታዊ ውጤት ማምጣት ይቻላል ብለዋል።

በአረንጓዴ ልማት ላይ ያለውን ትብብር ማፋጠን፣ የአረንጓዴ ልማት ውጥኖቻችንን በአንድነት በማሳደግ ልንሠራ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እ.ኤ.አ. ከ2019 ጀምሮ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ትኩረት ሰጥታ ከፍተኛ ተግባራዊ ርምጃዎችን መውሰዷን አስታውሰዋል።

በዓመት ከ25 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን በሚያሳትፈው ግዙፍ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር 32 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን መተከላቸውን አስታውቀዋል።

የአረንጓዴው ዐሻራ መርሐ ግብር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የተተከለውን ጨምሮ እ.ኤ.አ. በ2026 መገባደጃ ላይ 50 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል አጠቃላይ ዕቅዳችንን እናሳካለን ብለዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሩ ውጤት በዓመት

«ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## የመቐለ የውሃ ፕሮጀክትን እንደገና ለማስጀመር የአንድ ሚሊዮን ዶላር ዕቃዎች ግዢ ተፈፀመ

ሔርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- በጦርነት ምክንያት ተቋርጦ የቆየውን የመቐለ ከተማን የውሃ ፕሮጀክት እንደገና ለማስጀመር የአንድ ሚሊዮን ዶላር ዕቃዎች ግዢ መፈፀሙን የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሳኒቴሽን መሠረተ ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ኑረዲን መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በክልሉ በተለይ በመቐለ እና ዓዲግራት አካባቢዎች በጦርነቱ ምክንያት ተቋርጠው የቆዩ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አሉ፡፡ ፕሮጀክቶቹን ለማስጀመር

የመቐለ የውሃ ፕሮጀክትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ: በረሁን ታደሰ

ሚጀር ጀኔራል ተሾመ ገመቹ

## የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያን ወደ ገናና የዕድገት ደረጃ የሚያደርስ አዲስ ኃይል ነው

ገጽ 4

## ኢፕድ እና ዘ ኮሪያ ታይምስ በተለያዩ ጉዳዮች በጋራ ለመሥራት ስምምነት አደረጉ

ሄለን ወንድምነው



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና የደቡብ ኮሪያው ዘ ኮሪያ ታይምስ የሚዲያ ድርጅት በተለያዩ ጉዳዮች በጋራ ለመሥራት ስምምነት አደረጉ።


የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ እና ዘ ኮሪያ ታይምስ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሚስተር ቾ ጃ ሀዮን አብረው ለመሥራት ትናንት ተፈራርመዋል።

በወቅቱ ኢፕድ የ82 ዓመት ታሪክ ያለው አንጋፋ ተቋም መሆኑን የተናገሩት አቶ ጌትነት ታደሰ፤ በስድስት ጋዜጦችና በኦንላይን ሚዲያው በዓለም አቀፍና ሀገር

ኢፕድ እና ዘ ኮሪያ ታይምስ ... ወደ ገጽ 4







አቶ አሸናፊ ክንፉ

## ክልሉ ከ11 ሺህ 400 ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት እየሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው የምርት ዘመን 11 ሺህ 412 ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር ለመሸፈን አቅዶ እየሠራ እንደሚገኝ የደቡብ ምዕራብ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። ከዚህም ከ450 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል።

በደቡብ ምዕራብ ክልል የግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ እና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ክንፉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ በተያዘው ዓመት 11 ሺህ 412 ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት በማቀድ በስድስት ዞኖች የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተሠርተው ወደ ተግባር ገብቷል።

መስኖ ሊያለሙ የሚችሉ የወንዞች ልየታም በዞኖች ላይ መካሄዱን ጠቅሰው፤ በተጨማሪም 800 አነስተኛ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች (ፓምፖች) ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል ብለዋል።

እነዚህ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ለማልማት የታሰበውን ስንዴ ምርት እንዲሳካ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ አሁን ላይ አርሶ አደሩ ዝግጅት እና የማሳ ልየታው በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው። እስካሁንም ከተካሄደ የማሳ ልየታ ውስጥ አንድ ሺህ 205 ሄክታር መሬት መታረስ ተችሏል።

በክልሉ በ2014 ዓ.ም 400 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ መልማት መቻሉን አውስተው፤ የሚታረሰውን መሬት ሽፋን በ2015 ዓ.ም ወደ ሦስት ሺህ 467 ሄክታር ማሳደግ መቻሉን አንስተዋል።

በተያዘው የምርት ዘመንም ባለፉት ዓመታት ከለማው በሦስት እጥፍ በማሳደግ ለማልማት መታቀዱን በመግለጽ፤ ክልሉ ካለው የማልማት አቅም አንጻር ገና ያልተነካ ነው ብለዋል።

ክልሉ የበጋ የመስኖ ስንዴ በተጨማሪ የተለያዩ አትክልቶችና የስራስር ሰብሎች በበልግ ያለማል ያሉት አቶ አሸናፊ፤ በዚህም በአንደኛ ዙር የመስኖ ልማት ከ50 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት እንደሚለማ ተናግረዋል።

ክልሉ ያለው የመስኖ መሠረተ ልማት ዝቅተኛ ነው ያሉት አቶ አሸናፊ፤ ክልሉ ከ305 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በመስኖ የመልማት አቅም ቢኖረውም እስካሁን ግን ዜሮ ነጥብ ሁለት በመቶ የሚሆን የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታው ነው ያለው ሲሉ ገልጸዋል።

ይህም አንድ ሺህ 900 ሄክታር መሬት ብቻ የሚያለማ መሆኑን አብራርተዋል።

መንግሥት ለክልሉ ሰፊ የመስኖ ልማት ዕድገት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ አሸናፊ፤ ያለው የመስኖ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ችግር ለመቅረፍም አንድ የመስኖ አውታር ግንባታ ለማካሄድ ጥናቱ አልቆ ወደ ጨረታ ገብቷል ብለዋል።

ይህም የመስኖ አውታር ወደ ሥራ ሲገባ 15 ሺህ ሄክታር መሬት ማልማት የሚችል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

# ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

## ሰብሳቢ ዕጩ ከኅዳር 3 ጀምሮ የዕጩዎች ጥቆማ እንዲቀርብ ጥሪ ቀረበ

**ዘላለም ግዛው**


ቀሲስ ታጋይ ታደለ

አዲስ አበባ፡- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዕጩ መልማይ ኮሚቴ ከሰኞ ኅዳር 03 እስከ ኅዳር 13 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የዕጩዎች ጥቆማ ማድረግ እንደሚቻል ጥሪ አቀረበ።

ኮሚቴው የተጠቋሚዎችን መስፈርት፣ የጊዜ ገደብ እና የጥቆማ አቀራረብ መንገዶችን እንዲሁም ሥራውን በይፋ መጀመሩን አስመልክቶ ትናንት በሰጠው መግለጫ ይፋ አድርጓል።

መልማይ ኮሚቴው ግልጽ እና አወዳዳሪ በሆነ አካሄድ ዕጩዎችን ለማቅረብ ይቻል ዘንድ ይፋ የዕጩዎች ጥቆማ ጥሪ ለመላው ሕዝብ፣ ለፖለቲካ ድርጅቶች እና ለሲቪል ማኅበረሰብ ማቅረቡን ነው የጠቆመው።

ጠቋሚዎች ጥቆማውን ከሰኞ ኅዳር 03 ቀን 2 ሰዓት 30 ደቂቃ ጀምሮ እስከ ኅዳር 13 ረቡዕ ከቀኑ 11 ሰዓት 30 ደቂቃ 2016 ዓ.ም ድረስ ጥቆማቸውን ለመልማይ ኮሚቴው ማቅረብ እንደሚችሉ የኮሚቴው ሰብሳቢ ቀሲስ ታጋይ ታደለ አብራርተዋል። ከጊዜ ገደቡ ውጪ የሚቀርቡ ጥቆማዎች ተቀባይነት እንደሌላቸውም አመልክተዋል።

ለጥቆማ አቅራቢዎች የጥቆማ ማቅረቢያ መንገድ፤ ኢሜይል erc@hopr.gov.et፣ በዋትስ አፕ እና በተንቀሳቃሽ ስልክ፡- +251987141100፣ በቴሌግራም +251987141100፣ ፖስታ፡- ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ መልማይ ኮሚቴ የመልዕክት ሳጥን ቁጥር 80001 አዲስ አበባ አማራጭ መንገዶች ዕጩዎችን መጠቆም የሚቻል መሆኑን ጠቅሰዋል።

በአካል ማቅረብ ለሚፈልጉ ጥቆማ አቅራቢዎች ደግሞ አራት ኪሎ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የእንግዳ መቀበያ ቢሮ በተዘጋጀው ዝግ ሳጥን ውስጥ የጥቆማ ወረቀታቸውን ማስቀመጥ እንደሚችሉ ተጠቁሟል። ለበለጠ መረጃ በቀጥታ የስልክ መስመር +251111134974/ +251987141100 መጠቀም እንደሚቻልም ነው የተገለጸው።

ተጠቋሚዎች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶችን አስመልክቶም ትውልደ ኢትዮጵያዊ (ት) እና ኢትዮጵያዊ (ት) ዜጋ፣ ከማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ (ች)፣ መልካም ሥነምግባርና ስብዕና የተላበሰ (ች) ማለትም በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙኃኑ በሚስማማባቸው የግብረ ገብ እሴቶች፣ በሕጎችና በሙያ ሥነምግባሮች ላይ የተመሠረቱ መርሆዎችን የሚጥሱ ተግባራትን ፈጽመው ያልተገኙ፣ ተአማኒና ፍቃደኛ መሆን አለባቸው ተብሏል።

በተጨማሪም የሚሰጠውን (ጣትን) ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችል ከፍተኛ ብቃት ያለው (ላት)፣ ከምርጫ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ባላቸው እና ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ሙያዎች ሙያዊ ብቃት ያለው(ላት) እና ከሌሎች ጋር የመሥራት ክህሎት፣ የማስተባበርና ምቹ ሁኔታ የመፍጠር የተረጋገጠ ችሎታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል ብሏል።

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አዋጅ ቁጥር 133/2011 አንቀጽ 5/1/ ዕጩ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት መልማይ ኮሚቴ መቋቋም እንዳለበት ይደነግጋል።

በዚህ መሠረትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጥቅምት 23 ቀን 2016 ዓ.ም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ዕጩ መልማይ ኮሚቴ መሰየማቸው ይታወሳል።

# በሦስት ወራት

## 77 ሺህ 200 ዩኒት ደም መሰብሰብ ተችሏል

**አመለወርቅ ከበደ**


አቶ ሀብታሙ ታዬ

አዲስ አባባ፡- በ2016 በጀት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት 77 ሺህ 200 ዩኒት ደም መሰብሰቡን የኢትዮጵያ ደምና ህብረህዋስ ባንክ አገልግሎት ገለጸ።

የኢትዮጵያ ደምና ህብረህዋስ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በሦስት ወራት 77 ሺህ 200 ዩኒት ደም ተሰብስቧል። በሩብ ዓመቱ ለመሰብሰብ ታቅዶ የነበረው 90 ሺህ ዩኒት ደም ሲሆን፤ የተሰበሰበው የዕቅዱ 85 በመቶ ነው ።

ባለፉት ሦስት ወራት ከክረምት ወቅት ጋር ተያይዞ ደም ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ነበር ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ትምህርት ቤቶች ዝግ በመሆናቸውና ከአየር ንብረቱ አስቸጋሪነት ጋር ተያይዞ በቂ ደም ለጋሽ ለማግኘት ፈታኝ እንደነበር አስታውሰዋል።

ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ሐምሌና ነሐሴ ወር ላይ በመንገድ ድንኳን በመትከል የደም ልገሳ እንዲደረግ ጥረት ተደርጓል፤ የቅስቀሳ ሥራም በስፋት ለመሥራት ተሞክሯል ብለዋል።

መስከረም ወር ላይ የመስቀል፣ ኢሬቻ፣ መውሊድና ሌሎች በዓላትን ጨምሮ በርካታ የአደባባይ በዓላት መከበራቸውን ተከትሎ በተደራጀ ሁኔታ ደም ለመሰብሰብ ፈታኝ እንደነበር አውስተዋል።

የደም እጥረት ችግሩን ለመቅረፍ በጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ አካላትም ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በመስከረምና ጥቅምት ወራት የደም እጥረት አጋጥሞ የነበረ ቢሆንም፤ አሁን ላይ ትምህርት ቤቶች መከፈታቸውን ተከትሎ የማሰባሰብ ሂደቱ ጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከ400 መምህራንና የደም ልገሳውን ከሚያስተባብሩ መምህራን ጋር ፎረም በማዘጋጀት በቅንጅት እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በርካታ ሰዎች ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች እየተያዙ ከመሆኑና የካንሰር ሕክምና ተቋማት እየተስፋፉ እንደመሆኑ ያለው የደም ክምችት በቂ የሚባል አለመሆኑን አመልክተዋል።

የተሰበሰበው ደም አጭር ቀን የሚቆይ እንደመሆኑ ማኅበረሰቡ በየሦስት ወር በቋሚነት ደም የመለገስ ልምድ እንዲያዳብር ከመገናኛ ብዙኃን ጋር በመሆን የቅስቀሳ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ ከመንግሥትና ከግል ተቋማትም ደም እንዲለግሱ የሚሠራ ቢሆንም፤ ከተቋማት የሚሰበሰበው የደም መጠን ዝቅተኛ ነው።

በኅዳር ወር የተለያዩ ሃይማኖቶች አጽዋማት የሚገቡበት ወቅት መሆኑን ተከትሎ የደም እጥረት እንዳያጋጥም እየተሠሩ ያሉ ተግባራትን አጠናክሮ ለመቀጠል አቅጣጫ እንደተቀመጠ ገልጸዋል።

# በኦሮሚያ ክልል በመጀመሪያው ሩብ ዓመት

## - ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የዜግነት አገልግሎት ተሰጥቷል

## - 26 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የዜግነት አገልግሎት መሰጠቱን የክልሉ ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ። 26 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰቡና ከሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ምገባ መካሄዱም ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ የክልሉን የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈጻጸምን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ በሩብ ዓመቱ በጎ ፈቃድን መሠረት ባደረገው የዜግነት አገልግሎት ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ መስጠት ተችሏል።

በበጀት ዓመቱ በ102 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር የሚገመት የዜግነት አገልግሎት ለመስጠት መታቀዱን የጠቀሱት አቶ ኃይሉ፤ በቀጣይ ጊዜያት ዕቅዱን ማሳካት የሚያስችል ሥራ ይከናወናል ብለዋል።

በትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማት ግንባታ በሩብ ዓመቱ ሁለት ሺህ 444 ቡኡረ ቦሩ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው መጠናቀቃቸውን ጠቁመው፤ አራት ሺህ 052 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የመምህራን መኖሪያ ቤቶች መገንባታቸውን አስታውቀዋል።

በቡሳ ጎኖፋ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃግብር ከሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ተማሪዎች የምገባ



አቶ ኃይሉ አዱኛ

አገልግሎት መሰጠቱን ተናግረዋል።

በክልሉ የዜግነት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዜጎች ከ103 ሚሊዮን በላይ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከ124 ሺህ በላይ ኩንታል የምግብ እህል መቅረቡን አስረድተዋል።

በሩብ ዓመቱ ከመደበኛ፣ ከማዘጋጃና ከውስጥ ገቢዎች 26 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን አመልክተው፤ ገቢው ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የስምንት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ብልጫ እንዳለው አስታውቀዋል።

በግብርና ሥራ በ2015/16 የምርት ዘመን ዘጠኝ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በተለያዩ ሰብሎች በዘር ተሸፍኗል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ከ265 ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ አስረድተዋል።

በሩዝ ኢኒሼቲቭ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን በመግለጽ፤ 44 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ አመልክተዋል።

በክልሉ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን አቅዶ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከበጋ መስኖ ስንዴው 105 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 22 ሞዴል የማኅበረሰብ መድኃኒት ቤቶች ለመገንባት ታቅዶ ወደ ሥራ መገባቱን ያስረዱት የቢሮ ኃላፊው፤ እስካሁን ድረስ 23 የማኅበረሰብ መድኃኒት ቤቶች መገንባታቸውን ጠቁመዋል።

በክልሉ የተከሰተውን የኮሌራ በሽታ ስርጭት ለመቆጣጠር ለሁለት ሚሊዮን ዜጎች ሕክምና በመስጠት መቆጣጠር መቻሉን ገልጸው፤ የወባን ስርጭት ለመግታት የኬሚካል ርጭትና ሰባት ሚሊዮን አጎበር መከፋፈሉን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በክልሉ ዘላቂ ሠላምና ደህንነት እንዲሰፍን ፅኑ አቋም እንዳለው አሳውቀው፤ ማንኛውም ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት በድርድርና በንግግር ብቻ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የክልሉ መንግሥት በሠላም ጉዳይ ላይ ቁርጠኛ እንደሆነው ሁሉ በሌላ ወገን የሚገኙ አካላት ተመሳሳይ አቋም መያዝ አለባቸው ብለዋል።

# መታረም የሚያስፈልገው ለአእምሮ ህሙማን ያለው የተዛባ ዕይታ

**ተስፋ ፈሩ**

የኢትዮጵያ አእምሮ ሕክምና ማኅበር ይፋ ያደረገው መረጃ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 27 በመቶ ያህሉ የአእምሮ ጤና ችግር እንዳለበት ያመለክታል። ከችግሩ ስፋት አንጻር ለአእምሮ ጤና ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠው የአእምሮ ሐኪሞች ይናገራሉ። በሀገራችን የአእምሮ ህመም ችግር ያለባቸውን ሰዎች ማግለልና ለህመሙ በተጋለጡ ዜጎች የማፈርና የመደበቅ ሁኔታ በስፋት እንደሚስተዋል ይገለጻል።

ለመሆኑ በሀገራችን ስለ አእምሮ ህመም ያለው ግንዛቤ ምን ይመስላል? ለአእምሮ ህመም የተጋለጡ ሰዎች ላይ የሚፈጸመው ማግለል እንዴት ይገለጻል? ራስን ለማጥፋት ዋነኛ ገፊ ምክንያት ነው ተብሎ በሚታመነው የአእምሮ ህመም ለተጠቁ ሰዎችስ ምን ዓይነት እንክብካቤ ያስፈልጋል? መደረግ ያለበት ድጋፍስ ምንድነው በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ የዘርፉ ምሁራን አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

ዮናስ ላቀው (ዶ/ር) የአእምሮ ሕክምና ስፔሻሊስት ናቸው። «የአማኑኤል ሆስፒታል ታሪኮች» በሚል ርዕስ ከአእምሮ ህመም ጋር የተያያዙ አጫጭር ታሪኮችን የያዘ መጽሐፍ አሳትመዋል። እርሳቸው እንደሚናገሩት፣ ኅብረተሰባችን ስለ አእምሮ ህመም ያለው ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ ነው። በዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች በቀላሉ ሊድን የሚችል የአእምሮ ህመም አጋጥሟቸው ወደ ሕክምና ተቋማት ስለማይመጡ ሳይታከሙ ቀርተው ይሰቃያሉ። ይህም ሥራቸው፣ ትምህርታቸውና የፍቅር ሕይወታቸው ላይ ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል።

ከባድ የአእምሮ ህመም ከሚገጥማቸው 10 ታማሚዎች ውስጥ ወደ ሕክምና ተቋም የሚሄደው አንድ ሰው ብቻ ነው። ዘጠኙ ጎዳና ላይ ይወጣሉ አሊያም ቤት ውስጥ ታስረውና በተለያየ መልክ የስቃይ ሕይወትን ይመራሉ ይላሉ።

«በሀገራችን የአእምሮ ጤና መታወክ የገጠማቸው ሰዎች የሚገጥማቸውን መገለል በአራት ከፍሎ ማየት ይቻላል» የሚሉት የአእምሮ ስፔሻሊስቱ፣ የመጀመሪያው ተቋማዊ ነው። ለአእምሮ ጤና ሕክምና የሚሰጠውን ትኩረት፣ የሚመደበው በጀትና በየሆስፒታሉ ውስጥ የአእምሮ ተኝቶ ሕክምና አልጋዎችን ለማስፈቀድ ሲሞከር የሚያጋጥመው ፈተና መዋቅራዊ የሆነ ማግለልና መድሎ እንዳለ ያሳያል ይላሉ።

ሁለተኛው የአእምሮ ህመም የገጠማቸው ሰዎች ላይ በግለሰብ ደረጃ የሚፈጸም ማግለል መሆኑን በመግለጽ፣ በአእምሮ ህመም የሐኪም ፈቃድ ይዘው የሚሄዱ ሰዎች በአለቆቻቸው ዘንድ የሚስተናገዱበት መንገድ በግለሰብ ደረጃ የሚደረግ ማግለል መኖሩን እንደሚያመለክት ይጠቁማሉ።

ዮናስ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ በሦስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ማግለል በራሳቸው በታማሚዎቹ የሚፈጸም ሲሆን ታማሚዎቹ ራሳቸው የአእምሮ ህመም ስላለብኝ ምንም ማድረግ አልችልም ብለው ራሳቸውን የሚያገሉበት ነው። አራተኛው በተለያዩ አባባሎች፣ ቀልዶችና ተረቶች ለአእምሮ ህመም ዝቅተኛ ግምት በመስጠት የሚደረግ ሥነ ልቦናዊ የሆነ ማግለል ነው። በአማርኛ ቋንቋ ተረትና ምሳሌ «እብድና ብርድ ያስቃል በግድ» እንዲሁም «እብድ የያዘው ፊት አይበረክትም» የሚሉት አባባሎችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

በተጨማሪም በብዛት በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚሰራጩ ትክክል ያልሆኑ ሃሳቦች መኖራቸውን የሚገልጹት የአእምሮ ስፔሻሊስቱ፣ የአማኑኤል መድኃኒት ያጀዝባል፤ የአእምሮ ህመም አይታከምም እንደሚባልና ከአእምሮ ህሙማን ጋር ተያይዘው የሚነገሩ በርካታ አሉታዊ ቀልዶች እንዳሉ ያነሳሉ።

«በሀገራችን የአእምሮ ህመም 27 በመቶ የሆነውን ሕዝብ አጥቅቷል ስንል እስከ 30 ሚሊዮን የሚጠጋ ሰው በአንድ ወይም በሌላ ወቅት የእአምሮ ህመም ያጋጥመዋል ማለት ነው» ያሉት የአእምሮ ስፔሻሊስቱ፤ ችግሩ ብዙዎቻችን የአእምሮ ህመም የሚመስለን ልብሱን አውልቆ መንገድ ላይ የሚሮጥ ሰው ነው።

ከአጠቃላይ የአእምሮ ህመሞች አንጻር እዚህ ደረጃ የሚደርሱት አንድ በመቶ ያህል ናቸው። የተቀሩት በቀላሉ የማናስተውላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ህመሙ የሁላችንንም ቤት የሚያንኳኳ ነው ማለት ይቻላል። ነገር ግን ማግለል ስላለ ብዙዎች በግልጽ ለመናገር አይደፍሩም በማለት የችግሩን ስፋትና አሳሳቢነት ይገልጻሉ።

የአእምሮ ሕክምና አገልግሎትን ስንመለከት ጥራት ያለው ተደራሽ የሕክምና አገልግሎት የለም። በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ያለው የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አማኑኤል ነው። ከህመሙ ስርጭት አንጻር አንድ ሆስፒታል በቂ ስላልሆነ በየአራቱም አቅጣጫ የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ያስፈልጋሉ። በተጨማሪም በሁሉም ሆስፒታሎች ውስጥ ለአእምሮ ሕክምና የተመደቡ አልጋዎች መኖር አለባቸው ሲሉም ያክላሉ።

መፍትሔ ነው የሚሉትን ሃሳብ ሲጠቁሙም፤ የአእምሮ ሕክምና ላይ ሁለት ነገር ያስፈልጋል አንደኛው ግንዛቤ ነው። ሁለተኛው ጥራት ያለውና ተደራሽ አገልግሎት ነው። ከዚህ መነሻነት ኅብረተሰባችን ስለአእምሮ ጤና ያለውን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ ይኖርበታል፤ የሚመለከታቸው አካላት ደግሞ ለአእምሮ ሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ተደራሽ ጥራት ያላቸው አገልግሎቶች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ይመክራሉ።



ዶ/ር መስከረም አበበ



ዶ/ር ዮናስ ላቀው

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የአእምሮ ሕክምና እና ትምህርት ክፍል ኃላፊዋ ዶክተር መስከረም አበበ በበኩላቸው፣ ኅብረተሰባችን ስለአእምሮ ህመም ያለው ግንዛቤ በፊት ከነበረው የተወሰነ ለውጥ አለው። ነገር ግን አሁንም ቢሆን በጣም ይቀረዋል። ማኅበረሰባችን ለአእምሮ ህመም ያለው አመለካከት በጣም አናሳ ነው። ሰዎች በአእምሮ ህመም ከተጠቁ ምንም ጥቅም እንደሌላቸው ወይም ምርታማ እንደማይሆኑ አድርጎ የማሰብ ነገር አለ ይላሉ።

የአእምሮ ጤና ላይ ያለውን የግንዛቤ እጥረት ለመቅረፍ ምን መደረግ እንዳለበት ሲያመላክቱም የጤና ፖሊሲ አውጪዎች፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሰፊው ሊሠሩበት ይገባል። የአእምሮ ሕክምና ባለሙያዎች የአእምሮ ህመም ምን እንደሆነ፣ ምልክቶቹን እንዲሁም የአእምሮ ጤንነትን እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል በየጊዜው ለማኅበረሰቡ በማስረዳት በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ይገባቸዋል ነው ያሉት።

ማኅበረሰቡ የአእምሮ ህመም ያለበትን ሰው ወደ ሕክምና እንዲሄድ ማበረታታት፤ የተለያዩ ስሞችን ከመስጠት መቆጠብና ፍቅርና እንክብካቤ ማድረግ አለበት በማለት የተቀናጀ ሥራ መሠራት እንዳለበት ጠቁመዋል።

በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን በተደጋጋሚ በሚቀርቡ መረጃዎች በሀገራችን ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች ቁጥሩ እየጨመረ መምጣቱን እየተመለከትን ነው። አብዛኞቹ የአእምሮ ህመሞች ወደዚህ ሁኔታ ሊገፉ ይችላሉ። አንድ ሰው በአእምሮ ህመም ሲጠቃ ለዚህ ሁኔታ ተጋላጭነቱን ይጨምራል። ሚዲያዎችም ራሱን ስላጠፋ ሰው የሚዘግቡበት መንገድ ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባል። አንድ ሰው ራሱን ያጠፋበትን ሂደት በዝርዝር ማቅረቡ ሌሎች ሰዎች እንደ አንድ ችግርን መገላገያ ዘዴ እንዲቀበሉት ሊያበረታታ ይችላልና መገናኛ ብዙኃን በዚህ ጉዳይ ላይ ዘገባ ሲሠሩ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ መክረዋል።

ማንኛውም ሰው ራስን የማጥፋት ሃሳብ የሚመጣበት ከሆነ ለቤተሰብ ለጓደኛ ወይም ደግሞ ለአእምሮ ሐኪሞችና ለሥነልቦና ባለሙያዎች ማማከር ይኖርበታል ያሉት የአእምሮ ሐኪሟ፣ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የአእምሮ ጤናውን መንከባከብ፤ ለህመሙ ከሚያጋልጥ ነገር ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል ያሉት መስከረም (ዶ/ር)፣ «በአእምሮ ህመም የሚሰቃይ ሰው ሕክምና የማግኘት እንዲሁም አድሎና መገለል እንዳይደረግ የመጠበቅ ሙሉ መብት እንዳለው ገልጸዋል። ኅብረተሰቡ ይህንን በመገንዘብ ለህመሙ የተጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በመንከባከብ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል» በማለት አሳስበዋል።

የአእምሮ ሕመም (Mental Illness) አንድ ሰው የሚሰማውን ስሜት፣ ሃሳቡን፣ ጸባዩንና ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙነት በከፍተኛ ደረጃ የሚያውክ የአእምሮ ጤና መታወክ ነው። ዕድሜ፣ ጾታ፣ የገቢ ሁኔታ ወይም ዘር ሳይለይ ሁሉም ሰው ለአእምሮ ጤና መታወክ የመጋለጥ ዕድል እንዳለው የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

ዜና

# የማኅበረሰቡን መብት ሊያስጠብቅ የሚችል አዲስ የጫኝና አውራጆች መመሪያ ተዘጋጀ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የማኅበረሰቡን መብት ሊያስጠብቅና ቀደም ሲል ሲታዩ የነበሩ ችግሮች ሊፈታ የሚችል አዲስ መመሪያ መዘጋጀቱ የአዲስ አበባ ሠላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ የሕዝብ አደረጃጀት ዘርፍ ሰሞኑን 2016 የመጀመሪያ የሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ አካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠላምና ጸጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ሚደቅሳ ከበደ እንደገለጹት፤ ማኅበረሰቡ በርካታ ቅሬታ ሲያነሳበት የነበረውን የጫኝና አውራጆች አሠራር የሚያሻሽል አዲስ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ከጫኝና አውራጆች ጋር በተያያዘ ከከተማዋ ነዋሪ የተለያዩ ቅሬታዎች ለቢሮው ሲደርሱት መቆየቱን ገልጸው፤ በሩብ ዓመቱ ሲነሱ የቆዩትን ቅሬታዎች የሚፈታና የማኅበረሰቡን መብት የሚያስጠብቅ አዲስ መመሪያ መዘጋጀቱንና አሠራር መዘርጋቱን ገልጸዋል፡፡

መመሪያው ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት መዘጋጀቱን የገለጹት ምክትል ኃላፊው አሠራሩን ለማሻሻል የነበረውን አደረጃጀት በማፍረስ፣ በሕገወጥ የሚሠሩትን ወደ ሕጋዊነት የማምጣትና የማስተካከል ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡



አቶ ሚደቅሳ ከበደ

አቶ ሚደቅሳ ቀድሞ በነበረው አሠራር ጫኝና አውራጆች ከአቅም በላይ ዋጋ የሚተምኑበትና ባለ ንብረት እራሱ ዕቃውን ማውረድ የማይችልበት እንደነበር አስታውሰው፤ በአሁኑ መመሪያ ግን ባለንብረቱ ጫኝና አውራጅ አያስፈልገኝም እራሴ ማውረድና መጫን እችላለሁ ካለ ሙሉ ነፃነት የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ክፍያን በተመለከተም ቢሮው የገበያ ጥናት በየአካባቢው በማድረግ አማካይ ዋጋ በመውሰድ ተመን ማውጣቱንና ጫኝና አውራጆች ከዚህ ተመን በላይ ማኅበረሰቡን ማስከፈል እንደማያስችሉ በመመሪያው መካተቱን አብራርተዋል፡፡

ምክትል ኃላፊው ቀድሞ የነበረው መመሪያ ጫኝና አውራጅ ማኅበራት ሌሎችን ወክለው አልያም ቀጥረው ማሠራት ይፈቅድ እንደነበረ አውስተው፤ በተሻሻለው አዲሱ መመሪያ ጫኝና አውራጆች በውክልናም ሆነ ቀጥረው ማሠራት እንደማይችሉና ለሚጭኑትና ለሚያወርዱት ዕቃም ሙሉ ኃላፊነት እንደሚወስዱ ገልጸዋል፡፡ ይህም የማኅበረሰቡን ሙሉ ጥቅም የሚያስከብር መመሪያ መሆኑ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በአዲሱ አደረጃጀትም ጫኝና አውራጆቹ ጥሩ ሥነ ምግባር ያላቸው፣ ማኅበረሰቡን ሲያገለግሉ የነበሩና በበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ የተሳተፉ እንዲሁም በሠላም መጠበቅ ላይ ጉልህ ሚና ለነበራቸው ቅድሚያ መሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

አቶ ሚደቅሳ ከዚህ በተጨማሪም በሩብ ዓመቱ ኅብረተሰቡ የሠላም ባለቤት ከማድረግ አኳያ አካባቢውን እንዲጠብቅ መሥራት መቻሉና በዚህም በከተማዋ የወንጀል ምጣኔ የቀነሰበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

# የመቀለ የውሃ ፕሮጀክትን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**


መንግሥት በትኩረት እየሠራ ነው፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከያዛቸው ሁለት ትላልቅ ፕሮግራሞች መካከል በከተሞች ላይ የንፁህ ውሃ እና ሳኒቴሽን ግንባታ እንደሆነ የጠቀሱት ኃላፊው፤ የተቋረጡ የመቐለ እና ዓዲግራት የውሃ ፕሮጀክቶችን ማስቀጠል የዚህ ፕሮግራም አካል ናቸው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በከተሞቹ ላይ የሚደረገው ግንባታ እስከ አሁን የኤሌክትሮ ሜካኒካል ዕቃዎች የተቃጠሉ ፓምፖች ለመተካት የግዢ ኮንትራት ተፈርሞ በአስቸኳይ ወደ ግዢ መገባቱን አመላክተዋል፡፡

በዚህም የመቐለ ከተማን የውሃ ፕሮጀክት ለማስቀጠል የአንድ ሚሊዮን ዶላር ዕቃዎች ግዢ መፈፀሙን አመላክተው፤ ዓዲግራት የውሃ ፕሮጀክትን የማስቀጠል ሥራም የግዢ ሂደት ላይ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

እነዚህ ፕሮጀክቶች የውሃ ችግር ቁልፍ መፍትሄ እንደሚያመጡ የጠቆሙት ኃላፊው፤ ሌላ በወረዳ እና አነስተኛ ከተሞች ትኩረት በማድረግ የሚሠራ ፕሮጀክት እንዳለ በመጥቀስ፤ ሥራውን ለመቀጠል የተወሰነ ሲሆን፤ ተግባራዊ የሚደረገውም በራሱ በክልሉ እንደሆነና ገንዘብ ተመድቦ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል ሲሉ ገልፀዋል፡፡



ፕሮጀክቱ የጋራ መፀዳጃ ቤቶች ግንባታም የሚያጠቃልሉ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በአፋጣኝ የውሃና ሳኒቴሽን ችግሮችን እንዲቀርፉ ለማስቻል እየተሠራ መሆኑን የተናገሩት ኃላፊው፤ ቀደም ሲል በክልሉ ላይ ተበላሽተው የነበሩት ትላልቅ የውሃ ፓምፖች እና ጄኔሬተሮች ግዢ ተደርጎ ሥራ እንዲጀምሩ ተደርጓል ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ ፕሮጀክቱ በድርቅ እና በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች በተለይ ቦረና፣ አፋር እና አማራ ክልል ላይም ትኩረት በመስጠት በመንግሥትና በአፍሪካ ልማት ባንክ ፋይናንስ ተደርጎላቸው ዘላቂ መፍትሄ እንዲመጣ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

# ኢፕድ እና ዘ ኮሪያ ታይምስ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አቀፍ ቋንቋዎች መረጃን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

ኢፕድ ታሪክ በመሰነድ ለትውልድ እያስተላለፈ የሚገኝ ተቋም መሆኑን ገልጸው፤ ዘ ኮሪን ታይምስ ጋዜጣም የ73 ዓመት ታሪክ ያለው ተቋም በመሆኑ በጋራ መሥራታቸው ለተሻለ ውጤት እንደሚያበቃቸው ገልጸዋል።

ሁለቱ አንጋፋ ተቋማት አብረው መሥራታቸው የሀገራቱን ታሪክ እየሰነዱ ለትውልድ ከማሻገር ባለፈ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለማጠናከር ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል።

ኢፕድና ዘ ኮሪያን ታይምስ በሕትመት የሚዲያ ዘርፍ በየአህጉራቸው ቀደምት ከሆኑ ተቋማት መካከል ናቸው ያሉት አቶ ጌትነት፤ ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ከማጠናከርና የጋራ መግባባት እንዲኖር ከማድረግ ባለፈ በሕትመት ሚዲያው ያላቸውን ተሞክሮ እንዲጋሩ፣ በመረጃ ልውውጥ፣ በአቅም ግንባታ፣ በኦንላይን ሚዲያውና በሌሎች ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት ይረዳል ብለዋል፡፡

ኢፕድና ዘ ኮሪያን ታይምስ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት ስምምነት ላይ በመድረሳቸው ደስተኞች ነን ሲሉ አቶ ጌትነት ተናግረዋል።

የዘ ኮሪያ ታይምስ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሚስተር ቾ ጃ ሀዮን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ዘ ኮሪያ ታይምስ የ73 ዓመት ታሪክ ያለው አንጋፋ ጋዜጣ መሆኑን አስታውሰው፤ በአሁኑ ወቅት በሚዲያዎች በኩል ትብብር አስፈላጊ በመሆኑ በመረጃ ልውውጥና በተለያዩ ጉዳዮች ከኢፕድ ጋር በጋራ እንሠራለን ብለዋል፡፡

ስምምነቱ ለተሻለ ለውጥና ለጋራ ዕድገት የሚበጅ መሆኑን ጠቁመው፤ የተቋማቸውን የረጅም ጊዜ ልምድን በማካፈልና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ በማድረግ ስምምነቱን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

በደቡብ ኮሪያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ደሴ ዳልኬ በበኩላቸው፤ ሁለቱም የሚዲያ ተቋማት አንጋፋ በመሆናቸው በጋራ ለመሥራት መፈራረማቸው ያካበቱትን ልምድና አዳዲስ መረጃዎችን ለመለዋወጥ መልካም ዕድልን ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል።

ሁለቱ የሚዲያ ተቋማት ስምምነት ማድረጋቸው መረጃን ከመለዋወጥ ባለፈ ለማኅበረሰቡ ማድረስ ስላለባቸው መረጃዎች ተቀራርበው እንዲሠሩ ያግዛል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያና በደቡብ ኮሪያ መካከል ያለውን የቆየ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያነሱት አምባሳደሩ፤ አሁን ላይ ሁለቱ አንጋፋ የሚዲያ ተቋማት አብረው ለመሥራት መስማማታቸው የሀገራቱ ዲፕሎማሲ ላይ በጎ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሕትመት ዘርፍ ከ82 ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ የሚዲያ ተቋም ሲሆን፤ የዘ ኮሪያን ታይምስ ድርጅት ደግሞ ላለፉት 73 ዓመታት በሚዲያ ዘርፉ እየሠራ የሚገኝ ተቋም መሆኑ ታውቋል።

# የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያን ወደ ገናና የዕድገት ደረጃ የሚያደርስ አዲስ ኃይል ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያን ወደ ገናና የዕድገት ደረጃ የሚያደርስ አዲስ ኃይል ነው ሲሉ የኢፌዴሪ መከላከያ የውጭ ግንኙነትና ወታደራዊ ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሜጀር ጀኔራል ተሾመ ገመቹ ገለጹ፡፡

ተቀማጭነታቸውን አዲስ አበባ ያደረጉ ወታደራዊ አታሼዎችና የዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች የዓባይ ግድብን ትናንት ጎብኝተዋል፡፡

የኢፌዴሪ መከላከያ የውጭ ግንኙነትና ወታደራዊ ትብብር ዳይሬክተር ሜጀር ጀኔራል ተሾመ ገመቹ በጉብኝቱ ወቅት እንደገለጹት፤ የዓባይ ሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያን ወደ ታለመላት ልማትና የዕድገት ደረጃ የሚያደርስ አዲስ ኃይል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ቀደምት ከምትታወቅባቸውና ዝናዋን ከፍ ካደረጉ ቀደምት እሴቶች በተጨማሪ የዓባይ ግድብ ሌላ ተደማሪ አቅም ሆኖ የመጣ ነው ብለዋል፡፡

የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ከምትታወቅበት የማንነት መገለጫዎች አንዱ ነው ያሉት ሜጀር ጀኔራሉ፤ ግድቡ ትልቅ ብሔራዊ ኩራት መሆኑን ታስቦ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ግድቡ ከግብ እንዲደርስ አሁንም ሁሉም የበኩሉን መወጣት አለበት ያሉት ሜጀር ጀኔራል ተሾመ፤ ግድቡ በኢትዮጵያውያን ገንዘብ፣ እውቀትና ላብ እየተገነባ የሚገኝ አዲስ ብሔራዊ ኩራት መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ሜጀር ጀኔራል ተሾመ፤ ሠላምን ለማረጋገጥ የሁሉም ኃላፊነት ነው ያሉ ሲሆን፤ መንግሥት ሠላምን ለማስከበር የራሱ የሆነ ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ሕዝቡ ለሠላም መስዋዕትነት መክፈል አለበት ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራትና ለቀጣናው ሠላም እንዲረጋገጥ የበኩሏን ድርሻ ከማበርከት አኳያ ጉልህ ሚና የምትጫወትና እየተጫወተች የምትገኝ ሀገር እንደሆነችም ነው ሜጀር ጀኔራል ተሾመ የጠቆሙት፡፡

ኢትዮጵያ የሠላምና የልማት ዘብነቷን ወደ ፊትም አጠናክራ እንደምትቀጥል ሜጀር ጀኔራሉ ተናግረዋል።

እንደ ሜጀር ጀኔራሉ ገለጻ፤ ሠራዊቱ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ነፃነት እንዳይደፈር እንዲሁም የሕዝቦቿ ሠላም በማረጋገጥ ዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት እንዲቻል የሚጠበቅበትን ተግባር ያከናውናል፡፡

የሠራዊቱ የውጭ ግንኙነት ዲፕሎማሲ በመተማመንና የጋራ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጡ ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ያስታወሱት ሜጀር ጀኔራሉ፤ የዓባይ ግድብ ቀጣናውን በልማት የሚያስተሳስር ግዙፍ ፕሮጀክት መሆኑን ተናግረዋል።

የጉብኝቱ ዓላማም ወታደራዊ አታሼዎች ግድቡ ቀጣናውን በልማት ለማስተሳሰር ያለውን ፋይዳ እንዲሁም በታችኛው የተፋሰስ ሀገራት ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በአካል ተገኝተው እንዲመለከቱና እውነታውን እንዲረዱ ማድረግ መሆኑንም አመልክተዋል።

# «ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

64 ሚሊዮን በቤንዚን የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የሚለቁትን በካይ ጋዝ የማስወገድ ያክል አስተዋጽኦ አለው ሲሉ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ ከአረንጓዴ ዐሻራ ሥራዎች ባለፈ በስንዴ ልማትና በግብርና ሥራዎች ውጤት ማስመዝገቧን አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሳዑዲ - አፍሪካ ጉባኤ ጎን ለጎን ከጂቡቲ ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኦመር ጊሌህ እና ከሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሃሰን ሼህ ሞሃመድ ጋር ተወያይተዋል።

ከሳዑዲ - አፍሪካ ጉባኤ ጎን ከወንድሞቼ የጂቡቲ ፕሬዚዳንት ኢስማኤል ኦመር ጊሌህ እና የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሃሰን ሼህ ሞሃመድ ጋር በሁለትዮሽና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸውን በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው አስታውቀዋል፡፡

የሳውዲ-አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ የሳውዲ መንግሥት ከአፍሪካ ሀገራት ጋር በቀጣናዊ የጸጥታ ስጋቶች ዙሪያ ለመወያየት፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ትብብሮችን ለማሳደግ እንዲሁም የኢነርጂ መፍትሄዎች እና የኢንቨስትመንት አማራጮች ዙሪያ በትብብር ለመሥራት በማሰብ ያዘጋጀው ጉባኤ መሆኑ ተገልጿል።

ጉባኤው በሪያድ እየተካሄደ ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ጨምሮ የበርካታ ሀገራት መሪዎች በጉባኤው ለመሳተፍ ወደ ስፍራው አቅንተዋል፡፡

በጉባኤው ላይ የሳውዲ ዐረቢያ-አፍሪካ ግንኙነት፣ የእሥራኤል ፍልስጤም ጦርነት እንዲሁም ሌሎች አጀንዳዎች ተነስተው ውይይት ይደረግባቸዋል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተገልጿል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት

የውስጥ ገጾች



ገጽ 6

## ‹‹ከሀገራችን አልፈን

## ለአፍሪካ ኮንስትራክሽን መሠረት የሚጥል ተቋም መገንባት እንፈልጋለን››

- ኢንጂነር ዮናስ አያሌው

- የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ




የምናባዊ
ዕይታ ኃይል

ገጽ 12



የታዛው ስር ዋርካ ...

ገጽ 16

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ከሀገራችን አልፈን ለአፍሪካ ኮንስትራክሽን መሠረት የሚጥል ተቋም መገንባት እንፈልጋለን››

*-የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ዮናስ አያሌው*

እፀገነት አክሊሉ

የአንድ ሀገር የእድገት ደረጃ ከሚታይባቸው የልማት እንቅስቃሴዎች መካከል የኮንስትራክሽን ዘርፉ ቀዳሚና ተጠቃሽ ነው፡፡ኮንስትራክሽን ባሕልን የሥልጣኔ ደረጃን እንዲሁም የወደፊት ሕልምን ለማሳየት የሚያግዝ ከመሆኑ ጋር በተያያዘም ሀገራት እድገታቸው በዛ ሊለካ ይችላል፡፡

ኢትዮጵያም ረዘም ያለ የኮንስትራክሽን ጥበብ ባለቤት እንደመሆኗ ባሕሏን ወጓን የሥልጣኔና የእድገት ደረጃዋን ለማሳየት የሚያስችሉ በርካታ የኮንስትራክሽን ግንባታዎች ባለቤት ናት፡፡ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በዘርፉ አንጋፋና ብዙ የሥራ ልምዶች ያሉት በሀገር ደረጃም አንቱ ያስባሉትን ሥራዎች ያከናወነ ነበር። ነበር ያልንበት ዋናው ምክንያት ደግሞ በሥራ ሂደቱ ላይ ተፈጥረውበት በነበሩ ችግሮች ከዘርፉ ባይወጣም የሚጠበቅበትን ያህል ሚና እንዳይወጣ እንቅፋት ሆነውት ስለቆየ ነው፡፡

ተቋሙ ዛሬ በሚያስደንቅ ቁመና ላይ ያለ ከመሆኑም በላይ ወደፊት ከራሱ አልፎ ለሀገር ተስፋን የሚያጭሩ ሥራዎችን እየሠራ በአስደናቂ ብቃት ላይ የሚገኝ ሆኗል፡፡እኛም ይህንን የተቋሙን እድገትና የወደፊት ራዕዩን አስመልክተን ከተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ዮናስ አያሌው ጋር ቆይታን አድርገናል፡፡መልካም ንባብ፡፡

**አዲስ ዘመን፦ የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን የለውጥ እሳቤዎቹ እንዲሁም ሀገራዊ ተልዕኮዎቹ ምንድን ናቸው?**

**ኢንጂነር ዮናስ፦** የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን መድረስ ያለበት ቦታ ለመድረስ የሚያስችሉትን በርካታ የለውጥ ሥራዎች ሠርቷል። ነገር ግን ሁሉም ጅምር ናቸው ብሎ መውሰዱ ጥሩ ነው፡፡ በሌላ በኩልም ለለውጡ መነሻ የሆኑት ነገሮች በጠቅላላ በሀገራችን ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ችግር ነው፡፡

በሀገራችን ላይ ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መነሻ ተደርጎ እንዲሁም ደግሞ እንደዚህ ዓይነት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ያሉባቸውን ችግሮች ፈተን ለሀገር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለውጥ መሠረት መጣል የሚያስችል ተቋም መገንባትን መሠረት ያደረገ ሥራ ነው፡፡በመሆኑም የእኛ የሪፎርም ሥራ ግንባታዎችን መገንባት አልያም ከኮንስትራክሽን ጋር የተገናኙ ሥራዎችን መሥራት ብቻ ሳይሆን ምናልባትም ከሀገራችን አልፈን ለአፍሪካ ኮንስትራክሽን መሠረት የሚጥል ተቋም መገንባት የሚል ነው፡፡

እዛ ለመድረስም የተለያዩ ጎዳናዎችን መጓዝ ነበረብን ከዚህ መካከል ቀዳሚው ተቋም እንደየትኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ከለውጡ በፊት በጣም ብዙ ችግሮች የነበሩበት ነበር፤ በተለይም የአቅም ማነስ፤ ብክነት፤ የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ቴክኖሎጂን ከመጠቀም አንጻር ብዙ ችግሮች ነበሩ፡፡በሌላ በኩልም ባለሙያዎችና አመራሮች የሚሠሩትና እቅዶቻቸውን የሚተገብሩበት መንገድ የዘልማዳዊ አይነት ነበር። ፕሮጀክት የሚመራ ተቋም ይሁን እንጂ ፕሮጀክት ለመምራት የሚያበቃ ሥርዓትን ተከትሎ አልነበረም የሚመራው፤ ሠራተኛውና አመራሩ መካከል የነበሩ ልዩነቶች ችግሮች በጣም ከፍተኛ ነበሩ፡፡

አመራሩ ሠራተኛውን አያገኘውም በዚህ መካከል ደግሞ በሠራተኞች ከፍ ያለ ቅሬታ ነበራቸው፡፡ይህ ሁኔታ ደግሞ በሠራተኛ ማኅበር በመገናኛ ብዙኃን ሁሉ ይቀርብ ነበር፡፡እነዚህ የተቋሙ ውስጣዊ ችግሮች ሲሆኑ ከውጭ ደግሞ ዓለም አቀፍ መነሻዎችን መሠረት ያደረጉ ሥራዎችን መሥራት አለመቻሉ ነው። እነዚህን ችግሮች በሚቀለብስ መልኩ እንደ አዲስ ተቋሙን ሪፎርም የማድረግ ሥራዎች አከናውነናል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ለዚህ የሪፎርም ሥራችን መነሻ የሆነን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር መሥራት መቻላችን ነው፡፡

እንደ አጋጣሚ ሆኖ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፕሮጀክቶች እሳቸው እየመሩ ሠርተናል፤ ይህ ደግሞ በተለይም እሳቸው የሚመሩበትን የአካሄድ ሥርዓት ወደራሳችን ለመውሰድ ቻልን፡፡በሌላ በኩልም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፕሮጀክቶች በሚመሩበት አግባብ ሌሎቹንም መምራትና ማስተዳደር የሚቻል ከሆነ ትልቅ ስኬትን ለማምጣት እንደሚቻል ማሳያ ሆኑን። በመሆኑም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የሠራናቸውን አንድ ሁለት ፕሮጀክቶች ተሞክሮ አድርገንም ለለውጥ መነሻ አደረግነው፡፡

ሪፎርሙ ከመጀመሩ በፊት በምሥራቅ አፍሪካ ካሉ መሰል ተቋማት አንዱ መሆን የሚል ራዕይ ተቀምጦ ነበር ፡፡እውነት ለመናገር ግን ተቋሙ በነበረው ቁመና እንኳን ከምሥራቅ አፍሪካ ከሀገር ውስጥም ተወዳዳሪነቱ ምን ያህል ነው የሚለውን ማየት ያስፈልግ ነበር ፤ ምክንያቱም እዚህ እደርሳለሁ ተብሎ ሲታቀድ የቱ ጋር ነኝ? ምን ሠርቼ ነው የምደርሰው? የሚለውም መታየት ያለበት ወሳኝ ጉዳይ ነውና፡፡የእኛ ቪዝን የተቀመጠው ይህ በውል ሳይታወቅ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ተቋሙ ላለፉት በርካታ ዓመታት በሥራው ላይ የነበረ ብዙ ልምዶች ያሉት በርካታ አንቱታን ያተረፈባቸውን የግንባታ ሥራዎች በጥሩ ሁኔታ ያከናወነ ቢሆንም መካከል ላይ በተፈጠሩበት ችግሮች ከጨዋታ ውጪ የሆነ ተቋም ነበር፤ እንዴት አድርጎ ነው የምሥራቅ አፍሪካ ተወዳዳሪ የሚሆነው የሚለውን በደንብ ያልታየና ያልታሰበበት ነበር፡፡

በመሆኑም ይህንን ማጥራት ብዙ ሥራ የሚፈልግ ነበር፤ ነገር ግን እኛ ወደተቋሙ ከመጣን በኋላ በችግሮቹ ዙሪያ ቁጭ ብለን ውይይት በማድረግና እንደ አጠቃላይም የአመራር ለውጥ አድርገን በለውጥ አስተሳሰብ መሥራት የሚችሉ አመራሮችን ተክተን ሥራዎችን ለመሥራት ሞክረናል፡፡

አመራሩን ለመቀየራችን ዋናው ምክንያት ደግሞ ተቋምን ሪፎርም ማድረግ ጥሩ ሆኖ ሳለ በውስጡ አላሠራ በማለት ሲጎትቱ የነበሩ አካላትን ይዞ መቀጠል ተገቢ ስላልሆነ በመጀመሪያ የተሄደበት ተቋማዊ ሪፎርም መሥራት ላይ ነው፡፡

ተቋሙ ሪፎርም መሆን እንዳለበት አምነናል፤ ተስማምተናል፡፡ነገር ግን አሠራሩ በሠራተኞች ላይ ያለው አስተሳሰብ የተጠያቂነት ደረጃና ዓይነት በጠቅላላው በተቋሙ ላይ ያሉ ችግሮች ሳይፈቱ ወደሪፎርም መሄድ ማለት ተቋሙ ሊለውጠው ሳይሆን ሊያጠፋው የሚችል ስለነበር በቀጥታ ትኩረታችንን ያደረግነው ችግሮችን መፍታት ላይ ነበር፡፡

በውስጥ የነበሩብንን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ከፈታን በኋላ በቀጥታ ያመራነው ተቋሙን ሪፎርም ወደማድረጉ ነበር፤ በዚህም ለሠራተኛው ምቹ የሆነ የሥራ አካባቢን መፍጠር፡፡ሠራተኛውና አመራሩ መካከል ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ፡፡ሠራተኛው የተሰጡትን ተልዕኮዎች ፈጽሞ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችሉ ማትጊያዎችን ማድረግ፡፡ከገንዘብ ጋር ያሉበትን ጥያቄዎች በደመወዝና በጥቅማ ጥቅም መመለስ፡፡የተቋሙ ሀብት ሳይባክን ጥቅም ላይ የሚውልበትን አሠራር መቀየስ፡፡ተቋሙ ተጨማሪ ገቢን የሚያገኝባቸውን ሥራዎች መሥራት። ከሁሉም በላይ ደግሞ ከተቋሙ ጋር የሥራ ውል አስረው ለማሠራት እምነት አጥተው የነበሩ አገልግሎት


ፎቶ ሳሙኤል ተስፋዬ

**መልካም ዕድሎችን ሁሉ ተጠቅመን አስቻይ ሁኔታዎችን በሙሉ አይተን ሀገራችንን በኮንስትራክሽኑ ዘርፍ የምትጠቀስና የምትጠራ ብሎም በራሷ አምርታ የምትገነባ ለማድረግ እየሠራን ነው**

ፈላጊዎች እምነታቸው እንዲመለስ የማድረግ ሥራዎችን በመሥራት ዛሬ ላይ ተቋሙ መቶ በመቶ ስኬታማ ሥራን እየሠራ ስለመሆኑ መናገር የሚቻልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡

**አዲስ ዘመን፦ አሁን ላይ ተወዳዳሪ ተቋም መገንባት ችላችኋል ማለት ይቻላል ? አሁን ያለበትን ሁኔታስ ከቀድሞ አንጻር ሲታይ እንዴት ይገልጹታል?**

**ኢንጂነር ዮናስ፦** አዎ፤ አሁን ላይ በተቻለ መጠን ተወዳዳሪና ብቃት ያለው ተቋም እየተገነባ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡

በተለይም ከፕሮጀክቶች መምራት ጋር ያሉብንን ችግሮች መቅረፍ ችለናል፡፡ፕሮጀክት የመምራት እውቀት ሲባል እንግዲህ አንድ ፕሮጀክት ሲመጣ እንደሚጠናቀቅ ማሰብ መቻልን ይጠይቃል፤ ከዚህ ቀደም አንድ ፕሮጀክት ከ 7 እስከ 10 ዓመት እጃችን ላይ የሚዘገይበት ሁኔታ ነበር፤ ይህንን ለማስቀረት ዓላማው ያደረገውን ሪፎረም ወደተግባር ስናስገባ ግን አሁን ላይ ተቋሙ ቀጣይነት ባለው ሪፎርም እንዲመራ የማድረግ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ነን፡፡

በዚህም በተለይም ተቋሙ የነበረበትን የሪፎርም ማኔጅመንት ችግር ከ 80 በመቶ በላይ መሻገር የቻልንበትና ስኬት የሚባለው ደረጃ ላይ እየደረስን ያለንበት ጊዜ ላይ ነን፡፡ፕሮጀክቶችንም በተያዘው ዕቅድ መሠረት የማስረከብ ብቃት ላይ ደርሰናል፡፡

**አዲስ ዘመን፦ የኮንስትራክሽን ሚኒስትር ያወጣቸውን የፕሮጀክት አስተዳደር መመሪያዎች ከራሳችሁ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አስታርቃችሁ የመጠቀም ሁኔታውን እንዴት ይገልጹታል?**

**ኢንጂነር ዮናስ፦** አዎ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እንዲሁም ዓለም አቀፍ ከሆኑ ሌሎች ኢንስቲትዩቶች የሚመጡትንም የፕሮጀክት አስተዳደር ሥርዓቶች ከራሳችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመሥራት አካሄድን እየተከተልን ነው፡፡በሌላም በኩል የራሳችን የሆኑ 16 የፕሮጀክት አስተዳደር መመሪያዎችን በማበልጸግ እየተጠቀምን ነው፡፡በመሆኑም ከላይ እንደጠቀስኩት ፕሮጀክት አስተዳደር ሪፎረም ብለን የራሱ የሆነ መለያ (ሎጎ) አስቀምጠን ተግባራዊ አድርገናል፡፡

የፕሮጀክት አስተዳደር እውቀት ማለት እንግዲህ አንድ ፕሮጀክት ለተቋሙ ሲሰጠው እንደሚያልቅ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ከሀገራችን አልፈን ለአፍሪካ...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ማሰብ ማለት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የነበረው አስተሳሰብ ፕሮጀክት ሲመጣ ገንዘብ ይዞ ይመጣል የሚል ብቻ ነበር፤ ይህ ደግሞ በአብዛኛው ሠራተኛ አዕምሮ ውስጥ ለዘመናት የተቀመጠ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቶች እስከ አስር ዓመት የሚጓተቱበት ሁኔታ ነበር፡፡

ነገር ግን የሀገራችንንም የሌሎች ዓለማትንም ተሞክሮ በመቀመር በሠራነው የሪፎርም ሥራ አሁን ላይ በርካታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መጠናቀቅ እየቻሉ ነው፡፡በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ ሥርዓት ከመፍጠርም ባሻገር ተጠያቂነትም እንዲኖር በማስቻል አሁን ላይ ተቋሙ በማያቋርጥ የሪፎርም አስተሳሰብ ውስጥ እንዲቀጥል ለማድረግ ተችሏል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ትልቁ ተግዳሮት የግብዓት ችግር እንደሆነ ተደጋግሞ ይነሳል እናንተም በሪፎርም ላይ ሆናችሁ ብዙ ሥራዎችን በመቀበል ላይ ከመሆናችሁ አንጻር ይህንን ችግር እንዴት እያስፋችሁት ነው?**

**ኢንጂነር ዮናስ ፡-** እስከ አሁን በያዝነው ለውጥ በፕሮጀክት አፈጻጸም ደረጃችን 80 በመቶ ላይ ነን ካልን ለምንድን ነው 20 በመቶውን ማሳካት ያልቻልነው? ወደሚለው ነው በቀጥታ የገባነው፤ ለዚህ እንደ ምክንያት ያገኘነው ደግሞ የአቅርቦትና የምርት ችግር ነው፤ ይህ በምን ይፈታል ስንል ደግሞ ኢንዱስትሪያላይዜሽን የግድ መሆኑን ተረዳን፤ በተለይም በያዝነው ፍጥነት ተጉዘው በመላው ሀገሪቱ እንዲሁም በአፍሪካ ፕሮጀክቶችን የምንዘረጋ ከሆነ እንዴት ባለው መልኩ ነው ልንከታተል የምንችለው በማለት ዲጂታላይዜሽን እና ኢንዱስትሪያላይዜሽን ሪፎርም ወደማድረጉ ገባን፡፡

በነገራችን ላይ ለምሳሌ እንደ አገር በቁጥር በዛ ያሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ቢኖሩንም ለእኛ ተቋም በምንፈልገው ልክ እያቀረቡልን አይደለም፡፡ለምሳሌ ተቋማችን በዓመት በጣም ብዙ ሚሊዮን ኩንታል ነው የሚያስፈልገን ነገር ግን አሁን ላይ እየቀረበልን ያለው አንድ አራተኛ እንኳን አይሆንም፤ ይህ ደግሞ በተቋሙ የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ የሆነ ችግር እየፈጠረ ነው፡፡

ሌላው የሚመጡ ሴራሚኮችና የማጠናቀቂያ (ፊኒሺንግ) ዕቃዎች ከውጭ አገር መግባታቸው ሌላው ችግር ነው፡፡በመሆኑም እነዚህን ነገሮች ከውጭ የሚመጡትንም በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እጥረት ያለባቸውንም ነገሮች በቂ አቅርቦት እንዲኖራቸው የኢንዱስትሪያላይዜሽን ጉዟችንን ከምን እንጀምር ብለን ተነሳን፤ በዚህም እስኪ እጃችን ላይ ባለው የተገጣጣሚ ፕሮጀክት መምሪያ ማሽኖቻችን ከወዳደቁበት አንስተን በማስተካከል ወደ ሥራ እናስገባ ብለን አስገባናቸው። በተጨማሪም ከውጭ የሚገባውን የአልሙኒየም ብረት እየቆራረጥን በመገጣጠም ትርፋማና ውጤታማ ለመሆን ቻልን፡፡

በተመሳሳይ ከውጭ የሚመጣውንም ጂፕሰም በሀገር ውስጥ በማምረት ውጤታማ ለመሆን ቻልን። በጠቅላላው በኢንዱስትሪያላይዜሽን ጉዟችን የእንጨት በር፡፡አልሙኒየም ጂፕሰም እና ሌሎችንም በማምረት እየሠራን ሲሆን በቀጣይም እንደ ማርብልና ሌሎችንም ለማምረት የሚያስችሉ ሂደቶች ላይ እንገኛለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ያለውን የፕሮጀክት አስተዳደር እውቀታችንን እንዴት ይገልጹታል?**

**ኢንጂነር ዮናስ፡-** በጣም ትልቅ ክፍተት አለበት። በጣም ውስን ባለሙያዎች ሳይት ላይ ፕሮጀክት እንዴት እንደሚመራ እውቀትና ልምድ አላቸው ፤ ነገር ግን ፕሮጀክት መርተው የማያውቁ ምን እንደሆነ እንዴት እንደሚመራ በራሱ ምንም እውቀት የሌላቸው ሰዎች ሕግና ሥርዓቱ ስለሚፈቅድላቸው ብቻ ፕሮጀክት ማኔጀር ይሆናሉ፡፡



በዚህ ደግሞ ፕሮጀክት ማለት ሠራተኛ ግብዓትና ማሽን በቦታው ላይ አስገብቶ ሥራ ማስጀመር የሚመስለው በጣም ብዙ ባለሙያ እየተፈጠረ ነው። በመሆኑም መምራቱ በእውቀት የተመራ መሆን ይኖርበታል፡፡አሁን ላይ ችግሩ አሳሳቢ በመሆኑ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ሥልጠናዎችን መስጠት ጀምሯል፡፡ይህ ብቻውን በቂ ስላልሆነ እኛም እንደ ተቋም የራሳችን የሥልጠና ማዕከል ያስፈልገናል በማለት ከትምህርት ቤት የወጡ መሐንዲሶችን በደንብ ኮትኩተን መሪ መሆን የሚያስችል እውቀት ልናስጨብጣቸው የሥልጠና ማዕከል አቋቁመናል፡፡የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎችም በቅርቡ ትምህርታቸው ይጀምራሉ፡፡

ይህ የተቋሙ የሥልጠና ማዕከል ሰዎች ሥራቸውን እየሠሩ የሚሠለጥኑበት ሲሆን የፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት እንዲሁም ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የሥልጠና ማዕከሉን ከጎበኙ በኋላ በመደነቅ ይህ ከእናንተ አልፎ የእኛንም ባለሙያዎች የምናሠለጥንበት እንዲሆን ማስፋት አለባችሁ የሚል ሀሳብ ነው የሰጡን።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ ያለውን እድል እንዴት ይገልጹታል?**

**ኢንጂነር ዮናስ፡-** ኢትዮጵያ እንደአዲስ እየተገነባች ያለች ሀገር ነች፡፡ስለዚህም በዚህ ሙያ ውስጥ ያለን በሙሉ ሰፊ ዕድል አለን፡፡ዕድለኞች ነን፤ ዕድለኞች ብቻም ሳንሆን በሙያችን ልንኮራ የሚገባን ነው። ይህንን ያልኩበት ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያውያን መሐንዲሶች ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ ሀገራቸውን ገንብተዋል፤ ይህ አይነቱ ዕድል ግን በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የለም፤ ለምን መሰላችሁ አፍሪካን የገነቧት በተለያዩ ምክንያቶች የመጡ የውጭ አገር ዜጎች በመሆናቸው ነው፡፡

በመሆኑም ይህንን ዕድል እኛ እንደ ተቋም በቀላሉ የምናየው አይደለም፡፡መልካም ዕድሎችን ሁሉ ተጠቅመን አስቻይ ሁኔታዎችን በሙሉ አይተን ሀገራችንን በኮንስትራክሽኑ ዘርፍ የምትጠቀስና የምትጠራ ብሎም በራሷ አምርታ የምትገነባ ለማድረግ እየሠራን ነው፡፡

በነገራችን ላይ አሁን ከለውጡ ወዲህ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ የማጠናቀቁ ሂደት በመሻሻል ላይ ነው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምረውታል ከተማ አስተዳደሩም በዛው መንገድ እየሄደ ነው፤ ነገር ግን አሁንም በቀደመው የፕሮጀክት አስተዳደር ውስጥ እየዳከሩ ያሉ ተቋማት እንዳሉም ይታያል፡፡

በመሆኑም ተቋማት ፕሮጀክቶችን የሚያዩበትን መነጽር መቀየር አለባቸው፡፡አሁን ጊዜው ተለውጧል። በአንድ ቀን መፈታት የሚችሉ ችግሮች ዓመታት እየተሻገሩ መንግሥትን ላልተገባ ወጪ እየዳረጉ ኅብረተሰብንም እያማረሩ ነው፡፡ በመሆኑም አሁን ላይ ፕሮጀክት ስንጀምር ከምንም በላይ የተጠያቂነት ሥርዓትን አበጅተን ሊሆን ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋማችሁን ዓለም አቀፍ ደረጃ ያሟላ እንዲሆን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ካሉ ቢያብራሩልን ?**

**ኢንጂነር ዮናስ፡-** አዎ አምና 2015 ዓ.ም ላይ ኢንተርናሽላይዜሽን የሚል ነገር ጀመርን፡፡ በዚህም ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ግንኙነቶችን ማድረግ ነበረብን፤ የተለያዩ አምራቾች ፋብሪካዎች ተቋማትም አብረውን ይሠሩ ዘንድ የስምምነት ፊርማዎችን ተፈራረምን፤ በሌላ በኩልም ከሕንድ ቻይናና ዱባይ ካምፓኒዎች ጋር የጋራ ካምፓኒ ስምምነት በመፈራረምና 30 በመቶ እነሱ 70 በመቶውን እኛ በማድረግ ፋብሪካውን በዚህ ዓመት ሥራ እናስጀምራለን ብለናል።

ከሀገር ውስጥ ካምፓኒ ጋርም ሴራሚክ ለማምረት የመጀመሪያውን ስምምነት ጨርሰን ወደቀጣይ ምዕራፍ የመሄዱን ነገርም ጀምረነዋል፡፡

ከሁሉም በላይ ይህ ተቋም ሁልጊዜ ከብሔራዊ ባንክ ዶላር እየለመነ ብቻ መሥራት የለበትም፤ ወደውጭ ሀገር ሄዶ በመሥራት ራሱም የዶላር ምንጭ መሆን አለበት በማለት አሁን ለጊዜው ጅቡቲ ላይ የግንባታ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ነን። በዚህም ያለፉትን ሁለትና ከዚያ በላይ ዓመታት ከመንግሥት ምንም ዓይነት ዶላር አልወሰድንም። ወደፊትም በጅቡቲ የጀመርነውን ኬንያ፡፡ደቡብ ሱዳንና ደቡብ አፍሪካ እንቀጥላለን። በነገራችን ላይ ሌሎችም ሀገሮች ቅርንጫፍ ክፈቱ እንጂ እያሉ እየጠየቁን እኛም እየሠራንበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡

ሌላው ዓለም አቀፍና አፍሪካዊ የሆኑ ስብሰባዎችን በመካፈል በኩልም ለመጀመሪያ ጊዜ በኮንስትራክሽን ሙያ ላይ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ለውይይት የሚቀርብበት ፎረም አዘጋጅተን ነበር፡፡እኛም እንደ ተቋም (ቢግ 5) የሚባል በዱባይ ዓለም የሚገኝበት መድረክ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በመሳተፍና ተቋማችንን እንዲሁም ሀገራችንን በማስተዋወቅ ተመልሰናል፡፡ በቀጣይም እነሱም ወደ ሀገራችን መጥተው እየተሠሩ ያሉትን ሥራዎች ተመልክተው ጥሩ ግንኙነት ፈጥረን የተመለስንበት ነው፡፡

ይህም ቢሆን ግን እኛ ከእነሱ ጋር ስንነጻጸር የቱጋር ነን? የሚለውን እንመልከት በማለት ፌዴሬሽን ኦቭ አፍሪካ ኢንጂነሪንግ ኦርጋናይዜሽን እንዲያወዳድረን በማመልከት ተወዳደርን በዛው ወርቅ አግኝተናል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ተቋሙ አሁን ላይ በግብርናው ዘርፍም እየተሰማራ ነውና ፤ እስኪ ስለእሱ ትንሽ ይንገሩን?**

**ኢንጂነር ዮናስ፡-** እንግዲህ እኛም በተለይ ለሥራችን አጋዥ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የግድ የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ማየት ይጠይቃልና እኛም በኩራዝ እያለማን ያለነውን የመስኖ ሥራ ወደ ግብርናውም ብናሰፋው ጥሩ ነው በሚል 6 መቶ ሄክታር የእርሻ መሬት በመረከብና ትራክተሮችን በመግዛት ባለሙያዎችን በመቅጠር ወደሩዝ ምርት ገብተናል፡፡

ይህንንም ምርት በአንድ ጊዜ ወደ ውጭ እንልከውም፤ ነገር ግን በቀጣይ የምናመርተው ምርት ወደውጪ የሚላክ እንዲሆን እናስባለን። በዚህም በጊዜ ሂደት ከውጭ አልሚዎች ጋር በጋራ ሠርተን ወደውጭ በመላክ ዶላር ማምጣት የምንችልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ነገን ዛሬ እንደሚገነባ ተቋም ግን ለእርስዎ የስኬቶቹ ምንጭ ምንድናቸው ይላሉ?**

**ኢንጂነር ዮናስ፡-** ዋናው የአመራርና የሠራተኛው ትጋት ነው፡፡ በነገራችን ላይ እዚህ ተቋም ውስጥ ቁጭት ያለበት ብዙ ሠራተኛ አለ፡፡የሚያሠራን አመራር እስካለ ድረስ ብዙ መሥራት እንችላለን የሚሉ ባለሙያዎች በርካታ ናቸው፡፡የመንግሥት በቅንነት የመደገፍ ሁኔታዎችም ለስኬቱ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

መንግሥት እንደእኛ ያሉ የልማት ድርጅቶች ነፃ ሆነው ሠርተው አትራፊ እንዲሆኑ ከሀገራቸው አልፈው አፍሪካ ላይ እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል፡፡

አሁን እኛ የምንለው ተሳክቶልናል ሳይሆን የስኬት መስመር ውስጥ ገብተናል ነው፡፡ተሳካልን ልንል የምንችለው ዓለም አቀፍ ተቋም ሆነን ለሀገራችንና ለሕዝባችን ማድረግ የምንችለውን ሁሉ ስናደርግ፤ ዓለም ላይም ተወዳዳሪ ሆነን ስንመረጥ ነውና እሱ ላይ ለመድረስ እንሠራለን፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ተቋማችሁ በጥሩ አቋም ላይ የሚገኝ ነውና ወደፊትስ የት መድረስ ነው ሕልሙ?**

**ኢንጂነር ዮናስ፡-** አዎ የእኛ ራዕይ ቀደም ብለን ስንነሳ በምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ ካሉት ተመሳሳይ ተቋማት ከአንድ እስከ አምስት መሆን ነበር። አሁን ይህ ተቀይሯል፤ አሁን የወርቅ ደረጃ ላይ ነን፡፡ይህ ደግሞ መሪ አድርጎናል በመሆኑም አፍሪካዊ ተቋም ወደማድረጉ ነው የምንሄደው፡፡ አፍሪካውያን እንዲያውቁ ከእነሱ ጋር ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር ዓለማቀፋዊነት ሥራችንን መሠረት እናስይዛለን፡፡

የእኛ ቀዳሚ ሆኖ መውጣት ብቻውን ሚዛን ስለማይደፋ በአፍሪካ አገራት ያሉ አምባሳደሮች ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ተሳታፊ እንዲሆኑና እኛንም እንዲያግዙን ጥሪ እናቀርባለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ፡፡**

**ኢንጂነር ዮናስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ማህደረ ጤና

# ትብብር የሚሻው ፖሊዮን የማጥፋት ስራ

**አስናቀ ፀጋዬ**




ፖሊዮ (ፖሊዮሚለትስ) ተብሎ የሚጠራው የልጅነት ልምሻ በሽታ በ1800 አካባቢ እንደተከሰተ የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ ያመለክታል፡፡የልጅነት ልምሻ በዋናነት የሚያጠቃው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን ሲሆን ከሰው ወደ ሰው በንክኪ፣ በቫይረሱ በተበከለ ምግብ እና ውሀ አማካኝነት ወደ ሰውነት ሲገባ እንደሆነ የጤና ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡በሽታው ዓይነት 1፣ ዓይነት 2፣ እና ዓይነት 3 በሚባል ይታወቃል። በዘላቂነት የሰውን የአካል ቅርፅ በመቀየርም ለአካል ጉዳት ይዳርጋል፡፡ከዚህ አለፍ ሲል ደግሞ በሽታው ለሞትም ያበቃል፡፡

በአንድ ወቅት ፖሊዮ እንደሌሎች በሽታዎች ሁሉ ዓለም አቀፍ ስጋት ነበር፡፡በፖሊዮ ወይም የልጅነት ልምሻ ምክንያት በዓለም ዙሪያ በርካታ ሕፃናት ለአካል ጉዳተኛነት፣ ባስ ሲል ደግሞ ለሞት ተዳርገዋል፡፡ እንደ የዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ፖሊዮ በ1900 በወረርሽኝ መልክ በኢኮኖሚ አደጉ በተባሉ አገሮች ተከስቷል።

ሆኖም በሽታው በሕክምና የማይድን መሆኑን የተረዳው የዓለም የጤና ድርጅት ታዲያ እኤአ በ1988 በሽታውን በክትባት መከላከል የሚያስችል ስልት በመቀየሱና ተግባራዊ በማድረጉ በወቅቱ የልጅነት ልምሻ በነበረባቸው 125 አገራት በየዓመቱ ይመዘገብ የነበረው 350ሺህ የልጅነት ልምሻ በሽታ በዓመት ወደ 175 መውረድ ችሏል፡፡በዚህም በርካታ ሕፃናትን ከአካል ጉዳተኛነትና ከሞት መታደግ ተችሏል፡፡

ምንም እንኳን እንደ ሁልጊዜው ሁሉ አዲስ ክትባት ሲገኝ በቅድሚያ ተደራሽ የሚሆነው ላደጉት ሀገራት ቢሆንም ኢትዮጵያን ጨምሮ ለሌሎች ታዳጊ ሀገራት በሂደት የፖሊዮ ክትባቱ ደርሷቸው ህፃናቶቻቸውን ከትበዋል፡፡በዚህም በጊዜው ሊደርስ የሚችለውን የአካል ጉዳትና ሞት መቀነስ ችለዋል፡፡ ሆኖም አሁንም ድረስ ፖሊዮ፣ በተለይ ገና አዳጊ በሆኑ ሀገራት ለሕፃናት አካል ጉዳተኛ መሆንና ሞት መንስኤ መሆኑን ቀጥሏል።

እንዲህም ሆኖ ኢትዮጵያ የልጅነት ልምሻን በክትባት ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡በአስመዘገበችው ውጤትም ኢትዮጵያ ከፖሊዮ ነፃ ተብላ የምስክር ወረቀት አግኝታ ነበር፡፡ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም ከበሽታው ነፃ ተብለው የነበረ ቢሆንም ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት በሶማሌ ክልል የፖሊዮ ቫይረስ ያለበት ግለሰብ በመገኘቱ ክትባቱ እንደገና እንዲጀመር ምክንያት ሆኗል፡፡

በሽታውን ለመከላከል ክትባት ዋናው መፍትሔ መሆኑን በመገንዘብም እስካሁን ድረስ በሁለት ዙር የፖሊዮ ክትባት ዘመቻ ተደርጓል፡፡በዚህም በተደረገ የመጀመሪያ ዙር ክትባት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ16 ሚሊዮን በላይ ሕፃናትን መከተብ ተችሏል፡፡ በሁለተኛው ዙር የፖሊዮ ክትባትም ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት በሀገር አቀፍ ደረጃ ተከትበዋል፡፡

እንግዲህ ፖሊዮ በአደጉት ሀገራት ታሪክ ሆኖ ከቀረ የሰነበተ ቢሆንም ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች ገና በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገራት ምንም እንኳን እየቀነሰ እንደመጣ ቢነገርም አሁንም አልጠፋም፡፡ በተለይ ደግሞ በአፍሪካ በዋናነት ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገራት ፖሊዮ አሁንም ድረስ አለ፡፡በፖሊዮ ምክንያት ሕፃናት አሁንም አካል ጉዳተኛ ይሆናሉ፤ ይሞታሉ፡፡በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስከተብ ዝግጁ አለመሆን፣ በቀጠናው የሚታዩ የፀጥታ ችግሮችና የፖሊዮ ክትባት ተደራሽ እንዳይሆን ተፅእኖ ማሳደርና ሌሎችም ምክንያቶች በሽታው ከቀጠናው እንዳይጠፋ ምክንያት ሆነዋል፡፡በኢትዮጵያም የሚታየው ይኸው ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው እንግዲህ ዓለም አቀፍ የፖሊዮ ቀን ‹‹በጋራ ፖሊዮን እናጥፋ›› በሚል መሪ ቃል ባሳለፍነው ሳምንት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች በኢትዮጵያ የተከበረው፡፡በርግጥ የፖሊዮ ቀን ፖሊዮ በኢትዮጵያ ከተከሰተበት ግዜ ጀምሮ ይከበራል፡፡ዋናው ቁም ነገሩ ግን በየዓመቱ ቀኑን እየጠበቁ ማክበር ብቻ እንዳልሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ፖሊዮን ለማጥፋት በሚደረገው ርብርብ ከሕብረተሰቡና ከመንግስት በኩል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግንና በትብብር መስራትን ይጠይቃል፡፡በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች በክትባት ተደራሽ ለመሆን በተለይ በግጭት ቀጠና ያሉ ቦታዎች ወደ ሰላም ሊመለሱና የክትባት ስራውን ሊያግዙ ይገባል፡፡ሕብረተሰቡም ቢሆን በአንዳንድ የተዛቡ መረጃዎች ምክንያት ልጁን ከማስከተብ ወደ ኋላ ማለት የለበትም፡፡ይህም ጤና ሚኒስቴር ሁሌም የሚጎተጉተው ጉዳይ ነው፡፡

የጤና ሚኒስትር ዲኤታ ዶክተር ደረጀ ዱጉማ እንደሚናገሩት እስካሁን ድረስ ፖሊዮን ከናካቴው ከሀገሪቱ ለማጥፋት ባይቻልም፣ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ1988 ጀምሮ ዓለም አቀፉ ፖሊዮን ጨርሶ የማጥፋት ንቅናቄ /Global Polio Eradication Initiative - GPEI/ያስቀመጠቻቸውን ዋና ዋና የፖሊዮ ማጥፋት ስልቶች በመተግበር በርካታ ስራዎችን ሰርታለች፡፡ በዚህም ከ99 ነጥብ 9 በመቶ በላይ የፖሊዮ ጉዳቶችን መቀነስ ችላለች፡፡በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕጻናትም ከሕመም፣ ከሞትና ከአካል ጉዳተኝነት አትርፋለች። በዚህ ስኬት ውስጥም የጤና ሚኒስቴር አመራሮችና ባለሙያዎች፣ አጋር ድርጅቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በኢትዮጵያ የክትባት አገልግሎት ታሪክ ከአራት አስርት ዓመታት በላይ እንዳስቆጠረ ይነገራል፡፡ከነዚህ የክትባት አገልግሎቶች ውስጥ ታዲያ አንዱ የፖሊዮ ክትባት ነው፡፡የፖሊዮ ክትባት በኢትዮጵያ መሰጠት ከተጀመረ ወዲህ በርካታ ሕጻናትን ከሞት፣ ከሕመምና ከአካል ጉዳት ለመታደግ ተችሏል፡፡በሌላ በኩል እንደ ሀገር የኮቪድ_19 ክትባትን ጨምሮ፣ ከአስራ ሶስት በላይ ሌሎች የክትባት አይነቶች ለሕጻናትና ለሕብረተሰቡ እየተሰጡ ይገኛሉ፡፡በአሁኑ ግዜ ደግሞ የማሕፀን በር ካንሰር በሽታ መከላከያ ክትባት እድሜያቸው 14 ዓመት ለሆናቸው ሴት ልጆች እየተሰጠ በመሆኑና የማህፀን በር ካንሰርን በክትባት መከላከል ስለሚቻል ሕብረተሰቡ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ጤና ሚኒስቴር ይጠይቃል፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ ከፖሊዮ ነፃ ሆኖ ለማደግ ሁሉም ሕፃናት ክትባት የማግኘት መብት እንዳላቸው በመገንዘብ ቤት ለቤት የክትባት አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን በቁርጠኝነት በመስራት ሙሉ በሙሉ ፖሊዮን በማጥፋት ከስነ-ልቦና ጫናና ከአካል ጉዳት መታደግ ይገባል፡፡ለዚህም ከጤና ሚኒስቴር በተጨማሪ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ወሳኝ ነው፡፡ፖሊዮ ወይም የልጅነት ልምሻን ሕፃናትን በወቅቱ የክትባት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ መከላከል የሚቻል ከመሆኑ አኳያ መከላከል ላይ ይበልጥ ትኩረት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል፡፡ይህም በፖሊዮ ምክንያት በሕፃናት ላይ ለሚደርሰው የአካል ጉዳት ድጋፍ ሊወጣ የሚችለውን ወጪ ለመቀነስ ያስችላል፡፡

**ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ1988 ጀምሮ ዓለም አቀፉ ፖሊዮን ጨርሶ የማጥፋት ንቅናቄ /Global Polio Eradication Initiative - GPEI/ያስቀመጠቻቸውን ዋና ዋና የፖሊዮ ማጥፋት ስልቶች በመተግበር በርካታ ስራዎችን ሰርታለች**

የዓለም ጤና ድርጅት ተወካይ ዶክተር ፖል ሜይኑካ በበኩላቸው እንደሚሉት አሁንም ቢሆን ከፖሊዮ ነጻ የሆነች ኢትዮጵያና አፍሪካን ለመፍጠር ቅንጅታዊ ስራዎችና ትብብሮች ይበልጥ መጠናከር እንደሚገባቸው ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ፖሊዮን ለማጥፋት በፅኑ ፍላጎትና በቁርጠኝነት መስራት ያስፈልጋል፡፡ለዚህ ታዲያ በሀገር ውስጥ ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ እስከ ታችኛው ሕብረተሰብ ክፍል ድረስ ፖሊዮን ለማጥፋት ከሚደረገው የጋር ርብርብ በተጨማሪ የዓለም ጤና ድርጅት የፖሊዮ በሽታ ከኢትዮጵያ እስኪወገድ ድረስ የገባውን ቃል መጠበቅ ይኖርበታል፡፡አስፈላጊውን ድጋፍም አጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

በርግጥ ፖሊዮን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት በሚደረጉ ጥረቶች ብዙ ለውጦች እየመጡ ነው፡፡የኢትዮጵያ ጤና ሚኒስቴር ባደረገው ከፍተኛ ጥረትና ፖሊዮን የማጥፋት ዘመቻ እ.ኤ.አ በሰኔ ወር 2017 በአፍሪካ ክልላዊ የፖሊዮ ማጥፋት ኮሚሽን ባካሄደው መደበኛ ክትትል ሂደት ኢትዮጵያ ከዱር ፖሊዮ-ነፃ በመሆን እውቅና ማግኘቷ የዚህ ለውጥ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ይህም ስኬት የተገኘው የጤና ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሰራቸው ጠንካራ ስራዎችና የኢትዮጵያ መንግስት ከአጋር ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶ በመስራቱ ነው፡፡

በጤና ሚኒስቴር የእናቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጤና አገልግሎት መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶክተር መሰረት ዘላለም እንደሚገልፁት ከፖሊዮ ነፃ ሆኖ ለማደግ ሁሉም ሕፃናት ክትባት የማግኘት መብት እንዳላቸው በመገንዘብ ቤት ለቤት የክትባት አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን በቁርጠኝነት በመስራት ሙሉ በሙሉ ፖሊዮን ጨርሰን በማጥፋት ከስነ-ልቦና ጫናና ከአካል ጉዳት መታደግ ያስፈልጋል።

በተለይ ደግሞ በገጠራማ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ የፖሊዮ ክትባትን በስፋት ተደራሽ በማድረግ ፖሊዮን ለማጥፋት የተጀመረውን አጠቃላይ ዘመቻ አጠናክሮ ማስቀጠል የግድ ይላል፡፡ግጭቶች በነበሩባቸውና በግጭት ምክንያት ተፈናቅለው በመጠለያ ቦታዎች የሚገኙ ሕፃናትንም በተመሳሳይ በክትባት ተደራሽ መሆንና ሕፃናቱን ከአካል ጉዳትና ከሞት ማዳን ለነገ የሚተው ተግባር አይደለም፡፡ለዚህ ደግሞ እስከታች ድረስ ያሉ የክልል መዋቅሮችና ጤና ሚኒስቴር በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡

በዚህ በ2023ቱ “በጋራ ፖሊዮን እናጥፋ” በሚል ባሳለፍነው ሳምንት በተከበረው ዓለም አቀፍ የፖሊዮ መታሰቢያ ቀን ጉባዔ ላይ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የፖሊዮ በሽታ አሁን ላይ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ገለፃ በጤና ሚኒስቴር ባለሙያዎች ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ታዳጊ የአፍሪካ ሀገራት፣ በተለይ ከሰሃራ በታች ያሉት በፖሊዮ ክትባት ተደራሽ ሆነው ፖሊዮን እንዲያጠፉ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሀሳቦችና ስትራቴጂዎችም ቀርበዋል፡፡ የልምድ ልውውጥም ተካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ፣ የአጋር ድርጅቶች ኃላፊዎችና ተወካዮች፣ ከኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የተጋበዙ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎችም በተገኙበት፣ በቀጣይ ከፖሊዮ ነፃ የሆነች ኢትዮጵያን በመፍጠር ሂደት ምን ሊደረግ እንደሚገባ የሚያመለክቱ አቅጣጫዎች ተቀምጧል፡፡

ሁሌም ቢሆን ‹‹ፖሊዮን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት›› እየተባለ በየዓመቱ ይነገራል፡፡ፖሊዮ ግን ሲጠፋ አልታየም፡፡ስለዚህ ፖሊዮ ከኢትዮጵያ ጠፍቶ ልክ እንደሌሎቹ ሀገራት ታሪክ ሆኖ እንዲቀር የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡በቁርጠኝነት መስራት ከተቻለ ደግሞ ፖሊዮን ከኢትዮጵያ ማጥፋትና ፖሊዮን ለማጥፋት የሚውለው ገንዘብ ለሌሎች የልማት ስራዎች ማዋል እንደሚቻል የብዙዎች እምነት ነው፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# የአፍሪካን ቀንድ ቀጣናዊ የጋራ ልማትና እድገት ፍላጎቶች ለማሳካት የፌደራሊዝም እሳቤዎች አስፈላጊነት

**ኃይለየሱስ ታዬ ( ዶ/ር)**
**በፌደራሊዝም ጥናት ረዳት ፕሮፌሰር**

በአፍሪካ ቀንድ በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ሕዝቦች የዘላቂ ሰላም፤ የልማት እና እድገት ተስፋቸው በጥብቅ የተሳሰረ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም በቀጣናው በሚገኙ ሀገራት የሚኖሩ ሕዝቦች አሰፋፈር እና ትስስር፤ በጋራ እያሳለፏቸው ያሉ ሰው ሠራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋዎች፤ በጋራ ጥቅም ላይ ቢውሉ ቀጣናውን ይበልጥ ሊያስተሳስሩ እና ለቀጣናው ሰላም እና እድገት ሊውሉ የሚችሉ ሃብቶች መኖር ተስፋቸው የተሳሰረ መሆኑን አመላካቶች ናቸው፡፡

የትስስሩ አስፈላጊነት በዚህ ብቻ አያበቃም፤ ለረጅም ጊዜ ቀጣናው ከሚታወቅበት ተከታታይነት ካላቸው ግጭቶች፤ ስር የሰደደ ድህነት፤ ስደት፣ መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎቶችን እንኳ ለማሟላት ከለጋሽ ሀገራት እና ድርጅቶች ላይ ያለ እና የተጣባ ጥገኝነት ለመላቀቅ ሀገራቱ በጋራ የሚያስተሳስራቸው ጠንካራ ሥርዓት ማበጀት አሁን በምንገኝበት ክፍለ ዘመን የግድ ይላቸዋል፡፡

ሀገራቱ በየራሳቸው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ ሆኖ በተመረጡ እና ለቀጣናው መሠረታዊ ለውጥ በሚያመጡ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ ፍላጎትን መሠረት ባደረገ መልኩ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ የሚመሩበት በፌደራላዊ እሳቤ የሚመራ አደረጃጀት ፈጥረው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

ይህን ማድረግ ካልቻሉ፤ ለቀጣናው ማኅበረሰብ እንደ ጥቅልም ሆነ በየሀገራቱ የሚኖሩ ዜጎችን ዘላቂ ሰላም፤ የኢኮኖሚ፤ ማኅበራዊ ዕድገት እና የኑሮ መሻሻል ምላሽ እየሰጡ ከሌሎች የዓለም ክፍሎች ጋር እኩል የሚራመዱበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። ለዚህም ቀጣናው ከአሳለፋቸው እና እያሳለፋቸው የሚገኙ ነባራዊ ሁኔታዎች ግልጽ ምስክሮች ናቸው፡፡

ሉዓላዊ በሆኑ ሀገራት መካከልም የሚኖር ዘላቂ እና በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ፤ በጋራ በተሻለ መልኩ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን የሚፈታ፤ በጋራ ቢለሙ እና የጋራ ተጠቃሚነት ቢያረጋግጡ የተሻለ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ እንዲሁም የግጭት ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በጋራ ስምምነት ግልጽ በሆነ አግባብ እና አደረጃጀት የሚመራበት ሥርዓት ፈጥሮ ለመንቀሳቀስ ፌደራላዊ እሳቤዎችን መከተል ያስፈልጋል፡፡

ፌደራሊዝም በባሕሪው በአብሮነት የግል እና የጋራ ፍላጎቶችን ዴሞክራሲዊ እና ሚዛናዊ በሆነ አግባብ አቀናጅቶ ለሰው ልጆች ነፃነት፤ እኩልነትን፤ ሰላም፤ እድገት እያረጋገጡ የሚሄዱ አደረጃጀቶች በየደረጃው ተደራጅተው ወደ ሥራ መግባትን የሚደግፍ እና የተለያዩ ቅርጽ ያላቸው ፌደራላዊ የፖለቲካ ሥርዓቶችን አቅፎ የሚይዝ ፍልስፍና ነው። የሁሉንም መብት እና ፍላጎት በውይይት፤ በንግግር እና በመተማመን ማስከበር የሚያስችል የጋራ የሆነ ሥርዓት የሚፈጠርበት እሳቤ ነው፡፡

ፌደራሊዝም ሀገራት እንደ ሀገር፤ በቀጣና ደረጃ፤ በአህጉር እንዲሁም በዓለም ደረጃ በግል እና በጋራ ቢከናወኑ የተሻለ ውጤት ሊያመጡ እና የሰው ልጅን እና የሚኖርበትን ምሕዳር አስናስለው የበለጠ ተጠቃሚ ሊደርጉ የሚችሉ ጉዳዮች በየደረጃው ተለይተው እና ተሳስረው የሚፈጸሙበትን አሠራር፤ ሥርዓት እና አደረጃጀት የሚደግፍ ነው፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሀገራዊ ጉዳዮቻቸውን ከጋራ ጉዳዮቻቸው ጋር አስተሳስረው በቅንጅት እና በትብብር ካልሠሩ ሀገራት ችግሮቻቸውን ቀርፈው በጋራ የማደግ ተስፋቸው የተመናመነ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። በተለይም በከፋ ችግር እና ድህነት ውስጥ ባለው የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ችግሮችን በዚህ መልኩ መፍታት ካልተቻለ፤ ችግሩ ይበልጥ እየተባባሰ በከፋ መልኩ ለቀጣዩ ትውልድ ከመተላለፍ ባለፈ ሌላ መውጫ በር ይኖራል ተብሎ አይታሰብም።

በዓለም ላይ ካሉ የፌደራሊዝምን እሳቤ ከሚጋሩ አደረጃጀቶች የአውሮፓ ኅብረትን የአጀማመር ሁኔታ በአጭሩ መመልከት ተገቢ ነው። የአንድን ችግር ምንጭ በጋራ በማስተዳደር ለጋራ ጥቅም ለማዋል የሚያስችለውን እሳቤ በመያዝ፤ የራስ አስተዳደር እና የጋራ አስተዳደር አስተሳስሮ እና አናቦ የተጀመረው የአውሮፓ ኅብረት አሁን ላይ የደረሰበትን እና እየሄደበት ያለውን እርቀት ሲታይ አስተማሪነቱ ከፍ ያለ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የአውሮፓ ኅብረት ጥንስስ በ1951 እ.አ.አ በስድስት አውሮፓ ሀገሮች የተመሠረተው የአውሮፓ የዴንጋ ከሰል እና ብረት ማኅበረሰብ (European Coal and Steel Community) መሆኑ ይታወቃል፡፡መነሻ ሃሳቡ አውሮፓውያኑ በተከታታይ ግጭቶች እና በሁለት የዓለም ጦርነቶች ያሳለፋቸውን ችግሮች ላለመድገም ሀገራቱ ያላቸውን የድንጋይ ከሰል እና ብረት አስተዳደር ወደ ጋራ አስተዳደር ለማምጣት ነው፡፡

ይህ በሀገራት መካከል ሊኖር የሚችል የግጭት ፍላጎት በመቀነስ በጦር መሣሪያ የታገዘ ኃይል የተቀላቀለበት ግጭትን ለማካሄድ የሚያስችል ማቴሪያል ማግኘት የማይታሰብ እንዲሆን ለማድረግ የተከናወነ ነው። በተለይም በፈረንሳይ እና በጀርመን መካከል የነበረውን ግንኙነት በትብብር ላይ የተመሠረተ በማድረግ የጋራ የሆኑ ጉዳዩችን በጋራ ማከናወን ታሳቢ ያደረገ ነበር፡፡

ለዚህ ለአውሮፓ ኅብረት መጀመር መነሻ የሆነ እንቅስቃሴ በፈረንሳይ የወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበሩት ሮበርት ሹማን ከፍተኛ ሚና እንደተጫወቱ እና በስማቸው የሚጠራው የሃሳብ መግለጫ ሰነድ (shuman declaration) ለማኅበረሰቡ መመሥረት መነሻ ተደርጎ ይወሰዳል። ጀን ሞኔት ደግሞ የማኅበረሰቡ አደረጃጀት ነዳፊ ተደርገው የሚወሰዱ ሲሆን የመጀመሪያው ፕሬዚዳንቱም ነበሩ።

የነዚህ ቁልፍ ሰዎች ተግባር የሚያመላክተን ለቀጣናቸው ሰላም እና እድገት አርቀው የሚያስቡ እና የፌደራሊዝም እሳቤ የተላበሱ መሪዎች የአውሮፓን ዘላቂ ሰላም እና የጋራ እድገት አሻገረው በማየት የመነሻ ጥንስሱን የጠነሰሱ የፖለቲካ መሪዎች መሆናቸውን ነው። ከነዚህ መሪዎች የአፍሪካን ቀንድ ሰላም እና ደህንነት፤ ልማት እና እድገት የሚመኙ እና የወደፊቱን የቀጣናውን ብሩህ ተስፋ አሻግረው የሚያዩ የፖለቲካ መሪዎች ብዙ ሊማሩ ይገባል።

**እስከ አሁን በቀጣናው ሴራውም፤ መጠላለፉም፤ መጋጨቱም ተሞክሮ አዋጭ ሆኖ አልተገኘም፤ በግል እንደ ሀገር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከሀገር ሀገር የሚለያዩ አፈጻጸሞች ያሏቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ የሆኑ ቀጣናዊ ችግሮችን ለመፍታት እና የጋራ እድገት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቻለበት ሁኔታ አለ ብሎ ለማለት አያስደፍርም**

የቀጣናው ሀገራት መሪዎች የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የፌደራሊዝም እሳቤን መሠረት ያደረገ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ እንደሚገባ ያመላክታል፤ በተለይም በሀገራችን ለሚነሱ ቀጣናዊ የጋራ ልማት እና የጋራ ተጠቃሚነት እሳቤዎች መሠረት የሚሆን ተሞክሮ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ነው፡፡

በሀገራችን ወቅታዊ የሆነው ሁሉም የቀጣናው ሀገራት ተጠቃሚ የሚሆኑበት እና በጋራ ፍላጎት መመለስ የሚችለው የወደብ ጥያቄ እና ሌሎች ቀጣናውን ለማስተሳሰር የሚችሉ እንደ የኤሌክትሪክ ኃይል፤ የመንገድ፤ የባቡር፤ የአየር እና የባሕር ትራንስፖርት፤ የሰላምና ፀጥታ ጉዳዮች፤ የመጠጥ ሆነ ለግብርና ሥራ የሚውል ውሃ፤ የአካባቢ ጥበቃ፤ የጋራ ገበያ ወዘተ. የመሳሰሉ በጋራ ቢመሩ የበለጠ አዋጭ እና ለሁሉም የመጠቀም እድል ይፈጥራሉ።

ይህንን የጋራ ተጠቃሚነት መሠረት ያደረገ እሳቤ ተግባራዊ ለማድረግ፤ ጉዳዮችን በጋራ ማስተዳደር የሚችል አካል የፌደራሊዝምን እሳቤ መሠረት በማድረግ በማቋቋም ጥንስሱን መጀመር ወይም ለጥንስሱ ኢጋድ አለ ከተባለም ኢጋድን ሙሉ በሙሉ አደረጃጀቱን እና አሠራሩን በመለወጥ ወደ ሥራ ማስገባት ይቻላል።

ይህም ለቀጣናው መጭ ዘመናት ተስፋ ያለው እና ቀጣናውን ከሚታወቅበት እና መገለጫው እየሆነ ከመጣው ግጭት፤ ስር የሰደደ ድህነት፤ ስደት ለማላቀቅ ተስፋ የሚሰንቅ ተግባርን ማከናወን ያስችላል፤ ለዚህም በቀጣናው በሁሉም ዘርፍ የሚገኙ ልሂቃን እና ኅብረተሰብ ክፍሎች ደግመው ደጋግመው ሊያስቡበት የሚገባ እውነታ ነው።

የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትም የጋራ ችግሮቹን ለመፍታት እና የቀጣናውን ሰፊ የጋራ መልማት ዕድሎች በመጠቀም በቀጣናው ተዓምራዊ ለውጥ ለመምጣት እና ለቀጣይ ትውልድ የተሻለ በጋራ ችግሮችን መፍታት እና በጋራ ማደግ የሚያስችሉ ቀጣይነት የሚኖራው መሠረቶችን ጥሎ ማለፍ የዚህ ዘመን ትውልድ ግዴታ ሁኖ ይታያል፡፡

እስከ አሁን በቀጣናው ሴራውም፤ መጠላለፉም፤ መጋጨቱም ተሞክሮ አዋጭ ሆኖ አልተገኘም፤ በግል እንደ ሀገር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከሀገር ሀገር የሚለያዩ አፈጻጸሞች ያሏቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ የሆኑ ቀጣናዊ ችግሮችን ለመፍታት እና የጋራ እድገት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተቻለበት ሁኔታ አለ ብሎ ለማለት አያስደፍርም፡፡

በመሆኑም አሁን በምንገኝበት ክፍለ ዘመን እና ነባራዊ ሁኔታዎች የፓራዳይም ለውጥ ማድረግ እና የፌደራሊዝምን እሳቤ መሠረት ያደረጉ ተግባራትን በመፈቃቀድ፤ በመተባበር እና በመከባበር ላይ ተመሥርቶ ለመሥራት የሚያስችል ሁኔታዎችን መፍጠር ግድ ይላል። ከዚያ ውጭ ያሉ አማራጮች በሙሉ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ተሞክረው የፈቱትም ችግር ሆነ ያመጡት የጋራ ልማት ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ ለዚህ ደግሞ ምስክሩ የቀጣናው ነባራዊ ሁኔታ ነው፡፡

# ተናጋሪው ዶሴ

## የጓደኝነትን የፍቅር ገመድ የበጠሰች ቅፅበት

አስመረት ብስራት

በልጅነት ፍቅር ተጫውተው ቦርቀው ነበር አብረው ያደጉት። ከጎሬቤታሞቹ ወላጆቻቸው ቅርበት የተነሳ እንደ ወንድማማች ነበር የሚተያዩት። አብረው አፈር ፈጭተው፤ ያደጉቱ ሕፃናት ከፍ ሲሉ ለእረኝነት ከብቶቻቸውን ይዘው የወጡትም አብረው ነበር።

ለእረኝነት ሜዳ ሲውሉ ልፍያቸው ጫወታቸው ሳቃቸው ሌሎችን ያስቀና ነበር። አንዱን ያለ አንዱ መመልከት እጅግ በጣም ይከብድ ነበር። የተቋጠረላቸውን ስንቅ ተካፍለው እየበሉ፤ ከብቶቻቸውን አሰማርተው በሜዳ በገደሉ ሲቦርቁ ነበር ያደጉት።

እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም በአቅራቢያቸው ወዳለው የቀለም ትምህርት ቤት አብረው ገብተው እስከ አራተኛ ክፍል ተምረዋል። ልክ አካላቸው ጠንከር ሲል ነበር ከተማ ሄደው የመስራትን ሀሳብ ያመጡት።

ይህን ሀሰባቸውን ለማሳካት የሚችሉበት እቅድ ሲያወጡና ሲተውት የሰነበቱት ታዳጊዎቹ አንድ ከተማ ቆይቶ የመጣ አብሮ አደግ የጎረቤታቸውን ልጅ ያገኙታል። እነሱም እንደሱ ከተማ ሄደው መስራት እንደሚፈልጉ ነግረውት ተስማምተው ከወላጆቻቸው ጋር ተማክረው መልስ ለመስጠት ቀን ይቃጠራሉ።

ሁለቱም በየግላቸው ወላጆቻቸውን ከተማ መሄድ እንደሚፈልጉና አብረው እየኖሩ መስራት እንደሚፈልጉ ሊያሳምኑ ታገሉ። እድሜያቸው አስራ አራት ዓመት ቢሆንም የሰውነታቸው መቀጨጭ ግን ከእድሜያቸው በታች ያስመሰላቸው ነበር።

ይህን የተመለከቱት ወላጆች ‹‹አንድ ሁለት ዓመት ቆይታችሁ እድሜያችሁ ሲጠና ትሄዳላችሁ›› ቢሏቸውም ሀሳባቸውን መቀየር እንደማይፈልጉና አይሆንም ካሏቸው ጠፍተው ወደ አዲስ አበባ እንደሚሄዱ ለወላጆቻቸው ቁርጥ ባለ አንደበት ተናገሩ።

ሀሳባቸውን ካልለወጡ ጠፍተው ከሚሄዱ ቀድሚቸው ከተማ ከገባው ከሰፈራቸው ልጅ ጋር አድርገው ያላቸውን ቋጥረው፤ ከመቀነታቸውም ላይ ያገኙትን አስጨብጠው ቸር ይመልሳችሁ ብለው መርቀው ወደ አዲስ አበባ ያሳፍሯቸዋል።

ቀድሞ ቤት ተከራይቶ ከነበረው የጎረቤታቸው ልጅ ጋር ትንሽ እረፍት ካደረጉ በኋላ ልዩ ስሙ ካራ በሬ ተራ የሚባል አካባቢ የሸክም ስራ እየፈለጉ መስራት ጀመሩ።

### ጋደኛሞቹን ያቃቃረቻቸው ገጠመኝ

በእርሱ ፍቃድ አሳዬ እና ሳሙኤል አድነው ተመስገን ከተወለዱባት ቀዬ ከወጡ ከሁለት ዓመታት በኋላ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የተጋጩት። አንድም ቀን ክፉ ደግ ሳይነጋገሩ ያገኟትን ገንዘብ ለቤተሰቦቻቸው በመላክ በሰላም ይኖሩ ነበር።

ስራ ሰርተው እህል ቢጤ አፋቸው ላይ የሚጥሉባት አንዲት ምግብ ቤት ነበረች። የምግብ ቤቷ ባለቤት ፍቅራቸውን እያዩ እንዳይለያዩ እየመከሩ የሰሩበትን ብርም እንዳያጠፉ የቀን እቁብ ይጥሉላቸው ነበር። ልጆቹም ከሞቀ ቤታቸው ከወጡ በኋላ እንደ እናት የሚንከባከባቸው ሰው በማግኘታቸው የዘውዴ ቁርስ ቤት ቋሚ ደንበኛ ሆኑ።

እንዲህ እንዲህ እያሉ ከቆዩ በኋላ ከእለታት አንድ ቀን የምግብ ቤቷ ባለቤት እማማ ዘውዴ የምትረዳቸው ሰራተኛ ያመጣሉ። ልጅቷ ከመጣች በኋላ የጓደኛሞቹ ውሎ አዳር



እዛው ቤት ውስጥ ሆነ። ልጆቹ አዲሷን ልጅ ወደዋታል። ሁለቱም የራሳቸው ለማድረግ እንቅልፍ አጥተው ያስባሉ። ማልደው ወደ ምግብ ቤቱ እየሄዱ ይመለከቷታል።

ልባቸው ልጅቷን ቢወዳትም ቃል አውጥተው አልተነጋገሩም ነበር። ሁለቱም ለመነጋገር ተፋፍረው ወራትን አሳለፉ። አንድ ቀን ግን ሳሙኤል በድፍረት ልጅቷን እንደወደዳትና የእሱ ሊያደርጋት እንደሚፈልግ ለአብሮ አደጉ በእርሱ ፈቃድ ይነግረዋል።

በእርሱ ፈቃድ ደግሞ እኔ እንደወደድኳት ስላወክ ነው፤ ልትመቀኝ ፈልገህ ነው በማለት አንድ አንድ ሲባባሉ ቆይተው ለምሳ ወደ ምግብ ቤቷ ይሄዳሉ። ከተዋወቁ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጣሉት ጓደኛሞች ተኮራርፈዋል።

ምግብ ቤቷ እንደደረሱ እማማ ዘውዴ ባለመኖራቸው ሁለቱም ልጅቷን ለማነጋገር ቆረጡ። ምሳ አዘው እየበሉ እያለ ነበር ″ በሱዬ ብላ ″ የሚል ቃል ከልጅቷ አፍ የወጣው። ይህን ግዜ ሳሙኤል ቀድሞኝ ነግሯት ይሆናል በሚል በቅናት ጨሰ። እየበላ የነበረውን ምግብ አቋርጦ ወደ ደጅ ወጣ።

ስሙ በቁልምጫ መጠራቱ የልብ ልብ የሰጠው በእርሱ ፈቃድ ግን ቁጭ ብሎ ምሳውን ከጨረሰ በኋላ በኩራት ቆመው የሚያሰራቸው ሰው የሚጠብቁበት ቦታ ሄደ።

የበእርሱ ፈቃድን መምጣት የተመለከተው ሳሙኤል ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት የጓደኛውን አንገት አንቆ ይደበድበው ጀመር። ድብድባቸውን የተመለከቱ ሰዎች መሀል ገብተው ከገላገሏቸው በኋላ የተለያዩት ጓደኛሞች የሚሸከሙት ነገር አግኝተው በየፊናቸው በረሩ።

### የእማማ ዘውዴ አዲሷ ረዳት

ባዩሽ ትባላለች። ከወሎ አማራ ሳይንት አካባቢ ነው የመጣችው። አጠር ጎረድረድ ያለች ቆንጆ ልጅ ናት። አማማ ዘውዴ ለቅሶ ለመድረስ ወደ ትውልድ ሀገራቸው በሄዱበት ወቅት ነበር የተመለከቷት። ባዩሽ ለቀስተኛውን ልታስተናግድ ተፍ ተፍ ስትል አይናቸው የገባችው እማማ ዘውዴ ″ ይችን ልጅ ወስጄ ላስተምራት″ በማለት ወላጆቻን ያስፈቅዳሉ።

ልጅቷ ገና ከማደጓ አይን የምትገባ ልጅ በመሆና የተነሳ ስጋት የገባቸው ወላጆች ልጅቷ ከሰፈሩ ጎረምሶች አይን ተርፋ ትምህርቷን መማር ከቻለች በሚል ያለ ምንም ቅሬታ ነበር የፈቀዱት። ወላጆቿ አዲስ አበባ እንድትሄድ የፈቀዱላት ወጣት ስታልመው የኖረችውን የከተማ ኑሮ ልታገኘው እንደሆነ በማሰብ በደስታ ስትፈነጥዝ ሰንብታ ከእማማ ዘውዴ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጣች።

ለቀጣይ ዓመት ትምህርት ቤት እንደምትገባ የተነገራት ባዩሽ እማማ ዘውዴን በሙሉ ልቧ ለማገልገል ቆርጣ ተነስታለች። ማልዳ ተነስታ የቁርስ ቤቷን አጸዳድታ የሚሰራውን በፍጥነት ትሰራለች። ተስተናጋጆች ሲመጡም በፈገግታ ተፍ ተፍ የምትለው ወጣት የተመጋቢውን አይን ይዛለች።

ምግብ ለመመገብ ከሚመጣው ተስተናጋጅ በተጨማሪ ልጅቷን ለመመልከት የሚመጡት ደንበኞች የእማማ ዘውዴን ቤት ሞቅ ሞቅ አድርገውታል። ይቺ የቤታቸው ድምቀት የሆነችውን የዘመዳቸውን ልጅ እንዳትበላሽባቸው በመስጋት በአይናቸው ቢከታተሏትም በእሷ ምክንያት ገበያው መድራቱን ወደውታል።

ባዩሽም ተጠቃሚው እየተንጋጋ ቤቱን ቢሞላም ከስራዋ ባሻገር ምንም አይነት የተለየ እንቅስቃሴ አታደርግም። ከደንበኞቻቸው ሁሉ ግን በተለየ አይን ሁለት የማይለያዩ ጓደኞሞችን ትቀርባቸው ነበር።

ሁለቱ ጓደኛሞች ወንድሞቿ ስለሚመስሏት ሲመጡ ልቧ በደስታ ጮቤ ይረግጥ ነበር። በዛች በተረገመች ቀንም የበእርሱ ፈቃድ ስም አፏ ገብቶ ጠራችው እንጂ ለሁለቱም አንድ አይነት ስሜት ነበር የሚሰማት።

የሳሙኤል አኩርፎ መሄድ ቢከነክናትም ከቅርበታቸው የተነሳ የከፋ ፀብ ላይ ይደርሳሉ ብላ አላሰበችም። በእለቱ እንዲያ እየተሳሳቁ የሚመገቡት ጓደኛሞች መኮራረፋቸው ቢያስጨንቃቸው ልታባብላቸው ፊታቸው መመላለሷ በእርሱ ፈቃድን መጥራቷ ነበር እንግዲህ የጠባቸው መነሻ።

### ልብ ሰባሪው ጥቃት

በሱ ፈቃድ እንዴት ይመታኛል እያለ ቢያጉረመርምም የትናንት ጓደኝነታቸውን እያሰበ ይቅርታ ሊያደርግለት እየዳዳ ነበር የተሸከመውን እቃ አድርሶ ሲመለስ እያሰላሰለ የቆየው። ሳሙኤል ግን ከሸክሙ ሲመለስ ወደ ሚያድሩበት ቤት በመሄድ ደብቆ አስቀምጦት የቆየውን ጩቤ ይዞ መጣ።

የጓደኛውን መምጣት የተመለከተው በእርሱ ፈቃድ ይቅርታ እንዲጠይቀው በማሰብ ፊቱን ዞር ያደርጋል። ወትሮም ለጥቃት ተዘጋጅቶ የመጣው ሳሙኤል ጀርባ የሰጠውን ጓደኛውን ከጀርባ በኩል በያዘው ጩቤ ይወጋዋል። ያላሰበው ጥቃት የደረሰበት በእርሱ ፈቃድ ፊቱን ወደ ጓደኛው አዞሮ ሲወድቅ ከፊት ደረቱ አካባቢ ይደግመዋል።

ያኔ ወዲያው መተንፈስ ያቃተው በእርሱ ፈቃድ ለመሞት ያጣጥር ጀመረ። ይህን የተለመለከተው ጓደኛው በድንጋጤ የሚያደርገው ጠፍቶት እግሩ ወደ መራው አቅጣጫ መሮጥ ጀመረ። ቦታው ላይ የደረሱት ሰዎችም ለእርዳታ ቢረባረቡም የወጣቱን ሕይወት ግን ማትረፍ አልቻሉም ነበር።

ተወልደው ካደጉባት ቀዬ አብረው የተሰደዱት ጓደኛሞች በማይረባ ነገር እስከ ነፍስ መጠፋፋት ደረሱ። አብረው የማደግ ሕልማቸው በዛች ቅፅበት ጠፋ። አንዱ ከዚች ዓለም በሞት ሲለይ አንደኛው ደግሞ ማረፊያው ወህኒ ሆነ።

### የፖሊስ ምርመራ

የሰውን መሰባሰብ የተመለከተው የሕግ አካል በአካቢው በፍጥነት በመገኘት ሲመለከት የሆነውን ያያል። ወንጀሉን የፈፀመው ማን እንደሆነ አጣርቶ ሲፈልግ በድንጋጤ ሮጦ መግቢያ ያጣው ሳሙኤል ወንጀሉ ከተፈፀመበት ቦታ ብዙም ሳይርቅ በሚገኘው የመድህኒዓለም ቤተክርስትያን ተቀምጦ ሲያለቅስ ያገኘዋል።

አብሮ አደጉን ለአንዲት ልጅ ሲል እንዳጠፋው ሲያስብ ፀፀት እንደ እግር እሳት እያንገበገበው የሚያነባው ወጣት በፖሊሶች ቁጥጥር ስር ሲውል እራሱን ስቶ ነበር።

በግልፍተኝነት ያደረሰው ጥቃት ሁለቱን የሚከባበሩ ጎረቤታሞች ወላጆቻቸውን ደም የሚያቃባ መሆኑን ሲያስበው ሁሉ ነገር ከአቅሙ በላይ ሆኖበት በሀዘን ተቆራምዷል።

ፖሊስ ገዳዩን ሳሙኤልን ይዞ ሟቹን በእርሱ ፈቃድን ለአስክሬን ምርመራ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊንየም የሕክምና ኮሌጅ የፎረንሲክ ሕክምናና ምርመራ ክፍል በመላክ አስክሬኑ እንዲመረመር ያደርጋል።

ፖሊስም የአይን እማኞችን ቃል፤ የገዳይን የእምነት ክህደት ቃል፤ የአስክሬን ምርመራውን ውጤት አንድ ላይ በማጠናቀር ክስ እንዲመሰርት ለአቃቤ ሕግ ይልካል።

### የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ

ከሳሽ የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ሲሆን ተከሳሽ ሳሙኤል አድነው ተመስገን እድሜ 16 አድራሻ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር ተከራይ መሆኑን በክስ አቀራረቡ ላይ ተመልክቷል።

ወንጀሉ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 540 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መተላለፍ ሲሆን ወንጀሉም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል።

የወንጀሉ ዝርዝር ተከሳሹ ሰውን ለመግደል አስቦ በቀን 1/5/13 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ሲሆን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ክልል ልዩ ቦታው ካራ በሬ ተራ አካባቢ። ሟች በሱፍቃድ አሳዬ ጋር ተጣልቶ ከተገላገሉ በኋላ ወደ ቤቱ ሄዶ ጩቤ በማምጣት በግራ በኩል ጀርባውን አንድ ጊዜ ወግቶ ጥሎታል። በመቀጠልም ደረቱ ላይ በስለት ይወጋዋል። የስለት ውጊያ ጉዳት በማድረሱ ምክንያት ሳንባው ላይ የመበሳት ጉዳት ደርሶ ደም በመፍሰሱ ምክንያት በእለቱ ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርጎታል።

ያደረገው ድርጊትም ሆን ብሎ የተፈፀመ ሲሆን አቃቤ ሕግም በፈፀመው ተራ ሰው የመግደል ወንጀል ከሶታል።

### ውሳኔ

ተከሳሽ ሳሙኤል አድነው ተመስገን በተከሰሰበት ተራ ሰው የመግደል ወንጀል በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ በ 1/2/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክስና ማስረጃውን አገናዝቦ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥቶታል። ተከሳሹ ሆን ብሎ በፈፀመው ተራ ሰው የመግደል ወንጀል በአስር ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የሕዳር በሽታ እንዳይለምድብን!

**ዋለልኝ አየለ**

በተለምዶ «የሕዳር በሽታ» እየተባለ የሚጠራ በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የተከሰተ ወረርሽኝ ነበር፡፡ ይህ የሆነው ከመቶ ምናምን ዓመታት በፊት ነው፡፡ በዘመኑ እንደ አሁኑ የረቀቀ የመመርመሪያ ቴክኖሎጂ የለም፡፡ ክስተቱ እንደ ቁጣ (መለኮታዊ ኃይል) ተደርጎ ነው የሚታየው፡፡ የሕዳር በሽታ የተባለው ደግሞ የተከሰተው በሕዳር ወር ስለሆነ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት «ሕዳር ሲታጠን» የሚባል ልማድ አለ፡፡ "ለምን በሕዳር ወር ሆነ?። የሚለውን ጥያቄ በአሁኑ ዘመን ጥናት ማወቅ እንችላለን፡፡

ሰሞኑን የጤና ተቋማትና ማሕበራት መግለጫዎችን እየሰጡ ነበር፡፡ በሰጡት ማስጠንቀቂያ እንደተገለጸው፤ የጥቅምት እና የሕዳር ወር ጉንፋን መሰል ሕመሞች ይታዩበታል፡፡ ጤና ሚኒስቴር ከሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ በመሆን በሁለት ሺህ ያህል ናሙናዎች ላይ ምርመራ አድርጎ፤ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች የጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ በሽታ መከሰቱን ይፋ አድርጓል። ለጉንፋን መሰል ክስተቶች ምክንያት የተባለውም፤ የዝናብ ወራት ማለፉን ተከትሎ በጥቅምትና ሕዳር ወቅት ላይ አብዛኛውን ጊዜ የጉንፋንና ኢንፍሉዌንዛ በሽታ የሚከሰት መሆኑ ነው፡፡ ከጥናቱ ባሻገር ሁላችንም በየአቅራቢያችን እንደምናስተውለው ሰሞኑን ብዙ ሰው የጉንፋን መሰል ሕመሞች ታማሚ ሆኗል፡፡ ይህ ክስተት በዚህ ዓመት ብቻ የተስተዋለ ሳይሆን የጥቅምትና ሕዳር ወራት ላይ በየዓመቱ የሚታይ ነው፡፡

ትዝብታችን እዚህ ላይ ነው፡፡ የጤና ሚኒስቴርና የጤና ባለሙያዎች ማሕበራት ለእንዲህ አይነት ክስተቶች «መከላከያ» ብለው ያስቀመጧቸው ነገሮች አብዛኞቹ የማንተገብራቸው ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በዓመቱ ጥቅምትና ሕዳር ወር ላይ የእንዲህ አይነት ክስተቶች ተጠቂ እንሆናለን፡፡ የወቅት መፈራረቅ በኢትዮጵያ ብቻ ያለ ክስተት አይደለም፤ ዳሩ ግን የሰለጠኑት አገራት ሰው ሰራሽ በሆነው ጥበብ ይከላከሉታል፡፡

ተፈጥሮ ነውና ክረምት ተራውን ለመኸር ወቅት ይለቃል፡፡ በዚህን ጊዜ ብዙ አበቦች ይፈነዳሉ፤ ብዙ የዕፅዋት አይነቶች ያፈራሉ፡፡ ይህ ክስተት የአየር ለውጥ ያመጣል፡፡ በክረምት ውሃ የሞሉ ወንዞች መድረቅ ይጀምራሉ፡፡ እስከ ጥቅምት መጨረሻ መቆየት የቻሉ ወንዞች ካሉ ሕዳር ላይ ይደርቃሉ። ውሃ ያጠራቀሙ ቦታዎች ሁሉ ሲደርቁ ሌላ ሽታ ይፈጠራል፡፡

እነዚህ ከላይ የተገለጹት የተፈጥሮ ክስተቶች ወደ በሽታነት የተቀየሩት በእኛ በሰዎች ጥፋት ነው፡፡ ውሃ ይዘው የነበሩ ቦታዎች ላይ ቆሻሻ እንጥላለን፤ ውሃው ሲደርቅ መጥፎ ሽታ ይፈጥራል፡፡ ውሃ በተፈጥሮ ብቻውን ሽታ የለውም።የሚረብሽ ሽታ እንዲኖረው አድርገን ያበላሸነው እኛ ሰዎች ነን፡፡ በክረምትና በመኸር ወቅት ላይ ያለውን የአየር መለዋወጥ በቴክኖሎጂ ማስተካከል ባንችል እንኳን ቢያንስ በቀላሉ ባለመበከል መከላከል እንችል ነበር፤ ዳሩ ግን እዚህ ደረጃ ላይ ባለመድረሳችን የሕዳር በሽታ በዚህ ዘመንም እየደገመን ነው፡፡

የጤና ተቋማቱ "መከላከያ፡፡ ብለው ካስቀመጧቸው ነገሮች ውስጥ ሌላው ደግሞ የግልና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ነው፡፡ ለአንደኛ እና ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ሊነገር የሚገባውን የግልና የአካባቢ ንፅህና ጉዳይ ከዲግሪ በላይ የትምህርት ደረጃ ላለው ማሕበረሰብ ማስተማር ምን ያህል ገና ብዙ እንደሚቀረን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ይህ ችግር እየተፈጠረ ያለው "የተማሩ፡፡ በሚባለው የሕብረተሰብ ክፍሎች ጭምር ነው፡፡ በትልልቅ ተቋማት ውስጥ የምናያቸው ችግሮች አሳዛኝ ናቸው። እነዚያ ተቋማት ውስጥ ያሉት ግን "የተማሩ፡፡ የሚባሉ ሰዎች ናቸው፡፡

ጉንፋን እና መሰል በሽታዎች የሚከሰቱት ከመጥፎ ሽታ ነው፡፡ እነዚህ መጥፎ ሽታዎች የሚፈጠሩት ደግሞ ካለማወቅ ሳይሆን ከከፍተኛ ቸልተኝነት ነው። አልኮል ጠጥቶ ትራንስፖርት ውስጥ የሚገባ ሰው ሊረብሽ እንደሚችል አይጠፋውም፡፡ የጫማውን ንጽህና የማይጠብቅ ሰው ጫማ መጥፎ ሽታ እንደሚፈጥር አይሳነውም፡፡ ይህ መጥፎ ሽታ ጉንፋን እና ሌሎች ተዛማጅ በሽታዎችን እንደሚያመጣ አይይጠፋውም፤ ዳሩ ግን እነዚህ ሁሉ የሚሆኑት በከፍተኛ ቸልተኝነት ነው፡፡

ምንም እንኳን የወንዞች ዳርቻ ፕሮጀክቶች አዲስ አበባን ውብ እና ጽዱ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ላይ ቢሆኑም፤ ዳሩ ግን ዋናው ለውጥ መምጣት ያለበት የሰዎች ጭንቅላት ላይ ነው፡፡ አሁንም ድረስ ብዙ የወንዝ ዳርቻዎች አፍንጫ ተይዞ የሚታለፉ ናቸው። ራስ የሚያዞር መጥፎ ሽታ ያላቸው ናቸው፡፡ ያ መጥፎ ሽታ የተፈጠረው በክረምቱ ወቅት የወረደው ዝናብ ቆሻሻ ሆኖ ሳይሆን እኛ ሰዎች በክለነው ነው። በተጠራቀመው የዝናብ ውሃ ላይ ሌላ ባዕድ ነገር ቀላቅለንበት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ደረቅም ሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ የሚጥሉት ወንዝ መሰል ነገር ውስጥ ነው፡፡

የግዴለሽነታችን ነገር በጣም አሳሳቢ ነው። እንኳን እንዲህ ክረምትና መኸር የሚቀያየርበት ወቅት በሙሉው ክረምት ወይም የበጋ ወቅት ራሱ አስቸጋሪ ነው፡፡ በአንፃራዊነት ሙሉ ክረምት ሳይሻል አይቀርም፡፡ በእንዲህ አይነቱ ወቅት ብዙ መጥፎ ሽታዎች አሉ፡፡ በተፈጥሮ የተጠራቀመው እንዳለ ሆኖ፤ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ደግሞ ችግሩን ያባብሱታል። ከእነዚህም አንዱ በየሰፈሩ የሚሰበሰብ ቆሻሻ ነው፡፡

በብዙ አካባቢዎች እንዳስተዋልኩት በሳምንቱ ውስጥ የተወሰኑ ቀናት (ለምሳሌ እሁድ፣ ረቡዕ እና ዓርብ) በየአካባቢው ያሉ የተሰበሰቡ ቆሻሻዎች የሚነሱበት ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ቀናት የማንሻ መሆናቸውን የየአካባቢው ነዋሪ ያውቃል፡፡ ይሄ ብቻ አይደለም፤ በዕለቱ የሚያነሱ ሰዎች ሲመጡ በጡሩንባ «ቆሻሻ አውጡ!» እየተባለ በከፍተኛ ጩኸት ይነገራል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ቀን እየተበሳጨሁ «አንዴ ከተነገረ አይበቃም እንዴ!?» ብየ በውስጤ እገረማለሁ፡፡ ለካ ወደው አይደለም፡፡

አሳዛኙ ነገር ያ ሁሉ ጩኸት ተጮሆ ቆሻሻ የማያወጡ ሰዎች አሉ፡፡ ልክ አንሺዎች አንስተው ሲሄዱ ከየት እንደመጡ ሳይታወቅ ቆሻሻ ጥለው ይሄዳሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች እንግዲህ ሊቀጡ ይገባ ነበር፡፡ ሲጀመር የቆሻሻ ማንሻ ቀናትን ማወቅ ነበረባቸው። እሱም ይረሳል እንበል፤ ለማስታወስ ተብሎ ያን ያህል አካባቢው እስከሚናጋ ድረስ ቅስቀሳ ሲደረግ ማውጣት ነበረባቸው፡፡ እሱንም ሳይሰሙ ቀሩ እንበል፤ ቢያንስ ምናለ በሚቀጥለው ቀን የሚያነሱት ሲመጡ ቢያወጡት? እንዲያው ምናልባት ሆን ብለው ይሆን?

በሱፍ እና ከረቫት ዝንጥ ብሎ የለበሰ ሰው ያለምንም መሸማቀቅ መንገድ ዳር የተጠቀመበትን ሶፍት ይጥላል፡፡ ይሄ ለዚያውም ቀላሉ ነው፤ ከዋናው አስፋልት ገለል ብሎ ሽንቱን የሚሸናው ማንም ሰው የሚታዘበው ነው፡፡ የግንብ ጥግ ሆኖ መጥፎ ሽታ የሌለው ላይገኝ ነው ማለት ነው፡፡ የውሃ ማፋሰሻዎች ሽንትን ጭምር ነው የሚያፈሱት ማለት ነው፡፡

ታዲያ በዚህ ሁኔታ በሕዳር ብቻ ሳይሆን ዓመቱን ሙሉ ጉንፋን ቢይዘን ምን ይገርማል? እንዴት በሽታ እንኳን አያስተምረንም? የሕዳር በሽታ እንዳይለምድብን አሁንም ቀልብ እንግዛ!

# ዓለም አቀፍ

## ኬንያውያን መታወቂያ ለማውጣት እንዲከፍሉ መንግሥት ያወጣውን ትዕዛዝ ፍርድ ቤት አገደ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኬንያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ለማውጣት ዜጎች ክፍያ እንዲፈጽሙ መንግሥት ያወጣውን መመሪያ አገደ።

ማጋሬ ጊኬንይ የተባሉ ሐኪም መንግሥት አዲሱን መመሪያ ያወጣው "ድንገተኛ እና ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ" ነው ሲሉ የሕዝብ ድምፅ በማሰባሰብ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት የወሰዱት።


የተሰበሰበው የሕዝብ ድምፅ እንደሚለው በአዲሱ መመሪያ መሠረት "በርካታ ዜጎች መታወቂያ ካርድ በቀላሉ ማግኘት አይችሉም።"

ከዚህ ቀደም በነፃ ይሰጥ የነበረው ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ አሁን 1 ሺህ ሺልንግ (370 ብር ገደማ) እንዲሆን መንግሥት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አዟል። መታወቂያ ለማሳደስ ደግሞ ኬንያዊያን 2 ሺህ ሺልንግ እንዲከፍሉ ተጠይቀዋል።

ኬንያውያን እያሻቀበ ባለው የኑሮ ግሽበት ምሬታቸውን እየገለጡ ባሉበት ወቅት ነው መንግሥት ገቢውን ለማሳደግ ሲል ዜጎች ከዚህ ቀደም በነፃ የሚያገኟቸውን አገልግሎቶች በበለጠ ክፍያ እንዲሆን ያደረገው።

አዲሱ መመሪያ መታወቂያ ካርድ ብቻ ሳይሆን ፓስፖርት፣ የጋብቻ ወረቀት፣ የሥራ እና የመኖሪያ ፈቃድ እንዲሁም የልደት እና ሞት ምስክር ወረቀት ለማውጣትም ክፍያ ይጠይቃል።

አዲስ ፓስፖርት ለማውጣት አሊያም ለማሳደስ ይጠየቅ የነበረው ክፍያ 50 በመቶ ሲያድግ የልደት እና ሞት ወረቀት ለማውጣት የሚጠየቅ ክፍያ በአራት እጥፍ አድጎ 200 ሺልንግ ገብቷል።




በድንገት የተጫኑት የክፍያ መመሪያዎች አቅም የሌላቸው ዜጎች የመንግሥትን ግልጋሎት ተጠቅመው አስፈላጊ ወረቀት ለማግኘት ሊቸገሩ ይችላሉ የሚል ስጋት ጭሯል።

"ቀልዱን እንተወውና ለመታወቂያ ካርድ ክፍያ መጠየቁ የተወሰኑ ሰዎች አቅም ስለሌላቸው ለምርጫ መመዝገብ አይችሉም ማለት ነው። ይህ ደግሞ የመምረጥ መብታቸው ተነፈገ ማለት ነው" ሲል አንድ ግለሰብ ኤክስ ላይ አስተያየቱን አስፍሯል።

አንዳንድ ፖለቲከኞች አዲሱን መመሪያ ሲቃወሙ የተወሰኑ የመንግሥት ባለሥልጣናት ደግሞ በመመሪያው እንደማይስማሙ ገልጠዋል።

የሀገሪቷ ዳያስፖራ ጉዳዮች ክፍል ኃላፊ የሆኑት ሮዜሊን ንጆጉ ከኬንያውያን ለሚወለዱ ሕፃናት ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ለመስጠት የወጣው የክፍያ መመሪያ "በስህተት የገባ ነው" ይስተካከላል ብለዋል።

ፕሬዚደንት ሩቶ እስካሁን ስለ ዋጋው ጭማሪ ያሉት ነገር ባይኖርም ሐሙስ ዕለት ለሀገሪቱ ዜጎች ባስተላለፉት መልዕክት ኬንያውያንን ከዕዳ ጫና ለማላቀቅ "ቀላል ያልሆኑ ግን አስፈላጊ" ውሳኔዎችን ለመውሰድ ተገድጃለሁ ብለዋል።

## በሱዳን ጦርነት በተለያዩ ከተሞች አስከፊ ችግር እየተፈጠረ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በሱዳን ጦርነት አሁንም በተለያዩ ከተሞች አስከፊ ቀውስ እየተፈጠረ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

በሱዳን ዋና ከተማ ካርቱም እና በአገሪቱ ምዕራባዊ ክልል ዳርፉር ውስጥ ከባድ ውጊያ እየተካሄደ መሆኑን እና በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል።

በሱዳን ጦር ሠራዊት እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መካከል አዲስ በተቀሰቀሰው እና ሰሞኑን በተባባሰው ውጊያ ምክንያት በኦምዱርማን ከተማ ጎዳናዎች ላይ አስከሬኖች ወድቀው እንደሚገኙ የዐይን እማኞች ለፈረንሳይ ዜና ወኪል ኤኤፍፒ ተናግረዋል።

"ያለፈው ሐሙስ ዕለት ከተካሄደው ውጊያ በኋላ ወታደራዊ የደንብ ልብስ የለበሱ ሰዎች አስከሬኖች በከተማዋ ማዕከላዊ ክፍል በሚገኙ ጎዳናዎች ላይ ወድቀው ይገኛሉ" በማለት አንድ የዐይን እማኝ ተናግሯል።

በሱዳን ምዕራባዊ ክፍል በምዕራብ ዳርፉር ግዛት ውስጥ ደግሞ በተካሄዱ ግጭቶች 700 የሚደርሱ ሰዎች መገደላቸውን ዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (አይኦኤም) መግለጹን ድርጅቱ ያወጣውን መግለጫ በመጥቀስ ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቧል።

መግለጫው ጨምሮም የምዕራብ ዳርፉር ግዛት ዋና ከተማ በሆነችው ኤል ጄኒና ውስጥ ከ300 በላይ የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ ውጊያውን ተከትሎ የደረሱበት አለመታወቁን ገልጿል።



በካርቱም የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲም የዐይን እማኞችን መረጃ መሠረት አድርጎ "የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች እና በእነሱ የሚደገፉ ሚሊሻዎች በሚፈጽሙት ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መረበሹን" አሳውቋል።

ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ "የጎሳ ግጭት" ብሎ በገለጸው ጥቃት ውስጥ ኃይሎቹ እንዳልተሳተፉ በመግለጽ የቀረበበትን ክስ አስተባብሏል።

በአገሪቱ ምዕራባዊ ክፍል ውስጥ እየተባባሰ ያለውን ግጭት በመሸሽ ባለፉት ጥቂት ቀናት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የሱዳንን ድንበር በመሻገር ወደ ጎረቤት ቻድና ኢትዮጵያ ተሰደዋል።

ከተቀሰቀሰ ወራትን ባስቆጠረው በሱዳን እየተካሄደ ባለው ጦርነት እስካሁን ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ቀያቸውን ለቀው ለመሰደድ መገደዳቸው ተዘግቧል።


ባለፉት ወራት ጦርነት በማቆም ከስምምነት እንዲደረስ አሜሪካ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ ድርጅት እንዲሁም የአካባቢው አገራት ለማሸማገል ጥረት ቢያደርጉም እስካሁን አልተሳካላቸውም።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# የምናባዊ ዕይታ ኃይል

አስናቀ ፀጋዬ




የሰው ልጅ ወደዚች ምድር ከመጣ ወዲህ እያንዳንዱን ነገር መተግበር የሚጀምረው ከሃሳብ ነው፡፡ ሀሳብ ዘር ነው፡፡ የተዘራ ዘር ደግሞ ይበቅላል፡፡ የዘራነው ዘር የስንዴ ከሆነ ስንዴ ይበቅላል፡፡ የዘራነው ዘር ማሽላ ከሆነ ማሽላ ይበቅላል . . . ወዘተ፡፡ መቼም ስንዴ ዘርተን ማሽላ ልንጠብቅ አንችልም፡፡ የሰው ልጅ ሀሳብም እንደዛ ነው፡፡ለምሳሌ የአንድ ገበሬ ማሳ በሚገባ ታርሶ ከተዘጋጀ በኋላ ጤፍ ቢዘራበት ጥሩ የጤፍ ምርት ይሰጣል፡፡ ማሽላም ከተዘራበት ጥሩ የማሽላ ምርት ይሰጣል፡፡ ይህ ምሳሌ ታዲያ እንዴት ከእኛ ሕይወት ጋር ሊያያዝ ይችላል?

ማሳው ወይም የእርሻው ቦታ የኛ አእምሮ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር ይቻላል፡፡በማሳው ላይ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ጤፍና ሌሎችንም ዘሮችን እንደምንዘራ ሁሉ በአእምሯችን ላይ የምንዘራው ሀሳብ ነው፡፡ በአእምሯችን የምንዘራው ሀሳብ ታዲያ በጎም መጥፎም ሊሆን ይችላል፡፡በአእምሯችን ላይ በጎ ነገሮችን እስከዘራን ድረስ የምናጭደው በጎ በጎውን ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በአእምሯችን ላይ የምንዘራው መጥፎ ነገር እስከሆነ ድረስ የምናበቅለው ጥሩ ያልሆነውን ነገር ነው፡፡ ስለዚህ የእኛ መልካም ማንነት ሊመጣ የሚችለው በአእምሯችን ላይ በጎ ነገሮችን በዘራን ቁጥር ነው፡፡ መልካም ነገሮችን በአእምሯችን ውስጥ ባስገባን ቁጥር ውጤቱ መልካም ይሆናል፡፡

አንድ ዘር ተዘርቶ አንድ ዘር አይሰጥም፡፡በእጥፍ ተራብቶ ነው ዘር የሚሰጠው፡፡ ለምሳሌ አንድ ዘር እንክርዳድ በማሳ ውስጥ ቢዘራ ሙሉ ማሳውን በእጥፍ ያዳርሳል፡፡ በተመሳሳይ መጥፎ ነገርም በአእምሮ ውስጥ እስከተዘራ ድረስ መጥፎ ነገሮች ተመልሰው በአእምሮ ውስጥ በእጥፍ ይራባሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ መልካም ነገር በአእምሮ ውስጥ ሲዘራ በእጥፍ መልካም ነገሮችን ያባዛል፡፡

ይህም አንድ ሰው አላስፈላጊና መጥፎ ሀሳቦችን ወደ አእምሮው ማስገባት የለበትም ማለት ነው፡፡ ስለውድቀቱ፣ ስለ ድክመቱ፣ ከሰዎች ጋር መግባባትና አብሮም መስራት ስላለመቻሉና ሌሎች አሉታዊ ሃሳቦችን፤ ወይም፣ የሰውን አእምሮ የሚገሉ ሃሳቦችን ወደ አእምሮው ማስገባት የለበትም፡፡እነዚህ የማይጠቅሙ ሀሳቦች በአእምሮ ላይ እስከተዘሩ ድረስ መብቀላቸው አይቀርም፡፡ያን ግዜ በዛ አሉታዊ ሃሳብ ውስጥ ሆነን እንገኛለን፡፡

በልጅነት፣ በወጣትነት ወይም ደግሞ አሁን ባለንበት የእድሜ ዘመን በሕይወታችን እየገጠመን ያለው ነገር በርግጥ የምንፈልገውን አይነት ሕይወት ነው እየኖርን ያለነው? ‹‹እኔ እንዲህ አይነት ሕይወት መኖር እፈልጋለሁ›› ብለን ያሰብነውን ሕይወት ነው እየኖርን ያለነው? ወይስ ከዚህ ወጣ ያለና ያልሆነ ሕይወት ውስጥ ነው እየኖርን ያለነው፡፡ ገንዘብ ፈልገን የገንዘብ እጦት ይገጥመናል፡፡ ለምን? አእምሯችን የሚያስበው ስለገንዘብ ማጣት እንጂ ስለማግኘት ባለመሆኑ ነው፡፡

በነገራችን ላይ ይህች ዓለም በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሃብት የተትረፈረፈች ናት፡፡ በሀብት ውስንነት የተገደበች አይደለችም፡፡ ፈጣሪም ቢሆን ይህችን ዓለም ውስን አድርጎ አይደለም የፈጠራት። ሁሉንም ነገር አትረፍርፎ ነው በዚህች ምድር የፈጠረው፡፡ “መትረፍረፍ፡፡ ማለት ደግሞ አንድ ፍሬ የስንዴ ዘር ዘርቶ በእጥፍ አራብቶ እንደመሰብሰብ ነው፡፡ነገር ግን ውስን እንድንሆን የሚያደርገንና ለራሳችን ገደብ የምናበጀው እኛው ራሳችን ነን። እንዲህ እንድንሆን ሊያደርገን የሚችለው የተማርነው መደበኛና የሕይወት ልምድ ትምህርት፣ አብረን የምንውላቸው ሰዎች ወይም ጓደኞቻችን፣ ቤተሰቦቻችንና ዘመዶቻችን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እነዚህ የእኛን አእምሮ የማሰብ ፍላጎት ይገድቡታል፡፡ ስለሆነም በምንፈልገው ነገር ላይ ማተኮር አለብን፡፡ሁሉም ድርጊትና መሻት የሚመነጨው ከሃሳብ ነው፡፡ሀሳብ ወደ ቃል ይቀየራል፡፡ቃልም ድርጊት ወይም ተግባር ይሆናል።ለምሳሌ አንድ በጣም የምትወዱትና የምታከብሩት ሰው ቢሰድባችሁና ቢያመነጫችቃችሁ ለመጀመሪያ ጊዜ በትዕግስት ታልፉታላችሁ፡፡ በሌላ ግዜም ያ የምትወዱትና የምታከብሩት ሰው በቀልድ ወይም በሌላ መንገድ ለሁለተኛ ጊዜ ቢያመናጭቃችሁ፤ አልያም ቢሰድባችሁ ዝምታችሁ ወደ ቃል ያድጋል፡፡ ትእግስታችሁ ወደ ማጥቃት ይሸጋገራል፡፡

በመጀመሪያ ያ የምንወደው ሰው እንዲያ ሲሰድበንና ሲያመናጭቀን ‹‹ምን አስቦ ነው እንዲህ የሚሰድበኝ፤ የሚያመናጭቀኝ?›› ብለን እራሳችንን እንጠይቃለን። ከራሳችን ጋር እናወራለን፡፡ይህን ስናብሰለስለው የቆየነውን ሃሳብ ድጋሚ ሲሰድበንና ሲያመናጭቀን ወደ ቃል ለውጠነው አንድ ነገር እንለዋለን፡፡ ማለትም ሃሳባችን ወደ ቃል፤ ወይም ወደ ማውራት ይቀየራል ማለት ነው፡፡መልስ ወደ መስጠት እንሸጋገራለን፡፡መልሳችን ‹‹አንተ ስርዓት ይኑርህ፣ ምን ሆነህ ነው የምትሳደበው፣ እገልሃለሁ ....››ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

እዚህ ጋር ሰዎች እንዲህ ሲባሉ ከሃሳባቸው በኋላ የሚወስዱት እርምጃ ቃል አውጥቶ ለዚያ ስድብና ማመናጨቅ ምላሽ መስጠት ነው፡፡ምላሹ ግን እንደየሰው ባህሪና የማስተዋል ደረጃ ይወሰናል። ዞሮ ዞሮ ግን ሰዎች እንዲህ ሲባሉ በጣም ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኞቹ የቃላት ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ይህ የቃላት ምላሽ ካደገና ከዛኛው ሰው በኩል ከተደጋገመ ወደ ድርጊት ተሸጋግሮ ወደ ፀብ ሊያመራ ይችላል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ጉዳዩ ከሮ እስከ ሕይወት መጠፋፋት ሊያደርስ ይችላል፡፡እናንተም በሕይወታችሁ ውስጥ በአእምሯችሁ የምታመላልሱት ጉዳይ ሁሉ የዚሁ ምሳሌ ነፀብራቅ ነው፡፡

ስለዚህ በአእምሯችሁ በየእለቱ የምታመላልሱት ጉዳይ ፍቅር ነው?፣ ስኬት ነው?፣ ለውጥ ነው?፣ አንድነት ነው?፣ በእምነት ስለመጠንከር ነው?፤ ወይስ ስለውድቀት ነው? መልሱ እናንተ ጋር ነው ያለው። እንደውም ጥናቶች የሚያሳዩት በየሰከንዱ ከአስራ አንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሀሳቦች በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ እንደሚመላለሱ ነው፡፡ይህ በደቂቃ፣ በሰዓት፣ በቀንና በወር ሲታሰብ ደግሞ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

ስለዚህ በሕይወታችን ምን ላይ ማተኮር እንዳለብን፣ ፍላጎታችን ምን እንደሆነና የት መድረስ እንደምንፈልግ ለይተን ማወቅ ይኖርብናል። እቅዳችንን፣ ግባችንንና ራእያችንን ማወቅ ግዴታችን ነው፡፡ ምን አይነት ሕይወት መኖር እንደምንፈልግ ማወቅ አለብን፡፡ የራስህ ቤት፣ ሃብት፣ ድርጅትና ሌሎችም እንዲኖሩህ ትፈልጋለህ? ስለዚህ የምትፈልጋቸውን ነገሮች ከአእምሮህ ውስጥ አውጥተህ በወረቀት ላይ ፃፋቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በቅድሚያ እቅድ አውጣ፡፡ እቅድህ አጭር፣ መካከለኛና የረጅም ግዜ ሊሆን ይችላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ያወጣኸውን እቅድ በመልካም ጎኑ አድርገው ወይም ጀምረው፡፡ በርግጥ ሁሌም ቢሆን መጥፎ ሃሳቦች ወደ አእምሯችን በተደጋጋሚ ይመላለሳሉ፡፡ ሆኖም ግን መፅናት ያለብን መልካሙ ሀሳብ ላይ ነው፡፡ የምትፈልገው ውጤት ባይመጣም እንኳን ውጤት እንደሚመጣ በውስጥህ መሳል አለብህ፡፡ ለምሳሌ “ምን አይነት ቤት ውስጥ መኖር ትፈልጋለህ?፡፡ ተብለህ ብትጠየቅ ምን አይነት ቤት ውስጥ ነው መኖር የምትፈልገው? ብዙ አይነት ቤት አለ፡፡ ምርጫው ያንተ ነው፡፡ ነግር ግን መኖር የምትፈልግበትን ቤት በምናብህ ሳለው፡፡ቤቱ ያንተ እንደሆነ እመን፡፡ በውስጡ እየኖርክበት እንደሆነ አስብ፡፡

ሀሳብህን እውን ለማድረግና በምትፈልገው ቤት ውስጥ ለመኖር ታዲያ ካንተ በኩል ቁርጠኝነት፣ ፅናትና ዘለቄታዊነት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ እንደተሰጠህና እንዳገኘኸው አድርገህ ምኞትህን እውን ለማድረግ ትጋ፡፡ ለዚህም እምነት ሊኖርህ ይገባል፡፡በአእምሮህ ውስጥ የተፀነሰው ሃሳብ ነው ወደ ቃልና ድርጊት ተቀይሮ እውን የሚሆነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቢሊየነር የሆኑና በሀብትም ሆነ በዝና የናኙ ሰዎች ዛሬ ያሉበት ደረጃ ላይ የደረሱት ስለተማሩ ብቻ ሳይሆን ያሰቡትን ሃሳብ እውን በማድረጋቸው ነው፡፡ስለዚህ አንተም ብትሆን ጭንቅላትህን አሰራው፤ በአእምሮህ ውስጥ የሚመላለሰውን ሀሳብ አውጣውና እውን አድርገው።

ስለምንፈልገው ነገር በማሰብና በማሰላሰል በሕይወታችን ላይ ለውጥ ማምጣት ከፈለገን የምንፈልገው ነገር ላይ ሙሉ ትኩረታችንን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ እዚህ ጋር አይምሯችን ሁለት ክፍል እንዳለው ልብ ልንል ይገባል፡፡ የመጀመሪያው ኮንሺየስ ወይም ንቁው የአእምሮ ክፍል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሱብኮንሺየስ ወይም ድብቁ የአእምሮ ክፍላችን ነው፡፡ንቁው የአእምሮ ክፍላችን እያንዳንዱን ስራ የምንሰራበት ሲሆን፣ ድብቁ የአእምሮ ክፍል ግን ብዙም ጥቅም የሚሰጥ የማይመስለው፤ ነገር ግን ከተሰራበት አስገራሚ ውጤቶችን የሚያሳይ የአእምሮ ክፍል ነው፡፡

ስለዚህ በሕይወታችን ለውጥ ለማምጣት ፍላጎታችን ላይ ማተኮር ይገባል፡፡ የምንፈልገው ነገር እውን ሆኖ ከማየታችን በፊት በምናብ መሳል ትልቁ የስኬት ሚስጥር እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ይህ ነው ወደ እምንፈልገው ስኬት የሚንደረድረን። ይህ ነው በህይወታችን ለውጥ ማምጣት የሚያስችለን። ስለዚህ ፍላጎት ላይ በማተኮር የምንፈልገውን ነገር አውን ለማድረግ ነገሩን በምናብ በመሳል በአእምሯችን ውስጥ በተደጋጋሚ ማመላለስ ያስፈልጋል፡፡ ሕልማችን እውን እንዲሆን ማመን ያስፈልጋል፡፡ ይህ ማለት የምንፈልገው ነገር እንደሆነልን አስበን በምናባችን ወይም በሕሊናችን ማየት ነው፡፡

በአንደበታችን ደግሞ ያሰብነው ነገር እውን እንደሆነ አስበን ማመስገን ያስፈልጋል፡፡ ያሰብነው ነገር ባይሳካ እንኳን ቢያንስ በምናባችን አይተነዋል። ስለዚህ ሌላ ጊዜ እውን መሆኑ አይቀርምና የምንፈልገውን ነገር በአእምሯችን ውስጥ መሳልና ደግሞ ደጋግሞ የማመላለስ ጥረታችንን አጠናክረን መቀጠል ያስፈልገናል። ለምሳሌ አንድ ሰው የሆነ ነገር ሲያድረግላችሁ ታመሰግኑታላችሁ፡፡ ባያደርግላችሁም ቢያንስ ለጥረቱ ስትሉ ታመሰግኑታላቸው፡፡ልክ እንደዛው ሁሉ በአይምሯችሁ ስታመላልሱት የነበረው የሃሳብ ፍላጎት እውን ሳይሆን ቢቀር ማመስገን እንጂ ተስፋ መቁረጥ የለባችሁም፡፡ ምክንያቱም ሀሳብ መቋጫ የለውምና ዳግም በአእምሯችሁ ሌላ የፍላጎት ሃሳብ እንዲመላለስ በማድረግ ሃሳባችሁን እውን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

ስለዚህ ስሜታችሁን በምትፈልጉት ነገር ላይ ማቆየት ይኖርባችኋል፡፡ ውጤታማ እንደምትሆኑ፣ የምትፈልጉት ቦታ ላይ እንደምትደርሱ አምኖና ይህ እንደተሳካ አስቦ መስራት ያስፈልጋል፡፡መስራትና መተግበር ያለብንን ነገሮች ማድረግ፤ ሁሌም በጎ በጎ ነገሮችን ማሰብና መመኘት፤ ብሎም፣ ይህን ለአእምሮ መንገር፣ ለሰዎችም ማካፈል፣ የመስጠትና መቀበል ሕግን በደምብ መተግበር ከምናብ ዕይታ ወደ እውናዊ ክስተት የሚያንደረድሩ ቁልፍ የሕይወት መርሆች ናቸው፡፡

## ከአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# በአንድ እቅድና አንድ ሪፖርት አፈፃፀም የተገኙ ውጤቶች

በሀገር ደረጃ የሚሠሩ የልማት ሥራዎች መንግሥት በሚያቅዳቸው የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እቅዶች ላይ ተመሥርቶ የሚፈጸም ነው፡፡ የከተማችን አስተዳደር ከፌዴራል መንግሥት ፖሊሲዎችና እቅዶች ጋር የሚጣጣምና የከተማውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብቶ ከከተማ እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ወጥነት ያለው የእቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት ሥርዓት እየተከተለ ይገኛል። ይህ የተሻለና ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓትና የተቋም አቅም ግንባታ አካልም አንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት ነው።

በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ላሉት ሁሉም የመንግሥት ተቋማት ለኅብረተሰቡ ጥቅም ተብሎ የሚዘጋጁ የልማት እቅድና ሪፖርቶች ወጥነትና ጥራት ባለው መልኩ በተመሳሳይ የእቅድና ሪፖርት ቢጋር(ስታንዳርድ) ይዘት በመጠቀም ዘመናዊ የመረጃ ቅብብሎሽ የሚደረግበት የአሠራር ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ሂደት የተቋማት የእቅድ አዘገጃጀትና የሪፖርት አቀራረብ ተመሳሳይና ወጥ እንዲሆን ይጠበቃል። በመሆኑም አንድ እቅድ አንድ ሪፖርት አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስለተቋሙ የልማት እቅድና ሪፖርት ለተለያዩ አካላት ማለትም(ለምክር ቤት፣ ለከተማ አስተዳደር እንዲሁም ለፌደራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት) ወጥ የሆነ የልማት እቅዱንም ሆነ ሪፖርት አዘጋጅቶ ሲልክ ለሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ተመሳሳይ፣ ወጥ የሆነና እርስ በርሱ የማይጣረስ መረጃ መስጠት ማለት እንደሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ኮሚሽን የከተማ ማኅበራዊ ኢኮኖሚ ልማት ፕላን ዝግጅት አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ ይገልጻሉ፡፡



አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ

አቶ ቴዎድሮስ አያይዘውም፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የልማት ሥራዎቻቸውን እቅድና ሪፖርት በተለያየ አካላት ሲጠየቁ ለሁሉም አካላት አንድ አይነት የእቅድና የሪፖርት ቢጋር በመጠቀም ተመሳሳይ መረጃ መስጠት ሲገባቸው የተለያየ ቢጋር በመጠቀም የተለያየ መረጃ እየሰጡ ስለሆነና የሪፖርት ድግግሞሽ እና በአንድ ሥራ ላይ የተለያየ ሪፖርት እንዲቀርብ በማድረጉ፣ የመረጃ ቅብብሎሹ ያላግባብ የመንግሥት ሀብት እና ጉልበት ብክነትን በማስከተሉ፣ ጥራት ያለውና ተዓማኒ የሆነ እንዲሁም ጊዜ እና ሀብት ቆጣቢ የሆነ የእቅድና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ እንደተገኘ ይናገራሉ።

የአንድ እቅድ የአንድ ሪፖርት ዓላማ በተቋማት የሚሠሩ ተግባራት ድግግሞሽ እና የተሳሳተ የመረጃ ቅብብሎሽ ማስቀረት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥራት፣ ተዓማኒነት ያለው እንዲሁም ጊዜ፣ ሀብትና ጉልበት ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ፈጣን የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት፣ ለጠንካራ ክትትል፣ ቁጥጥርና፣ ምዘና አመቺ በመሆን የተጠያቂነት አሠራር በማስፈን፣ ተቋማት አቅደው የሚያከናውኗቸው ተግባራት በአንድ ወጥ እቅድና አንድ ሪፖርት ተጠቃለው ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

እስከአሁን ባለው የተቋማት እቅድና የሪፖርት ቅብብሎሽ ሂደት ላይ የሚስተዋለው ውስንነት መኖር፣ ከረጅም ዘመን መሪ ፕላን ያልተቀዳና ያልተናበበ፣ በዋና ዋና የተቋሙ ስትራቴጂክ ግቦች ላይ ያላተኮረ የእቅድ ዝግጅት ክፍተት የታየ ሲሆን፣ የአፈፃጸም ሪፖርቱ ደግሞ አልፎ አልፎ ሂደት የበዛበትና በስታንዳርድ ቢጋር የማዘጋጀት ከታዩ ክፍተቶች መካከል እንደነበሩ ምክትል ኮሚሽነሩ ይናገራሉ፡፡

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ገለፃ፣ አሁን ላይ አንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት አሠራር ተግባራዊ መደረጉ የሚመነጩ መረጃዎችን ክፍተት ለመሙላት ይጠቅማል፡ ወጥና ተዓማኒነት ያለው ወቅታዊ ሪፖርት (መረጃ) ለማግኘት ያስችላል፣ ለኅብረተሰቡ ጠቀሜታ የሚውል ትክክለኛ ውሳኔና እርምጃ እንዲወሰድ ያግዛል፣ በተቋማት መካከል የሚፈጠረውን የሥራ ድግግሞሽ ያስቀራል፡ የመንግሥት ሀብትና የጉልበት ብክነትን ያስቀራል፡ ለእቅድ አፈጻጸም ተቆጣጣሪ አካላትም ይሁን ለሌላ አካላት ተዘጋጅቶ የሚላክ እቅድና ሪፖርት በዋናነት የተቋማትን ያለእቅድ የመሥራት ክፍተት ይቀርፋል፡፡ ሥራዎችን ከጅምር እስከ ውጤት ድረስ ለማስኬድ ያመቻል፡፡

አሠራሩ በመተግበሩ ቀደም ሲል በተቋማት መካከል የነበረውን የሥራ ድግግሞሽ ከማስቀረቱም ባሻገር የሚዘጋጀው እቅድና ሪፖርት ወጥና በተሟላ መልኩ የተቋሙን መረጃዎች ያጠቃለለና እቅዱና ሪፖርቱ ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾችን Key Performance Indicators (KPI) ያካተተ ተደርጎ የሚለካ መሆኑ፣ እቅድ እና ሪፖርቱ በትክክል ተቋሙ የሚሠራቸውን ተግባራት በግልፅ ያመላከተ እንዲሆን አስችሎታል፡፡ ይህንን ሁኔታ ለማጠናከር የሚያስችሉ የእቅድ አፈጻጸም ድጋፍና ክትትል ሥራዎች ተጠናከረው እየተከናወኑ ሲሆኑ ከማዕከል እስከ ወረዳ የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በእቅድ ዝግጅት፣ በአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ እንዲሁም በKPI ዝግጅትና የምዘና አሠራሮች ላይ በስፋት ሥልጠናዎች እየተሰጡ ነው ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በተጨማሪም ይህ አሠራር ማኅበረሰቡ ወደ የትኛውም የከተማ አስተዳደሩ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ሲሄድ የሚፈልገውን መረጃ ለማግኘት እንደሚጠቅመው የሚገልፁት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ በከተማ ደረጃ ተግባራዊ የተደረጉ ሥራዎች በትክክል ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ ስለመሆኑ ከማረጋገጥ ባሻገር ክፍተት ካለ ተጠያቂ ለማድረግም ያስችላል ይላሉ፡፡

ይህ የአሠራር ሥርዓት እንደከተማ በሁሉም ተቋማት ተቀባይነት አግኝቶ ውጤት እያመጣ ያለና እየባከነ የነበረውን የመንግሥት ሀብትና ጉልበት ችግር እየፈታ ያለ ነው የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ፣ ኮሚሽኑ በአንድ ማዕከል ስር በተቀናጀ ሁኔታ መሥሪያ ቤቶችን ለመከታተል፣ በክፍተቶች ላይ ግብረ-መልስ ሰጥቶ ለማስተካከል መሰረታዊ ውስንነት ነበረበት። ስለዚህ አንድ እቅድ አንድ ሪፖርት አሠራር ለሁሉም መሥሪያ ቤቶች ተግባራዊ መደረጉ ወጥነት ያለው መረጃ ተደራሽ ለማድረግ አስችሏል ሲሉ ያስረዳሉ።

ኮሚሽኑ ከፌዴራል ፕላንና ልማት ሚኒስቴር ጋር በትብብር አንድ እቅድ አንድ ሪፖርት አሠራርን ተግባራዊ እያደረገ ነው፡፡ በአንድ እቅድ አንድ ሪፖርት መነሻ ተደርጎ የዕቅድ አፈፃፀም ምዘና እስከ ክፍለ ከተማ ድረስ ተሠርቶበታል የሚሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ አሠራሩ ተቀባይነት ስላገኘ ለከተማው ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ እና ከክልሎች ለመጡ ለአብነት(አፋር፣ ሶማሌ፣ ሐረሪ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር) ጋር ባለፈው በጀት ዓመት የልምድ ልውውጥ መደረጉን ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ አሠራሩ በብዙ አቅጣጫ ችግሮችን ከጊዜ፣ ከበጀት፣ ከሰው ኃይል፣ ከተዓማኒነት፣ ከጥራት አንፃር እየፈታ ያለና የሥራ ድግግሞሽ የማስቀረት ሚናው የጎላ ነው፡፡ እንዲሁም የሚሠሩ የልማት ሥራዎች ከወረቀት በዘለለ ኅብረተሰቡ ከልማቱ ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆነ በተጨባጭ ማስረጃ ማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር ሆኖ ተገኝቷል በማለት አብራርተዋል፡፡

## ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ ቅዳሜ የሚታተም

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት ተሞክሮዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው እና በመጀመሪያ ደረጃ የጤና አሃድ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ኮንፍረንስ በሀገራችን አዘጋጅነት ተካሂዶ ነበር፡፡ ኮንፍረንሱ ሁሉም ሀገራት ጥራት ያለው እና ፍትሐዊ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነበር፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አሃድ የጤና አገልግሎትን ለሁሉም ለማዳረስ ቁልፍ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም፣ ሀገራትም ሆኑ ለጋሽ ድርጅቶች በመጀመሪያ ደረጃ ጤና አሃድ ላይ የሚያደርጉት ኢንቨስትመንት እና የሚሰጠው አገልግሎት የሚፈለገውን ያህል ያላደገ ከመሆኑም በላይ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደ ሀገርም እንደ ዓለምም ያጋጠሙ እንደ ኮቪድ ያሉ የጤና ችግሮች፣ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አሃድ ላይ ትኩረት በመስጠት ቢሠራ ወረርሽኞችን በቀላሉ መከላከል እንደሚቻል አሳይተዋል፡፡

በኮንፍረንሱ ሀገራት የውጭ ድጋፍን ብቻ ሳይጠብቁ በራሳቸው የውስጥ ፋይናንስ በመጠቀም እንዲሁም ሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች እንዴት ሀገራት ቅድሚያ ከሚሰጡት እቅድ ጋር ፕሮጀክቶቻቸውን አጣምረው ድጋፍ ማድረግ በሚችሉባቸው ሁኔታዎች ላይ የመከረ ነው፡፡ በኮንፍረንሱ የተሳተፉ ሀገራት የልምድ ልውውጥ ያደረጉበት እና እንደሀገር በዘርፉ የደረስንበትን ደረጃ በማስተዋወቅ ድጋፍም የተገኘበት ነበር፡፡

ከ50 በላይ ከሚሆኑ ሀገራት የመጡ 260 ተሳታፊዎች የታደሙ ሲሆን የክልል ተወካዮች፣ ኤክስፐርቶች፣ ተመራማሪዎች፣ ፈጻሚዎች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ ዓለም አቀፍ ለጋሾች፣ ሲቪል ማኅበራት፣ እና የግል የጤና ዘርፍ ተወካዮች በኮንፍረንሱ በመሳተፍ የፓናል ውይይት አካሂደዋል፡ ፡ በዓለም አቀፍ ኮንፍረንሱ ላይ የበርካታ ሀገራት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የተሠሩ ጥናታዊ ጽሑፎች በተመራማሪዎች ቀርበዋል። ኢትዮጵያን በተመለከተም እንዲሁ በሀገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ተመራማሪዎች ስለመጀመሪያ ጤና አገልግልት አሰጣጥ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበዋል፡፡

### በኢትዮጵያ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች

ከቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች ትኩረቱን በኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ መመዘን ላይ ያደረገውንና በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የተዘጋጀው አንዱ ነው፡፡ በሪፖርቱ መሠረት የኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት ሽፋን መሻሻል ያሳየ ቢሆንም አሁንም ድረስ ግን በገጠር የሚኖሩ ማኅበረሰቦች የጤና ሽፋን ተደራሽነት አዝጋሚ ነው። በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎትን በገጠር ለማስፋፋት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ሪፖርቱ ጠቁሟል።

ሌላው የቀረበው ጥናት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከኩዊንስላንድ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጥምረት የሠራው ነው፡፡ ጥናቱ በሀገራችን እየተሰጠ የሚገኘውን የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት ፕሮግራም እና ሲስተም ምዘና እና ቅኝት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው አሁን ያለው የፕሮግራሙ ፍሬምወርክ የፖሊሲ፣ ክሊኒካል እና የማኅበረሰብ ተሳትፎ የሚታዩ ክፍተቶችን ከመሙላት ባለፈ ሁሉን አቀፍ የጤና ተደራሽነትን ለማረጋገጥም የሚያስችል አጋጣሚን የሚፈጥር መሆኑን ነው፡፡

በዓለም አቀፉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት ኢንስቲትዩት የቀረበው ጥናት ደግሞ ከሀገራችን የጤና ፋይናንሲንግ ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን እና ስኬቶችን የዳሰሰ ነበር፡፡ በጥናቱ ውጤት ላይ ተመሥርቶም የሀገራችን የግሉ ዘርፍ ለጤና ፋይናንሲንግ ሊያበረክት የሚችለው አስተዋፅዖ እንዲጠናና የመንግሥት የጤና ፋይናንሲንግ ሥርዓትም ተጨማሪ ጥናቶች እንዲደረጉበት ተጠቁሟል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት መስጫዎች የአረጋውያን ማገገሚያ ሥራዎችን በተያያዥነት አገልግሎት እንደሰጡ የሚል ምክረ-ሃሳብ የዓለም የጤና ድርጅት ለኢትዮጵያ አቅርቧል፡፡ በቀረበው ምክረ-ሃሳብ የአረጋውያን ማገገሚያ በመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት መስጫዎች መስጠት መጀመሩ በቀላሉ አገልገሎቱን ማዳረስ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

በጆኤስአይ እና በዩኤስኤአይዲ ከዲጂታል ሄልዝ ጋር የተያየዙ ሦስት ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያ ጥናታዊ ጽሑፍ ዲጂታል ሄልዝ እና ሥነ-ጾታ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ሁለተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ ደግሞ ዲጂታል ሄልዝን በመጠቀም የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነበር፡፡ ሦስተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ ደግሞ የጤና ኤሌክትሮኒክስ ምዝገባ እና መረጃ አያያዝ ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡

በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ የሲስተም ማነቆዎችን የሚዳስስ ጥናታዊ ጽሑፍ ደግሞ የቀረበው በክሊንተን ሄልዝ አክሰስ ኢኒሺዬቲቭ ነበር፡፡ በጥናቱ መሠረት የጤና አገልግሎቱ ዋነኛ ማነቆ የፋይናንስ እና በጀት ማኔጅመንት ችግር ነው።

በመጨረሻ የምናየው ደግሞ በፓዝ ኢትዮጵያ የቀረቡ ሁለት የጥናት ጽሑፎችን ነው፡፡ የመጀመሪያው በግጭት የወደሙ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ተቋማትን በተሻለ መልኩ መልሶ ማቋቋም ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን፣ ዳግም የሚቋቋሙት ጤና ጣቢያዎች በተለይም የእናቶች እና ሕጻናት የአዕምሮ ጤና ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ምክረ-ሃሳብ ተቀምጧል። ሌላኛው ጥናታዊ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የሚሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎትን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን ወጪ እና ግብዓት የዳሰሰ ነበር፡፡

በአዲስ አበባ የተዘጋጀው ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስ የጋራ አቋም በመያዝ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ከጉባኤው በርካታ ተሞክሮዎችን መቅሰም ተችሏል፡፡

### ዓለም አቀፍ የጋራ አቋም

በጉባኤው ማጠናቀቂያ የተለያዩ የጤና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም መያዝ ተችሏል። የጋራ አቋም የተያዘባቸው ጠንካራ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ እንዲኖር አስፈላጊውን መዋዕለ ንዋይ ለመመደብና ለመደገፍ የላቀ የመንግሥትና ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነት መኖር፣ ዘላቂነት ያለው የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ ማቋቋም፣ ግለሰብ እና ማኅበረሰብን ማሳተፍ እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ትብብርን ማጠናከር የሚሉት ይገኙበታል።

ዓለም አቀፍ ጉባኤው በሀገራችን መካሄዱ በርካታ ጥቅሞችን ለሀገራችን ያስገኘ ነበር። በኮንፍረንሱ የተሳተፉ የውጭ ሀገር ዜጎችም በመድረኩ የልምድ ልውውጥ ማድረግ መቻላቸውን እና በቆይታቸውም ደስተኞች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ከዓለም አቀፍ ኮንፍረንሱ ጎንዮሽ በርካታ መርሐ-ግብሮች የተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ በሀገራችን ምን እንደሚመስል ከሌሎች ሀገራት ለመጡ ተሳታፊዎች የመስክ ጉብኝት አድርገዋል፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ለአምራችና ሸማች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የተገነባው የግብይት ማዕከል

**አንተነህ ቸሬ**

በየጊዜው እያሻቀበ የመጣው የዋጋ ንረት የኅብረተሰቡን፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል ኑሮ እጅግ የከበደ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለዋጋ ንረቱ የተለያዩ ምክንያቶች ሲጠቀሱ ቆይተዋል፡፡ መሠረታዊ የሆኑ የምጣኔ ኃብት መዋቅሮች አለመስተካከል፣ የሰላምና የፀጥታ መደፍረስ፣ የምርት አቅርቦት መቀነስ፣ የምርት ግብዓቶችና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እጥረት፣ የነዳጅ ዋጋ መጨመር እና የብር የመግዛት አቅም መዳከም ተደጋግመው ሲነገሩ የኖሩ የዋጋ ንረቱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ምክንያቶች ተደጋግመው ይገለፁ እንጂ ኑሮ ናላውን ላዞረው ኅብረተሰብ በሚፈለገው ደረጃ መፍትሄ አላስገኙም፡፡ ‹‹ኑሮውን አልቻልነውም … የዋጋ ንረቱ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል …›› የሚሉና ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሲደመጡ የቆዩ የኅብረተሰብ ድምፆች ዛሬም እየተስተጋቡ ነው፡፡ አንዳንድ ግለሰቦች የዘንድሮው የዋጋ ንረት ከዚህ ቀደም ከነበረው ሁሉ የተለየ ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡ በአንዳንዶቹ ምርቶች ላይ ደግሞ በገበያ የሚታየው የዋጋ ንረት ጠዋትና እና ከሰዓት በኋላ የዋጋ ልዩነት እስከማሳየት የደረሰ ነው ይላሉ፡፡

እጅግ የሚያስገርመው ነገር አገሪቱ ከበቂ በላይ የምታመርታቸው ምርቶች ሳይቀሩ ዋጋቸው ሰማይ መድረሱ ነው፡፡ ለአብነት ያህል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከበቂ በላይ ተመርተው ከማሳ የሚያነሳቸው አጥተው ለብክነት እንደሚዳረጉ የምርቶቹ ባለቤቶች ይናራሉ፡፡ በከተሞች ያለው የእነዚህ ምርቶች ዋጋ ግን ‹‹ጆሮ አይስማ›› የሚያሰኝ ነው፡፡

‹‹…አንዳንድ ጊዜ የአትክልትና ፍራፍሬ ገዢ ስለማይኖር ማሳ ላይ ይቀርና ከብት ይበላዋል …›› ይህ ከአንድ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች አርሶ አደር የተነገረ ነው፡፡ አርሶ አደሮቹ እንደሚሉት ሽንኩርትና ቲማቲም ከማሳቸው ላይ የሚሸጡት በዝቅተኛ ዋጋ ቢሆንም ምርቱ አዲስ አበባን ጨምሮ ወደ ሌሎች ከተሞች ከገባ በኋላ ግን ገበሬው ከሸጠበት ከእጥፍ በላይ በሆነ ዋጋ ይሸጣል። የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ለማሳያነት ያህል ተጠቀሰ እንጂ በሌሎቹም ምርቶች ላይ ያለው የዋጋ ንረት የሚቀመስ አይደለም፡፡

ታዲያ በዚህ ሁሉ ምስቅልቅል መሀል ደግሞ በንግድ ሰንሰለት ውስጥ የሚፈጠርና በኅብረተሰቡ በተለይም ደግሞ በሸማቹ ላይ የተጋረጠ እጅግ አደገኛ ነቀርሳ አለ፡፡ ይህ ነቀርሳ ውስብስቡ የደላሎች ሰንሰለት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ በደላሎች ተፅዕኖ ስር ያልወደቀ የኢኮኖሚ ዘርፍ የለም፡፡

‹‹ደላላ በመሀል ሲገባ ገበሬ እና ነጋዴ አይገናኙም። ደላላና ነጋዴ ይነጋገራሉ፤ ደላሎች ከገበሬው እንደፈለጉ ገዝተው ነው ለነጋዴው የሚሸጡት …›› ይላሉ አርሶ አደሮቹ። ይህ ሁኔታ ደግሞ ገበሬውንም ሆነ ሸማቹን ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ከማድረጉም ባሻገር የኅብረት ስራ ዩኒየኖች ምርቶችን በሙሉ አቅማቸው ተረክበው ለተጠቃሚው ማድረስ እንዳይችሉ እስከማድረግም እየደረሰ መሆኑ ይጠቆማል፡፡ ይህ ቅጥ ያጣው የደላሎች ተግባር ለአገሪቱ ምጣኔ ሀብትም ትልቅ መሰናክል ሆኗል፡፡

በንግዱ ዘርፍ ላይ የሚስተዋሉት እነዚህ ችግሮች መንግሥት አምራችና ሸማችን በቀጥታ በማገናኘት ሸማቹ የተሻለ ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ፣ አምራቹም ለምርቱ ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ ለሚያስችሉ አሰራሮች ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ እያደረጉት ይገኛሉ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማው የሚስተዋለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋትና አምራችን ከሸማች ጋር በቀጥታ ለማገናኘት የሚያስችሉ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ እየሰራ ነው፡፡ ከተማ አስተዳደሩ በአምስቱም የከተማዋ መግቢያ በሮች አካባቢ የሚስገነባቸው የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከላት ከእነዚህ የመፍትሄ አቅጣጫዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ ማዕከላት ከአምራች አርሶ አደሩ እስከ ሸማቹ ድረስ ያለውን እጅግ የተንዛዛውንና የተበላሸውን የግብይት ሰንሰለት ቀላልና ቀልጣፋ በማድረግ ሸማቹ ጥራት ያለው ምርት ፍትሀዊ በሆነ ዋጋ እንዲያገኝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ ይታመናል፡፡ የገበያ ማዕከላቱ የግብርና ውጤቶችን በወቅቱ በማቅረብ የአቅርቦት ችግር እንዳይፈጠር በማድረግ የከተማውን ነዋሪ ከኑሮ ውድነት ጫና ለመታደግ የሚያስችሉ ከመሆናቸው ባሻገር አምራቾችም ምርቶቻቸውን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማዕከላቱ በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ይህ አሰራርም ፍትሐዊ ግብይትን በመፍጠር ማኅበራዊ መረጋጋት እና ጤናማ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ እንዲኖርና በጎ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ታምኖበታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የዋጋ ንረት በኅብረተሰቡ ኑሮ ላይ የፈጠረው ጫና ከባድና አሳሳቢ በመሆኑ በከተማዋ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላት ግንባታዎችን በቀን ለ16 ሰዓታት ያህል በትጋት በመሥራት በፍጥነት ለማጠናቀቅ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡

የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላቱ ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት ማሟላት ያሉባቸውን ቴክኖሎጂዎች ሁሉ ያሟሉ ናቸው፡፡ ቴክኖሎጂዎቹ በሙቀት የሚበላሹ ምርቶችን ለማቆየት እንዲሁም በቅዝቃዜ ውስጥ መቆየት የማይችሉትን ምርቶችን ደግሞ ለማሞቅ የሚያስችሉ ናቸው። የደህንነት ካሜራዎች፣ የቆሻሻ ማስወገጃና የመኪና ማቆሚያም የማዕከላቱን አገልግሎት የተሟላ የሚያደርጉ ግብዓቶች ናቸው፡፡

የማዕከላቱን ግንባታ የሚያከናውነው የግንባታ ተቋራጭ ድርጅት የፕሮጀክቶቹን የዲዛይን ስራዎችንም እንዲሰራ መደረጉ የፕሮጀክቶቹን የግንባታ ጥራት ለመቆጣጠርና ፕሮጀክቶቹ ተጨማሪ ዋጋ እንዳይጠይቁ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩም ተጠቁሟል። ከዚህ በተጨማሪም የማዕከላቱ ግንባታ ለበርካታ ዜጎች ስራ እድሎችን ፈጥሯል። የማዕከላቱ ግንባታ በአገር በቀል የስራ ተቋራጭ ድርጅት እንዲከናወን መደረጉም ለአቅም ግንባታና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

ከእነዚህ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላት የመጀመሪያ የሆነውና በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የሚገኘው የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከል ጳጉሜ 4 ቀን 2015 ዓ.ም ተመርቆ ለአገልግሎት እንደበቃ ይታወሳል፡፡ ይህ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላት ግንባታ ተግባር ቀጥሎ፣ የትልልቅ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ከሚያስገነባቸው የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከል አንዱ የሆነውና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ (ቤተል ሳይት) የሚገኘው የኮልፌ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከል ጥቅምት 24 ቀን 2016 ዓ.ም፣ ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ይህ ማዕከል በሁለት ነጥብ ሦስት ሄክታር መሬት ላይ የተገነባ ሲሆን፣ ለግንባታውም ከአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ወጭ ተደርጎበታል፡፡

በ‹‹ኦቪድ ኮንስትራክሽን ግሩፕ›› (OVID Construction) በአስር ወራት ውስጥ ተገንብቶ የተጠናቀቀው የግብይት ማዕከሉ፤ በውስጡ አራት ትልልቅ ህንፃዎች፣ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ዘመናዊ የምርት ማቀዝቀዣና ማሞቂያ፣ ለምርት ማጠቢያ፣ ለባንኮች እና ለቢሮ ግልጋሎት የሚውሉ ክፍሎች፣ የምርት ማከማቻዎች፣ የጅምላና የችርቻሮ መሸጫ ሱቆች እንዲሁም በአንድ ጊዜ ከ200 በላይ ተሽከርካሪዎችን መያዝ የሚችል የመኪና ማቆሚያ ስፍራን ያካተተ ነው።

የግብይት ማዕከሉ የአስተዳደር ሕንፃ በውስጡ ለባንክ፣ ለካፌ እና ለቢሮ አገልግሎት የሚሆኑ ክፍሎችንም ይዟል፡፡ የችርቻሮ መሸጫ ሱቁ ደግሞ ከ80 በላይ የችርቻሮ ሱቆች፣ ሱፐር ማርኬት፣ ሚኒ ሱፐር ማርኬት፣ የምርት ማቀዝቀዣና ማሞቂያ ክፍሎች አሉት፡፡ ከ12 በላይ ሱቆችን አካትቶ የያዘው የጅምላ መሸጫ ሱቅም የማዕከሉ አካል ነው፡፡

ከ90 በላይ የምርት ማስቀመጫና ማከማቻ፣ ከዘጠኝ በላይ የምርት ማሞቂያ እንዲሁም ለሽያጭ የሚቀርቡ ግብዓቶች የሚታጠቡባቸው ከ10 በላይ የማጠቢያ ክፍሎች የሚገኙት ደግሞ በማዕከሉ የማከማቻ ሕንፃ ውስጥ ነው። ማዕከሉ በዋናነት ከምዕራቡ የኢትዮጵያ ክፍል ወደ አዲስ አበባ የሚገቡ የግብርና ምርቶች ለሸማቹ በቀጥታ የሚቀርቡበት የግብይት ስፍራ ነው፡፡

ማዕከሉን መርቀው ስራ ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የከተማ አስተዳደሩ በአምስቱም የከተማዋ መግቢያ በሮች የሚያስገነባቸው የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከላት አምራቹንና ሸማቹን በቀጥታ በማገናኘት፣ አምራቹ ጥራት ያለው ምርት እንዲያገኝና ዋጋ እንዲረጋጋ ለማድረግ እንደሚያስችሉ ተናግረዋል፡፡ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የተገነባው የኮልፌ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከል ወደ ስራ መግባት ሸማችን ከአምራች ጋር በቀጥታ በማገናኘት በከተማዋ የሚስተዋለውን የዋጋ ንረት በዘላቂነት በማረጋጋት ረገድ ጉልህ ሚና እንዳለውም ገልፀዋል፡፡



በቅርቡ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የጀመረው የኮልፌ የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከል

**ይህ ማዕከል በሁለት ነጥብ ሦስት ሄክታር መሬት ላይ የተገነባ ሲሆን፣ ለግንባታውም ከአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በላይ ወጭ ተደርጎበታል**

‹‹ይህ ፕሮጀክት በአምስቱም የአዲስ አበባ በሮች ትልልቅ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላትን በመገንባት የሕዝባችንን የኑሮ ጫና እናቃልላለን፣ አምራቹንና ሸማቹን እናገናኛለን ብለን ቃል ከገባንባቸው እና ቃላችንን ጠብቀን ከገነባናቸው ፕሮጀክቶች አንዱ ነው፡፡›› ሲሉ ከንቲባዋ ተናግረዋል፡፡ ‹‹የማዕከላቱ ግንባታ አምራችንና ሸማችን በቀጥታ ያገናኛል፡፡ አምራችና ሸማቹን ማገናኘት በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ዋጋን ያረጋጋል፣ ሸማቹ ጥራት ያለው ምርት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ በግብይት ሰንሰለት ላይ ያሉ ችግሮችን በማቃለል ግብይቱን የተረጋጋ ያደርገዋል፡፡ ››ሲሉም ጠቅሰው፣ በአጠቃላይ የከተማዋን ነዋሪዎች ትልቅ ጫና የሚያቃልል ፕሮጀክት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች የከተማ አስተዳደሩ በግብርና ምርቶች ዋጋ መናር ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለመቀነስ በሁሉም የከተማዋ መግቢያ በሮች የግብርና ምርቶች የግብይት ማዕከላትን እየገነባ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መሰል ፕሮጀክቶች በከተማዋ መግቢያና መውጫ በሮች ተገንብተው ለአገልግሎት እንዲበቁ የሚከናወኑ ተግባራት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አረጋግጠዋል፡፡

‹‹ለሕዝባችን የገባነውን ቃል በየደረጃው ተግባራዊ እያደረግን ነው›› ያሉት ከንቲባዋ፣ ‹‹አዲስ አበባን እንደስሟ አዲስና ውብ እናደርጋለን ስንል የሕዝቡንም ኑሮ በማሻሻል፣ የሰውም ሕይወት አብሮ እንዲያብብ በማድረግ ጭምር ነው፡፡ ለሕዝብ የገባነውን ቃል ወደተግባር እየመነዘርን ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ከተማ መገንባታችንን አጠናክረን እንቀጥላለን›› በማለት አስታውቀዋል፡፡

የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላት ግንባታ ኃላፊ ኢንጂነር ብስራት አባተ፤ የኮልፌ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከል ተገቢውን የጥራት ደረጃ አሟልቶ የተገነባ ማዕከል እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ‹‹ማዕከሉ ለ24 ሰዓታት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ የተገነባ ነው፡፡ ለዚህም የራሱ የሆነ የትራንስፎርመር ሰብስቴሽን አለው፡፡ መብራት በአጋጣሚ ቢቋረጥ ወዲያውኑ አገልግሎቱን ማስቀጠል የሚችሉ ጀነሬተሮችም ተገጥመውለታል›› በማለት የማዕከሉን ዘመናዊነት ይገልፃሉ፡፡

የአዲስ አበባ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ደቦ ቱንካ በበኩላቸው፣ ማዕከሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የተሟሉለትና የግብርና ምርቶችን ለማገበያየት የሚስፈልጉ መሰረተ ልማቶች የተዘረጉለት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ማዕከሉ በርካታ የጅምላ እና የችርቻሮ ማከማቻና መሸጫ ሱቆች፣ የምርት ማሞቂያና ማቀዝቀዣ ክፍሎች፣ ሰፊ የመኪና ማቆሚያ ስፍራ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ እና ሌሎች ዘመናዊ ግብዓቶች እንዳሉትም ኢንጂነር ደቦ አስታውቀዋል፡፡ ‹‹ማዕከሉ ለዜጎች ሰፊ የሥራ እድል ከመፍጠር ባሻገር፤ አምራቾችን ከሸማቾች በቀጥታ የሚያገናኝ ግዙፍ የልማት ትሩፋት ነው›› ብለዋል፡፡

ማዕከላቱ አምራቾች ምርቶቻቸውን በቀጥታ ከማሳ ወደ መጋዘን ይዘው እንዲገቡ በማድረግ በምርት ጥራትና በአቅርቦት አስተማማኝነት እንዲሁም በዋጋ ተመጣጣኝነት አምራቹንና ሸማቹን ፍትሃዊ ተጠቃሚ ማድረግ ጀምረዋል። ከሁለት ወራት በፊት አገልግሎት መስጠት በጀመረው የለሚ ኩራም ሆነ ሰሞኑን በተመረቀው የኮልፌ የግብርና ምርቶች ግብይት ማዕከላት ምርቶቻቸውን ያቀረቡ አምራቾች የማዕከላቱ መገንባት ምርቶቻቸውን ያለማንም ጣልቃ ገብነት ለሸማቹ እንዲያቀርቡ እንዳስቻላቸው መግለጻቸው የተጠቆመ ሲሆን፣ ይህም በዋጋው ላይም ተጨባጭ ለውጥ እንዲኖረው ማድረጉን መናገራቸው ተመልክቷል፡፡

በማዕከላቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሸማቾች በበኩላቸው፣ በማዕከላቱ የሚቀርቡ ምርቶች በሌሎች የግብይት ስፍራዎች ከሚቀርቡ ምርቶች የተሻለ ጥራትና ዋጋ እንዳላቸው መገለጻቸው ተጠቁሟል፡፡ በመደበኛ የግብይት ቦታዎች ላይ ጥራቱን የጠበቀና ጥራቱን ያልጠበቀ ምርት እኩል ሲሸጥ መመልከታቸውን የገለጹት ሸማቾች፣ በግብይት ማዕከላቱ የቀረቡ ምርቶች ግን ከፍተኛ ጥራት እንዲሁም ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ስለመሆናቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ድህነትን በርግጥም ታሪክ ለማድረግ!

ኢትዮጵያ ለግብርና ክፍለ-ኢኮኖሚ ምቹ የሆነ የአየር ንብረት፣ መሬት እና ሰፊ የውሀ ሀብት እንዳላት ብዙ ተብሏል ፤ ዘርፉን በማዘመን የተሻሻለ እና ጥራቱን የጠበቀ ምርት በማምረት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አቅም ማሳደግ እንደሚቻልም በስፋት ተነግሯል፣ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጥር፣ ከኢትዮጵያውያን የዕለት ተለት የሕይወት እንቅስቃሴ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የኢኮኖሚ ምንጭ እንደሆነም በተለያዩ አጋጣሚዎች ተገልጿል፡፡

ይህም ሆኖ ግን ከተነገረለት ይልቅ ያልተነገረለት እየሆነ፣ በዘርፉ የተሰማራውን 80 ከመቶ የሀገሪቱን የሰው ኃይል /አርሶ አደሩን እንኳን መመገብ ሳይችል ቀርቶ ሀገሪቱ በተለያዩ ወቅቶች በተከሰቱ የድርቅ አደጋዎች፣ ዜጎች ለከፋ ረሀብ ተጋልጠዋል ፣ በዚህም ብዙዎች ለሞት፤ ለመፈናቀልና ለስደት ተዳርገዋል።

ከዚህም ባለፈ ዘርፉ በደህናውም ወቅት ምንም ትርፍ ምርት የማይፈጠርበት በመሆኑ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እንዲያቆጠቁጡና እንዲያድጉ የሚያግዝ ሀገራዊ የካፒታል ክምችት መፍጠር እንዳይቻል አድርጓል። የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ምንጭም ይሄው የግብርና ዘርፍ መሆኑ የሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት እንዲቀጭጭ ምክንያትም ሆኗል።

በትክክለኛ የፖሊሲ አቅጣጫና በሀገራዊ ራዕይ የተቃኘ ቁርጠኛ አመራር ያለመኖር፣ ለግብርና ልማት ምቹ የሆኑ አካባቢዎችን ለይቶ አለማወቅ፣ የግብርና ቴክኖሎጂ ልምምድ አለመኖር፣ የግብርና ባለሙያዎች ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን ዘርፉ የአቅሙን ያህል እንደ ሀገር የሚጠበቅበትን እንዳያበረክት ዋነኛ ተግዳሮት ሆኖበታል፡፡

የለውጥ ኃይሉ ወደ ሥልጣን ከመጣበት ጊዜ አንስቶ፤ እነዚህን ክፍተቶች በመዝጋት ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ በስፋት ተንቀሳቅሷል። በተለይም በዘርፉ ያለውን አመራርና ባለሙያ በአዲስ ዕይታ አስተሳሰቡ ብቻ ሳይሆን አሠራሩን እንዲቃኝ በማድረግ ረጅም ርቀት ተጉዟል። በዚህም እየተመዘገበ ያለው ውጤት ተስፋ ሰጭ ስለመሆኑ ዕለት ተዕለት የምናያቸው ተጨባጭ ተሞክሮዎች ማሳያ ናቸው።

የአርሶ አደሩ የተሻለ የምርት ግብዓትና ማዳበሪያ የመጠቀም ልምድ ማሻሻል፣ ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ጉልህ ድርሻ ካለው የመስመር እርሻ ስልት ጋር መለማመድ እንዲሁም ብጥስጣሽ እርሻ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለማስቀረት በርካታ ኩታ ገጠም ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች በተያያዘ ሰፊ ማሳ ላይ ማምረት መጀመራቸው በባሕላዊ የምርት ስብሰባ ወቅት የሚባክነውን እስከ 30 በመቶ የሚደርስ ምርት ለመቀነስ አነስተኛና ከፍተኛ የምርት ስብሰባ ሜካናይዜሽን የመጠቀም ልምድ እየተሻሻለ መምጣቱ የዚህ እውነት አካል ናቸው።

ይህም የአርሶ አደሩን ምርታማነት በእጅጉ መሻሻል አስችሏል። በስንዴ ምርታማነት ላይ ያለውን ለማየት ብንሞክር እንኳን ፤ ከዚህ ቀደም በአንድ ሄክታር መሬት ከስድስት እስከ ስምንት ኩንታል ስንዴ ያመረት የነበር ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ግን በግብርና ሜካናይዜሽን በመታገዝ በሄክታር በአማካይ 64 ኩንታል ለማምረት ተችሏል። ይህ በሀገሪቱ በስንዴ ሊለማ ከሚችለው መሬት አንጻር ሲታይ የቱን ያህል በስንዴ ልማት እንደ ሀገር ያለንን አሁነኛ አቅም አመላካች ነው።

ይህ በግብርናው ዘርፍ እየተመዘገበ ያለው ተስፋ ሰጭ ውጤት ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተያዘላቸው ዕድገት አቅጣጫ እንዲጓዙ የሚያግዝ ሀገራዊ የካፒታል ክምችት መፍጠር የሚያስችል ነው። ከዛም ባለፈ የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪን ግኝትን በማሳደግ የሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት እመርታ እንዲያሳይ ትልቅ መነቃቃት ሊያመጣ ይችላል። በተለይም ለኢንዱስትሪና ለአገልግሎት ዘርፎቹ ዕድገት ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦ የጎላ ነው ።

ይህም ሆኖ ግን አሁንም በዘርፉ ከሚስተዋለው ችግር አንጻር እየታየ ያለው ስኬት በተሞክሮ መልኩ የሚወሰድ፤ ገና ብዙ ማሰብ፣ ማቀድ እና መሥራት የሚጠይቅ ነው ። በተለይም ዘርፉን በሁለንተናዊ መልኩ በማዘመን፤ አርሶ አደሩ የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆንበትን፤ ሀገርም እንደ ሀገር በዘርፉ ያላትን እምቅ አቅም ተጨባጭ ተስፋ በማድረግ ተጠቃሚ የምትሆንበትን የአስተሳሰብ እና የአሠራር ሥርዓት ማበጀት እና በጠንካራ ዲሲፕሊን መምራት ያስፈልጋል። ይህንን ማድረግ ስንችልም ነው ድህነትን ታሪክ ልናደርግ የምንችለው!።

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለብሔራዊ ምክክሩ ስኬታማነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የብዙ ባሕላዊና መንፈሳዊ እሴት ባለቤት የሆኑ ኢትዮጵያውያን ለገጠማቸው ችግር መላ መዘየድ ያውቁበታል፡፡ መከራ የቱንም ያህል ቢፈትናቸው «ይህም ያልፋል» «ይሁን ተመስገን» እያሉ መታገስን ብሎምመታዘብንይመርጣሉእንጂተስፋአይቆርጡም። በርግጥ ሰው ያለ ተስፋ አንድ ቀን ማደር የማይቻለው ደካማ ፍጡር ነውና ተስፋ ማድረግን የግድ ይለዋል፡፡ ይህም ሆኖ ግን በሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ተስፋን የሚያጨልሙና ነገን በጭላንጭል ለማየት የሚፈትኑ ችግሮች መግጠማቸው አይቀሬ ነው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያንም ብዙ ተስፋ አስቆራጭና እልህ አስጨራሽ የሆኑ በርካታ ችግሮች ገጥመውን «ይሁን ተመስገን» በማለት አልፈናቸዋል፡፡ ዛሬም ቢሆን እንደ ሀገር ያልተሻገርናቸው በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህ ችግሮች እርስ በእርስ እንዳንተማመንና እንድንፈራራ በማድረግ አንዳችን ሌላችንን በጥርጣሬ እንድናይ እያስገደዱን ነው፡፡ በአዳዲስ የተዛቡ ትርክቶችም እንዲሁ የእኛ የሆነውን ዛሬን ጨምሮ የልጆቻችንን ነገ የሚያበላሹ ክስተቶችን እያስተዋልን ነው፡፡

**እንደ ሀገር የተጋረጠብንን ሁለንተናዊ አደጋ ለመሻገር ብቸኛው አማራጫችን ሀገራዊ ምክክርና ንግግር ይሁን ካልን ደግሞ ትናንትን ለትዝታ ትተን ነገን ተስፋ ማድረግ የግድ ይለናል**

ያለንበትም ወቅት ከሁሉም በላይ በመሐከላችን ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ በማፈላለግ በውስጣችን ያለውን ቁርሾ ማስወገድ ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህም ኢትዮጵያዊ በሆነ ወግና ባሕል ሰከን ብሎ መነጋገርና መመካከር ቀዳሚውና አማራጭ የሌለው ዘላቂ መፍትሔ ነው፡፡

«ተማክረው ምን ያሉት ምን አይልም» እንዲሉ አበው፤ ሀገሪቷ አሁን ከገባችበት ምስቅልቅሎሽ መውጣት የምትችለው ሕዝቡ በአንድነት ሆኖ መምከርና መመካከር፤ መወያየትና መደማመጥ፤ ሲችል እንደሆነ ይታመናል፡፡ ብሔራዊ ምክክር ወቅታዊ አጀንዳችን የሆነውም ለዚሁ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ካሳለፈችውና ካለችበት ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ብሔራዊ ምክክሩ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን አንገብጋቢ እንደሆነ በብዙዎች የሚታመን ጉዳይ ነው፡፡ በሀገራችን ለረጅም ጊዜ የቁርሾ ምንጭ ሆነው የቆዩ እንደ ሀገር ልንስማማባቸው የሚገቡ፤ በልዩነት የቆምንባቸው፤ ጫፍና ጫፍ ሆነን የምንቆስልባቸው ብዙ ጠርዞች አሉ፡፡

ችግሮቻችን የቱንም ያህል ቢሰፉ መፍትሔው መነጋገር፣ መመካከርና ኢትዮጵያዊ በሆነው ባሕልና ወግ «አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ» መባባልና መረዳዳት ነው፡፡ ለዚህም በብዙዎች ዘንድ ትልቅ ተስፋ የተጣለበት ብሔራዊ ምክክሩ ዋንኛ አጋዥ አቅም ሊሆነን የሚችል ነው፡፡ ተስፋን ያነገበው ብሔራዊ ምክክሩ ቋጠሮዎችን ፈትቶ ቁርሾን ማሻር እንዲችል ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ብዙ የቤት ሥራ አለ፡፡

እንደ ሀገር የተጋረጠብንን ሁለንተናዊ አደጋ ለመሻገር ብቸኛው አማራጫችን ሀገራዊ ምክክርና ንግግር ይሁን ካልን ደግሞ ትናንትን ለትዝታ ትተን ነገን ተስፋ ማድረግ የግድ ይለናል፡፡ ከዚህም በላይ ኢትዮጵያዊ በሆነ ጨዋነት መነጋገር፣ መመካከርና መደማመጥን ልምድ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

በተለይም ለዘላቂ ሀገራዊ ሰላማችን መክፈል የሚገባንን የመጨረሻውን የሕይወት መስዋዕትነት ከመክፈል ይልቅ ወደ ቀደመው ማንነታችን ተመልሰን እንደ ባሕልና ወጋችን ችግሮቻችንን መፍታት ቅድሚያ የምንሰጠውና አማራጭ አልባ ምርጫ ሊሆን እንደሚገባ በአግባቡ መረዳትና ለተግባራዊነቱ ራስን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

ለዚህም ብዙ ዋጋ የማይጠይቀን፣ ነገር ግን በብዙ እጥፍ የምናተርፍበት ኢትዮጵያዊ ባህልና ወግ አለን። የመልካም እሴቶች ባለቤትነታችን ለብሔራዊ ምክክሩ ስኬት ትልቅ አቅም ሊሆን የሚገባ ብሔራዊ ሀብታችን ነው፡፡ የቀደመው ኢትዮጵያዊ ማንነታችን፣ ወግና ሥርዓታችን፣ ባሕልና ዕምነታችን ለአሁነኛ ችግሮቻችን መፍቻ ትልልቆቹ ጉልበቶቻችን ናቸው ፡፡

ዛሬ እነዚህ ሁሉ ሀገራዊ ፀጋዎቻችን የት ገቡ፤ ምን ዋጣቸው፤ ብለን ልንጠይቅና ልንመረምር ይገባል። ለመጠየቅም ሆነ ለመመርመር ታዲያ ኢትዮጵያዊ በሆነ ጨዋነት ሰከን ብሎ እንደ አንድ ሕዝብ በጋራ መነጋገር ይገባል፡፡ ንግግርና ምክክራችንም ስለ ትናንቱ ሳይሆን ስለ ነገ ተስፋችን ቢሆን እርምጃችን ወደፊት ይሆናል፡፡

ፍጹም ኢትዮጵያዊ ባልሆኑ ማንነቶች መገፋፋታችን በዝቶ ጦርነት መለያችን በሆነበት፤ የፈጠርነው የተሳሳተ ትርክት ከባሕል ዕምነታችን አስወጥቶ አገር ሊያሳጣን እያንዣበበ ባለበት በዚህ ጊዜ አሽቀንጥረን የጣልነውን ኢትዮጵያዊ ማንነት መመለስ የውዴታ ግዴታችን ነው።

መለያችን እየሆነ ለመጣው የእርስ በእርስ ጦርነት፣ ረሃብ፣ መፈናቀልና ስደት ተጠያቂዎቹ እኛው፣ መፍትሔዎቹም እኛው ነንና ተስፋ ባለመቁረጥ ነገን ዛሬ እንሥራ፡፡ እርግጥ ነው አሁን የያዝነው መንገድ ብዙ ድካምና መሰላቸት፤ አባጣ ጎርባጣ የበዛበት፤ መንገድ ነው፡፡ ያም ሆን ግን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሀገሩ ጉዳይ ተስፋ አይቆርጥምና ስለ ኢትዮጵያ የሰላ ጆሮ የነጠረ ዓይን ይኑረን፡፡

ሕዝቡ የኑሮ ሸክሙ የቱንም ያህል ከብዶ ቢጫነው የኑሮ ብልሃቱ አይጠፋውምና ቆሎ ቆርጥሞ ውሃ ከጠጣ «ይሁን ተመስገን አገር ሰላም ይሁን» በማለት በተስፋ የሚጠግብ ሕዝብ ነው፡፡ ለዚህም ነው ዕለት ዕለት የሚፈራረቅበትን መከራ፣ ችግር፣ ረሃብ፣ ጦርነት፣ ስደትና ጉስቁልናውን ተቋቁሞ ሀገራዊ አንድነትን ከሀገራዊ ምክክሩ በተስፋ እየጠበቀ ያለው።

ሀገር ሰላም ውላ ሰላም እንድታድር እንዲሁም ሕዝቦች በአንድነት፣ በመተባበርና በመግባባት እንዲኖሩ ብዙ ተስፋ የተጣለበት ብሔራዊ ምክክሩ ከሕዝቡ ተሳትፎ ውጭ ብቻውን ምንም አይደለም። ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የውይይት ሂደቶችን ከማመቻቸት ውጭ የማደራደር ሥልጣን የሌለው መሆኑ ለስኬታማነቱ የበርካቶችን የነቃ ሕዝባዊ ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡

በተለይም ሀገሪቷ ያለፈችበትን ውጣ ውረድ በቅርበት የሚያውቁ የማኅበረሰብ ክፍሎች አባቶች፣ እናቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሚዲያ ባለሙያዎችና ሌሎችም ለምክክሩ ስኬት የጎላ ፋይዳ ይኖራቸዋል። እነዚህ አካላትም ፍጹም በሆነው ኢትዮጵያዊ ጨዋነት መክረውና ዘክረው ሀገራዊ አንድነትንና ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ በኃላፊነት መንፈስና በቁርጠኝነት ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡

በሕዝብ ልብ ውስጥ የኖሩ ቁርሾዎች እንዲሽሩና የተለያዩ ቋጠሮዎች እንዲፈቱ ተስፋ የጣልንበት ሀገራዊ ምክክሩ ዕውን መሆን አለበት፡፡ ለዚህም በጎ የሆኑ እሴቶቻችንን ከጣልንበት ማንሳት ቀዳሚው ሥራችን ይሁን፡፡ ሆደ ሰፊነትን ከቤተሰብ ጀምረን በጎረቤት በአካባቢና በሀገር ላይ እናስተጋባ፡፡ ለብሔራዊ ምክክሩ ውጤታማነት የሰነቅነው ተስፋ ዕውን እንዲሆን ያለንን በማዋጣት ዘላቂ ሰላምን ለሀገራችን፤ አንድነትን፣ ስኬትና ብልጽግናን ለሕዝባችን እንመኝ ሰላም!

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## የታዛው ስር ዋርካ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

### ልጅነት ማርና ወተት ...

ልጅነቷ እንደ እኩዮቿ ነው:: ከሜዳ ከመስኩ፣ ስትሮጥ ትውላለች:: በትንሽ ነገር ደስ ይላታል:: ዕንባና ሳቅ አይለያትም:: በየሰበቡ ታለቅሳለች:: ይህ የሕጻንነቷ ጊዜ ለእሷ የተለየ ነው:: ወላጆቿ በስስት ያይዋታል:: ባልንጀሮቿ ለጨዋታ ይጠሯታል::

ውዴ ለቤተሰቦቿ ልጅ ብቻ ነች:: ማንም ጉዳት ድካሟን አይሻም:: ሁሉም ስትወጣ ስትገባ በፍቅር እየሸኘ ይቀበላታል:: እናት አባቷ የእሷን ዓለም ማየት ይሻሉ:: ልጃቸው በወጉ ብትማር ደስ ይላቸዋል:: በሆታና ዕልልታ ተድራ፣ በልጆቿ አያት ብታደርጋቸው ከልብ ይመኛሉ::

አሁን ውዴ በዕድሜ ከፍ ብላለች:: ልጅነቷን ተሰናብታ ለወላጆቿ አድራለች:: የታዘዘችውን እየሠራች ቤተሰቡን እየደገፈች ነው:: ወጣትነቷ ሊያብብ፣ ውበቷ ሊታይ ጀምሯል:: እንዲህ ሲሆን ወላጆች ብዙ ያስባሉ። ጎረምሶች ያማትራሉ፤ ዝምድናን የሚሹ ዓይናቸውን ይጥላሉ::

### እንግዳዋ ወይዘሮ ...

አንድ ቀን በእነ ውዴ መንደር አንዲት እንግዳ ከአዲስ አበባ መምጣታቸው ተሰማ:: ሴትየዋ እንግዳ ቢሆኑም ጠጉረ ልውጥ አይደሉም:: ተወልደው ያደጉት በእነ ውዴ አገር ‹‹ብቸና›› ውስጥ ነው:: ኑሮና ሕይወት ቢያርቃቸውም አንዳንዴ ብቅ እያሉ ዘመድ ይጠይቃሉ።

ውዴ ስለ አዲስ አበባ ሲወራ ሰምታለች:: ብዙዎች ወርቅ ይታፈስበታል፤ ብር ይቆጠርበታል ብለዋታል። ቤተሰቦቿ ለከተማው ያላቸው ስሜት የተለየ ነው። እንግዳዋን ጨምሮ በርካቶች ስፍራው ደርሰው ኑሮ እንደለወጣቸው ያውቃሉ።

አንድ ማለዳ በእነ ውዴ ቤት በርከት ያሉ ሰዎች ደርሰው በር አንኳኩ:: እንዲገቡ ተፈቅዶ ወደ ውስጥ ዘለቁ:: በአካባቢው አንቱ የተባሉ ሽማግሌዎች ናቸው። ሳይቀመጡ በፊት ጥያቄ አቀረቡ:: የውዴ ወላጆች ‹‹ልጃችሁን ለልጃችን›› ተባሉ::

ሰዎቹ በዚህ ብቻ ዝም አላሉም:: ሀሳባቸውን ማብራራት፣ መተንተን ያዙ:: ውዴ የታጨችው ሰሞኑን ከአዲስ አበባ ለመጡት ወይዘሮ ልጅ ነው። ልጃቸው በሥራ ምክንያት ባገር የለም:: እሱ በአካል ባይገኝም እንደወጉ ክብር እናት ሽማግሌዎች ልከው አስጠይቀዋል::

ሁኔታው ድንገቴ ቢሆንም እናት አባት አላንገራገሩም። ለደንቡ ጥቂት መክረው ጋብቻውን በደስታ ተቀበሉ:: ሴትዬዋ ከአዲስ አበባ መምጣታቸው የቤተሰቡን ስሜት ገዝቷል:: ሙሽራው ውጭ አገር ነው መባሉ ኩራት ሆኖ ሁሉም በይሁንታ ቃሉን ሰጥቷል::

ውዴ በእሷ ላይ የተመከረውን ሰምታለች:: ጉዳዩ ቢያስደግጣትም አልተቃወመችም:: ካለችበት የተሻለ ዓለም እንደሚቆያት ስታስብ ነገዋን ናፈቀች:: ወርቅ በሚታፈስባት፣ ብር በሚቆጠርባት ከተማ ምቹ ትዳር መያዝን አልጠላችም:: ኑሮው ከብቸና መብለጡን ያመኑ ሁሉ በጋብቻው ተስማሙ:: ዕድለኛነቷ ያስቀናቸው፣ ዕጣ ፈንታዋ የገረማቸው ባልንጀሮቿ እሷን መሆን ተመኙ::

### ስንብት ...

አሁን ትንሽዋ ውዴ ወላጆቿን ልትተው፣ አገር ቀዩውን



ወ/ሮ ውዴ አስ ተስፋው

ልትርቅ ነው:: እናት አባት ቆመው ባይድሯትም በዓይን ላላዩት፣ ባገር ለሌለው አማታቸው ሰጥተዋታል። በቃ! ከዚህ በኋላ ውዴ የባሏን እናት እጅ ይዛለች:: ወላጆቿን፣ ጓደኞቿን ተሰናብታለች:: ‹‹አይዞሽ በርቺ፣ ልመጂ›› ያሏትን አመስግና ካገር ቀየው ርቃለች::

ውዴና አማቷ አዲስ አበባ ደርሰዋል:: እናት የልጃቸውን ሚስት ይዘው ቤታቸው ሊገቡ መንገድ ላይ ናቸው:: እሷ የገጠር ልጅ ነች:: ስለከተማ ሕይወትና ድምቀት አታውቅም:: እግሯ ከመኪናው ወርዶ ሀገሩን ከማየቷ ተገርማለች:: ግርግሩ፣ የሰዉ ብዛት፣ የመኪናው ፍጥነት . . . አስደንቋታል::

ሁሉን አልፈው ከታሰበው ሰፈር ሲገቡ ወይዘሮዋ እግራቸው ወደ አንድ መንደር አቀና:: ደማቅና ብዙ ነዋሪ ያለበት ነው:: አላፊ አግዳሚው የሚተያይ አይመስልም። ሁሉም በራሱ ዓለም ከላይ እታች ይሮጣል:: ውዴ ወይዘሮዋን እየተከተለች ነው::

አማትና ምራት ጥቂት ተራምደው ከአንድ ግቢ ደረሱ። ውዴ ባልዋ ባገር እንደሌለ ብታውቅም እንደ ሙሽራ ‹‹ዕልል›› ቢባልላት ተመኘች:: እንዳሰበችው አልሆነም። ሴትዬዋ መለስ ያለውን በር ገፋ አድርገው እግራቸውን አስቀደሙ:: ግራ እንደገባት ተከተለቻቸው። ከጠባቧ ክፍል አንድ ባለ ሁለት ከራንቾች ጎልማሳ ተቀምጧል::

ሰውዬውና አማቷ ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ:: ውዴ የያዘችውን ጓዝ አስቀምጣ ከአንድ ጥግ አረፍ አለች። ጥቂት ቆይቶ ሰውዬውና ውዴ ለትውውቅ እጃቸው ተጨባበጠ:: ከዚህ በኋላ ወይዘሮዋ አልዘገዩም:: ለውዴ የወደፊት ባሏ፣ የትዳር አጋሯ ይህ ሰው መሆኑን እቅጩን ነገሯት::

### ሙሽሪት ልመጂ ...

ውዴ በሰማችው እውነት ክው ብላ ደንግጣለች። ውጭ ሀገር ነው ተብላ በእምነት የተዳረችለት ባሏ ይህ ሰው መሆኑን ባወቀች ጊዜ አንገቷን ደፋች:: አሁን ‹‹ከፋኝ፣ ተቀየምኩ›› የምትልበት ጊዜ አይደለም:: አገር አታውቅም፣ ዘመድ ወዳጅ የላትም:: ጨነቃት፣ ግራገባት፣ አሳልፈው በሰጧት ወላጆቿ ድርጊት ከልብ አዘነች። ዕድሏን አማረረች:: ያለማቋረጥ ስታለቅስ ዕንባዋን ያበሰላት አልነበረም::

እነሆ! ቀን አልፎ ቀን ተተካ:: አሁን የትናንትናዋ ትንሽ ልጅ ‹‹ወይዘሮ›› መባል ይዛለች:: ውዴ

... ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የታዛው…

ከ16ኛ ገጽ የዞረ

ከአባወራዋ ጋር ሕይወት ብትጀምርም ኑሮ አልተመቻትም፡፡ በየቀኑ የሆነባትን እያሰበች ትተክዛለች፡፡ የወላጆቿ ድርጊት ያናድዳታል፡፡ የእሷ አምኖ መቀበል ያበሸቃታል፡፡ የወደ ፊት ዕጣ ፈንታዋን እያሰበች በሀሳብ ትነጉዳለች፡፡

አካል ጉዳተኛ ባሏ ልበ ክፉ አይደለም፡፡ የትዳር አጋር በማግኘቱ ከልቡ ተደስቷል፡፡ ባጋጠመው አደጋ በክራንች መጠቀም ከጀመረ ጥቂት ሰንብቷል። ጉዳተኛ በመሆኑ እንደ በፊቱ ሠርቶ አይገባም። ውዴ ይህን ሁሉ አምና ተቀብላለች፡፡ በአካል ጉዳቱ አልናቀችውም፡፡ የወላጆቿን ድርጊት ግን በዋዛ ይቅር ማለት አልተቻላትም፡፡ ዘመድና አገር አታውቅም፡፡ ልጅነቷን እየከፈለች ነው፡፡

ውዴ በማታውቀው ዕቅድ ብትጠለፍም ዝላ መውደቅን አልመረጠችም፡፡ ሁኔታዎች ቢያደክሟትም እየተንገዳገደች ቆማለች፡፡ አንዳንዴ ለውስጧ ‹‹ዕድሌ ነው›› ስትል ትነግረዋለች፡፡ እንዲያም ሆኖ ራስዋን ከኑሮ አላምዳ፣ ሕይወትን መቀበል አላቃታትም፡፡

ቀናት እየገፉ፣ ወራት እየተተኩ ነው፡፡ የውዴን ልጅነት የሚያዩ ያዝኑላታል፡፡ ጥንካሬዋን ያስተዋሉ ያደንቋታል፡፡ ትንሸዋ ልጅ ሆዷ እየገፋ ሰውነቷ እየጨመረ ነው፡፡ ርጉዝ መሆኗን አውቃለች፡፡ ይህ እውነት የትም እንዳትሄድ አስሯታል፡፡

### ባል አልባው መልስ…

ከቀናት በአንዱ ብቸና ካሉት የውዴ ቤተሰቦች ድንገቴ ጥሪ ደረሰ፡፡ አያቷ በትልቅ ድግስ የልጅ ልጃቸውን መልስ ሊጠሩ ተዘጋጅተዋል፡፡ ጥሪው የደረሳት ውዴ ጭንቅ ያዛት፡፡ ከዚህ ቀድሞ ባሏ ውጭ አገር መሆኑ ተሰምቷል፡፡ አሁን አብረው መኖራቸው በመታወቁ ለእሷ ክብር ሲባል ድግስ ተዘጋጅቷል፡፡

ውዴ የቤተሰቦቿን ሀሳብ አልገፉችም። አክብረው ስለጠሯት ደስ ብሏታል፡፡ ባሏን ይዛ ከጥሪው ለመገኘት ግን አቅም አጥታለች፡፡ ብዙ የተወራለት፣ ባሏን ‹‹ይህ ነው›› ብላ መውሰድ አልሆነላትም፡፡ ከጥሪው መቅረት አልቻለችም። ለእሷም፣ ለቤተሰቦቿም ስትል በደሷን ሁሉ ረሳች፡፡ ባሏን በቤቱ ትታ ከአማቷ ጋር በድግሱ ተገኘች፡፡

ስፍራው ሲደርሱ ትልቅ ዳስ ተጥሎ በርካታ ታዳሚ ተገኝቷል፡፡ ጭፈራው፣ ዕልልታው በበዛበት ድግስ አገሬው የውዴን ባል ለማየት ተሸቀዳደመ፡፡ ባልንጀሮቿ ብዙ የተባለለትን ሰው ለማወቅ አንጋጠጡ። እንደ ባል በውዴ ቀኝ የተቀመጠ የለም፡፡

ከሙሽሮቹ ቦታ ሙሽሪትን ብቻ ያዩ “ለምን?።፣ “እንዴት?፡፡ ሲሉ ጠየቁ፡፡ ውዴ ለመዋሸት አፏን ያዛት፡፡ አማትና ቤተሰቦቿ ግን ምላሽ አላጡም። ለጠየቃቸው ሁሉ ሙሽራው ባገር አለመኖሩን እያሳመኑ ተናገሩ፡፡

ስለ ልጃቸው ትዳር ጭምጭምታ የሰሙት አባት ተመልሳ እንዳትሄድ ሊያሳምኗት ሞከሩ፡፡ እሷ ኑሮ ብላ የገባችበትን ሕይወት ማፍረስ አልፈለገችም። “ትዳሬን አልፈታም፣ ባሌን አልተውም፡፡ ስትል ‹‹እምቢኝ›› አለች።

ውዴና አባቷ ሙግት ይዘዋል፡፡ እሷ በውሸት ታሪክ የልጅነት ዓለሟን፣ የጠዋት ዕድሏን፣ እንደሰበሩባት እየነገረቻቸው ነው፡፡ አሳልፈው ከሰጧት፣ ከባልንጀሮቿ በታች ካደረጓት በኋላ አሁን ‹‹ ተመለሺ፤ ትዳሩ ይቅርብሽ›› ማለታቸው አልተዋጠላትም፡፡

የአባትና ልጅ ስንብት ባለ መስማማት ተቋጨ። አባት ውዴን ከሸኙ በኋላ ያለ እሷ ፈቃድ ባደረሱባት በደል ፀፀት ገባቸው፡፡ ይህ ስሜት ውስጣቸው አልቀረም። ተታለልኩ፣ ተዋሸሁ ብለው ከሙሽራው ወገኖች ጠብ ገጠሙ፡፡

ውዴና አማቷ ወደ መጡበት ተመልሰዋል፡፡ ሕይወት በአዲስ አበባ ከባድ ነው፡፡ የአንድ እጅ ገቢ ባለበት ጎጆ የዕለት አስቤዛው ይቸግራል፡፡ አካባቢውን የነዋሪው ሕይወት ያመሳስለዋል፡፡ የአብዛኞች ገቢ ቤትን ለሴተኛ አዳሪዎች በማከራየት ላይ ተመሥርቷል። ውዴ ትዳር ከያዘች ጀምሮ ቤቷን የምትመራው በየቀኑ የጓዳ አልጋዋን እያከራየች ነው፡፡

የመጀመሪያ ልጅዋ ከተወለደች በኋላ ሕይወት መክበድ ያዘ፡፡ አካልጉዳተኛ አባወራ፣ ጨቅላ ሕፃንና አሮጊት እናት ባሉበት ቤት ጫናው በውዴ ትከሻ ላይ ወደቀ፡፡ ቤተሰቡን ለማኖር የልጅነት ጉልበቷን ገበረች። በየቤቱ ልብስ ማጠብ፣ ያገኘችውን መሥራት ግዴታዋ ሆነ፡፡ እንዲያም ሆኖ ጠግቦ ማደር አልሆነም፡፡ አንዱ ሲሞላ ሌላው እየጎደለ ቤቱ በችግር ተፈተነ፡፡

### የነበረው እንደነበረ…

ጊዚያት ነጎዱ፡፡ ሕይወት አልተለወጠም፡፡ ውዴ ተጨማሪ ሦስት ልጆች አከታትላ ወለደች፡፡ በቤቱ ድህነትና ችግር ተንሰራፋ፡፡ አባወራዋ ሕመሙ ባሰ። እግሮቹ መላወስ አቃታቸው፣ ከዊልቸርም ዋለ። ይህ አጋጣሚ እጆቹን ለልመና አዘርግቶ ምጽዋት አስጠየቀው፡፡

ውሎ አድሮ በሰፈሩ ቤትን ለሴተኛ አዳሪዎች ማከራየቱ ቀረ፡፡ ውዴ እጇ ነጠፈ፡፡ ልጆቿ ተራቡ። ይሄኔ ለሊት፣ ዘጠኝ ሰአት እየወጣች ለንግድ ቤቶች ቡና መቁላት ጀመረች፡፡ መንገዱ ለሌባ ያሰጋል፡፡ የምታገኘው ገንዘብ ቀዳዳ አይደፍንም፡፡ እሱን ይዛ ለቤተሰቡ ዳቦ ታቃምሳለች፡፡

ዓውደ ዓመት በደረሰ ግዜ ውዴ ጭንቀቷ ያይላል። ልጆቿ የሰው ቤት እንዳያዩባት አትሆነው የለም፡፡ አንዳንድ ልበ መልካሞች ዝም አይሏትም፡፡ እንደወጉ የአቅሟን ሞልታ ቀኑን ታሳልፋለች፡፡

### ያልጎበጠ ትከሻ

ውዴ አምስተኛውን ልጅ አርግዛለች፡፡ ይህ እርግዝናዋ ጤና አልሰጣትም፡፡ በሄደችበት ሆስፒታል ሁሉ ልጁ በተለመደው አቀማመጥ ላይ እንዳልሆነ ተነግሯታል። አንድ ቀን በድንገት ምጥ ተያዘች፡፡ ሆስፒታል መድረስ አልቻለችም፡፡ ቤት ውስጥ ወንድ ልጅ በሰላም ወለደች። አራት ሴቶች ስላሏት ልጇቿ ወንድም ስላገኙ ተደሰተች። በሆስፒታል አብሯት የዋለው ሕጻን ብዙ አልቆየም፡፡ መሞቱ ተነገራት፡፡

ከዓመት በኋላ ውዴ በድጋሚ ነፍሰጡር ሆነች፡፡ ውሎዋ ይፈትናል፡፡ ሥራዋ ፀሐይ፣ ዝናብ፣ እሳት፣ ውሀ አይልም፡፡ የአሁኑ እርግዝና በጣም እያስጨነቃት ነው፤ ዕንቁጣጣሽ ደርሷል፡፡ ዕለቱን ቡና ስትቆላ ውላለች። ድንገት ሕመም ተሰማት፡፡ ሰባት ወሯ ቢሆንም ስሜቱ ምጥ ነበር ፡፡

ሐኪም ቤት ስትደርስ ባሰባት፡፡ ማማጥ ጀመረች። ሥራ የጎዳው አካሏ አላገዛትም፡፡ በድካም ዛለች፡፡ ጊዜው ደርሶ በጭንቅ ስቃይ ተገላገለች፡፡ ጥቂት ቆይቶ ሐኪሞቹ ሁለት ልጆች ስለመውለዷ ነገሯት፡፡ ለጊዜው ከሕመሟ እፎይ አለች፡፡ ጥቂት ቆይቶ ግን ሕመሙ ቀጠለ፡፡ ሦስተኛው ልጅ እየመጣ ነበር፡፡

ሦስት መንታ ልጆችን የወለደችው ውዴ ለተሻለ ሕክምና ወደ ሌላ ሆስፒታል ተላከች፡፡ እስካሁን ልጆችዋን ያሳያት የለም፡፡ ለቀናት ሆስፒታል ስትተኛ ሙቀት ክፍል መሆናቸው ተነግሯታል፡፡ ከድካሟ ስትነቃ ‹‹ልጆቼን›› አለች ሁሉም ዝም አላት፡፡ ደግማ ጠየቀች፡፡ የሰማችው ክፉ ዜና ውስጧን ሰበረው፡፡ የሶስቱም መንታ ልጆቿ ሕይወት አልቀጠለም፡፡

### ውዴ - የታዛው ስር ዋርካ

ውዴ በቤቷ ታዛ ስር ላሉ ነፍሶች ሁሉ ታላቅ ዋርካ ነች፡፡ ሁሉንም በጉልበቷ፣ በላቧ ወዝ ታሳድራለች። አካል ጉዳተኛ ባለቤቷን አክባሪ፣ ትዳሯን ወዳድ ወይዘሮ ናት፡፡ ዛሬ ዕድሜ የተጫናቸውን አማቷን ጨምሮ ለሥራ ያልደረሱ ልጆቿ ተስፋ የእሷ ትከሻ ነው፡፡ ውዴ ለባለቤቷ ሚስት ብቻ አይደለችም፡፡ እጅና እግሩም ነች። እንደ እናት፣ ታስብለታለች፣ እንደ ሚስት አጋሩ ነች፡፡

በእነ ውዴ ቤት እንደሌሎች ጤፍ መግዛት ይከብዳል። ከዕለት የማይዘለው ገቢ ከግዢ እንጀራ አያልፍም፡፡ በተገኘ ጊዜ ሁሉም እሱን ተቃምሶ ያድራል። በሌለ ቀን ጥሬ ቆርጥሞ ውሀ ጠጥቶ ማደር ብርቅ አይደለም፡፡ እንዲህ ሲሆን እናት ስለራሷ ግድ አይላትም። ቅድሚያውን ለልጆቿ ትሰጣለች፡፡

አንዳንዶች የአካሏን መወፈር ሲያዩ ጠግባ አዳሪ ትመስላቸዋለች፡፡ እሷ ግን በልተው ከተረፋቸው ፍርፋሪ ለልጆቿ ቢሰጧት ለመቀበል አታፍርም፡፡ ጠንካራዋ፣ ብርቱዋ ሴት ዛሬ ከአስራ ስምንት ዓመታት በላይ ትዳሯን መርታለች፡፡

እነዚህ ዓመታት በዥንጉርጉርና ሻካራማ የሕይወት መንገድ አራምደዋታል፡፡ ትናንትን በችግር አልፋለች፡፡ ዛሬ ላይ ስትቆም ስለነገ ተስፋ አትቆርጥም፡፡ የቤቱ ታዛ የቤተሰቧ ዋርካ ነች፡፡ ውዴ አለ ተስፋው፡፡


## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ልደታ ክ/ከ ወረዳ 06 የቤት ቁጥር 134 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0000741306 ዘበነ ፍቅሬ ገብሬ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ልደታ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከቁጥር 0001 እስከ 0250 እንዲያሳትሙ ተፈቅዶ ከታተመው ውስጥ ከ51 እስከ 100 የተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀስው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ልደታ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ዘበነ ፍቅሬ ገብሬ**

## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 942 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0074544034 አቢሲኒካ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ምሥራቅ አ/አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 0001 እስከ 0026 የተሰራበት እና ከቁጥር 0027 እስከ 0050 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀስው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ምሥራቅ አ/አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም አቢሲኒካ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 965/ሀ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0006003391 አድያምሰገድ እያሱ መልኬ የተመዘገብኩበት የካ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 001 እስከ 250 ያልተሰራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት የተመዘገብኩበት የካ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**ግብር ከፋይ ስም አድያምሰገድ እያሱ መልኬ**

## ማስታወቂያ

ቢኮኔክትድ ፕሪንቲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህ 1 ነባር ባለአክሲዮን ያለዉን አክሲዮን በሽያጭ ለ1 አዲስ ገቢ ባለአክሲዮን በሽያጭ ለማስተላለፍ ጥያቄ አቅርበዋል።

**<u>የነባር ባለአክሲዮን (ሻጭ) አድራሻ</u>**

Beconnected labeling PLC- ከተማ ኣ.አ ክ/ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ወረዳ 01 የቤ.ቁ አዲስ የአዲስ ገቢ ባለአክሲዮን (ገዥ) አድራሻ EU Bestsaler Trading PLC- ከተማ ኢ.አ ክ/ከተማ ቦሌ ወረዳ 02 የቤቁ አዲስ ከላይ በቢኮኔክትድ ፕሪንቲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማህ የተገለጸላቸው አመልካቾች በዚህ የ15 ቀናት የተቃውሞ ጥሪ ጊዜያት ዉስጥ ዉህደቱ እንዳይመዘገብ ተቃውሞ ከቀረበበት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንኑ ለሚመለከተው አካል የሚያሳዉቅ ሲሆን ተቃውሞ ካልቀረበ ግን የተቃዉሞ ጥሪ ማስታወቂያው ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን የአክሲዮን ማህበራት አደረጃጀት ድጋፍና የውህደት ዴስክ በመቅረብ የውህደት ማስታወቂያ ደብዳቤ የተሰጠ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የብርታት ተምሳሌቱ ምሁር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ግብርና ለኢኮኖሚ የጀርባ አጥንትና በኢትዮጵያውያን ሕይወት ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያለው ነው፡፡ ግብርናው ሕዝብን ስለመገበና የሀገርን ምጣኔ ሀብት ስለደገፈ ብቻ ወሳኝ ዘርፍ የሆነው አይደለም። ከዚህም ባለፈ የግብርናው ዋና ባለድርሻ አርሶ አደሩ ክረምት ከበጋ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል እያመረተ ያለበት ሁኔታም አርሶ አደሩን የጥንካሬ ተምሳሌት አርጎታል፡፡ ግብርና ብዙ ሥራ ያለውና አድካሚ እንደመሆኑ አርሶ አደሩ ብቻ ሳይሆን በጠንካራው በአርሶ አደሩ ቤተሰብ ውስጥ ያደገ አብዛኛው ሰው ጠንካራና ብርቱ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የዕለቱ እንግዳችንም የጠንካራ ገበሬ ልጅ ምሳሌ ውጤታማ መምህርና ነጋዴ ናቸው፡፡ ዶክተር መስፍን ሞላ ይባላሉ፡፡ ዶክተር መስፍን ገና በለጋ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመታቸው ጀምሮ ፍየል፣ ጥጃ እያሉ በርካታ ከብቶችን ጭምር አግደዋል፤ ገና የ12 ዓመት ታዳጊና የ6ኛ ክፍል ተማሪ እያሉም በሬ ጠምደው ማረስም ጀምረዋል፡፡ ከእርሻ ሥራው በተጓዳኝ በሬ ጠምዶ ከማረስ ጀምሮ በጉልጓሎው፣ በአረሙ፣ በአጨዳውና በውቂያ ሁሉ አልፈዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ሥራና ድካም ውስጥ ከእዚህ ቤተሰብ ቤት አንድ ጉዳይ አይረሳም፡፡ እሱም ትምህርት ነው። በትምህርት ሰዓት ቀልድ የለም፡፡ የግብርና ሥራው በሙሉ የሚሰራው ከትምህርት ሰዓት ውጭ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ወላጅ አባታቸው ለትምህርት ትልቅ ቦታ የሚሰጡ በመሆናቸው ነው፡፡ ለእርሻ ሥራቸው የሚሰጡትን ያህል ትኩረት ለትምህርታቸውም እንዲሰጡ ያግዟቸዋል፡፡ ከትምህርት የተረፈ ጊዜያቸው ግን ሙሉ በሙሉ ለቤተሰቡ የግብርና ሥራ ይውላል፡፡ ይህም ጠንካራና ብርቱ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

ከትምህርታቸው ጎን ለጎን በግብርና ሥራ ብርቱ ገበሬ እንደነበሩ ያስታወሱን ዶክተር መስፍን ለማ በዲላ ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና ስነ-ባህሪ ተቋም ዲን ናቸው። ጎበዝ ተማሪና ብርቱ ገበሬ የነበሩት ዶክተር መስፍን፣ የማያልቀው የገበሬ ቤት ሥራ ከትምህርታቸው አላስተጓጎላቸውም፤ ይልቁንም ጎበዝ ተማሪ እንዲሆኑ አገዛቸው፡፡ የግብርና ሥራው የቱንም ያህል ቢበዛ አንድም ቀን ከትምህርት ገበታቸው ተስተጓጉለው አያውቁም፡፡

ተወልደው ያደጉት በቀድሞ አጠራሩ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በአዲሱ አጠራሩ ደግሞ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሆሳዕና ከተማ ነው፡፡ በአዲሱ የክልል አደረጃጀት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መቀመጫ በሆነችው ሆሳዕና ተወልደው ያደጉትና የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም የተከታተሉት ዶክተር መስፍን፤ ገና ከልጅነት ዕድሜያቸው ጀምረው ከማለዳው 11 ሰዓት መነሳት የዕለት ተዕለት ተግባራቸው እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

እሳቸው ተማሪ የነበሩበት ወቅት እንዲህ እንደ ዛሬው ተማሪ ብዙ የትምህርት ድጋፍ የሚያገኝበት ባለመሆኑ በብዙ ልፋትና ድካም ውስጥ እያለፉ ነው ትምህርታቸውን መከታተል የቻሉት፡፡ የልፋታቸው ውጤትም አስደሳችና አመርቂ ሆነላቸው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት ማጠናቀቅ ቻሉ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተውም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በትምህርት አስተዳደር ያዙ፡፡

የመጀመሪያውን የሥራ ዓለም ሕይወታቸውን አሀዱ ያሉት ከትውልድ አካባቢያቸው ሆሳዕና ከተማ 32 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው በሀዲያ ዞን ሶሮ ወረዳ ጊንቢቾ ከተማ ላይ በሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በምክትል ርዕሰ መምህርነት ነበር፡፡ በጠንካራ የሥራ ባህል ያደጉት ዶክተር መስፍን፣ በወቅቱ የተማሩትን ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል ከፍተኛ ጉጉት የነበራቸው ስለመሆናቸውም እንደተመሰከረላቸው ይገልጻሉ፡፡

በወጣትነት ሙቅ ልባቸው የግብርና ሥራውን ያቀላጥፉ የነበሩት ዶክተር መስፍን፤ ይህን ብርታታቸውን በትምህርት ሕይወታቸው ደግመው ብቻ አላበቁም፤ ለሶስት ዓመታት በምክትል ርዕሰ



ዶክተር መስፍን ሞላ

መምህርነት ባገለገሉበት ወቅትም ደግመውታል፤ ይህን ትጋታቸውን የተመለከተው የሚሰሩበት ወረዳ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት የመማር ዕድል እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረላቸውና ይህን ትምህርታቸውንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መከታተላቸውን ገልጸዋል፡፡

ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ይዘው ወደ ዲላ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት ሁለት ወር እንዳገለገሉ የዩኒቨርሲቲው ሀዋሳ ቅርንጫፍ የትምህርት ክፍል አስተባባሪ ሆነው ተሾሙ። በዩኒቨርሲቲው የዘጠኝ ወር የአገልግሎት ጊዜያቸውም የዲላ ዩኒቨርሲቲ የተከታታይ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ሆነው ተሹመዋል፡፡ ዶክተር መስፍን፤ በዩኒቨርሲቲው በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡ ከአራት ዓመታት ቆይታ በኋላም የፒኤችዲ ትምህርታቸውን የመከታተል ዕድል ከዩኒቨርሲቲው አግኝተዋል፡፡

የፒኤችዲ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ በሚከታተሉበት ወቅት ደግሞ ዶክተር መስፍን ከቢዝነሱ መንደር ጎራ የማለት አጋጣሚ ተፈጠረላቸው፤ ይህም ትርፍ ጊዜውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት እድል ፈጠረላቸው፡፡ አጋጣሚውን ተጠቀሙበት፤ የፒኤችዲ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የንግድ ሥራን አብረው ይከውኑ ጀመር፡፡

‹‹ሰው ከጣረ ትልቅ ደረጃ ላይ ይደርሳል፤ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም የቻለና ለሥራ የሚተጋ ሰው ምንም አያቅተውም የሚል አመለካከት ያላቸው ዶክተር መስፍን፤ በወቅቱ የተለያዩ የመንግሥት ጨረታዎችን በመከታተል የስቴሽነሪ ዕቃዎችን ለተለያዩ ተቋማት ለማቅረብ ነበር ወደ ንግድ ሥራው የገቡት፡፡

በወቅቱ ጨረታ አሸንፎ የሚፈለገውን ዕቃ ገዝቶ ለማቅረብ እጅግ ፈታኝ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ ያም ቢሆን ይህ ስራ ገና በጅምሩ በስም እንጂ ቆጥረው ከማያውቁት ገንዘብ ጋር አስተዋወቃቸው፡፡ ዶክተር መስፍን እንደሚሉት፤ ወደ ንግዱ ሲገቡ የስቴሽነሪ እቃዎች ምን ምን እንደሆኑ በቅጡ አያውቁም ነበር፤ መርካቶ ግን ሁሉንም አስተማራቸው፡፡ ‹‹ማንም ከእናቱ ማሕጸን አላገኘውም›› በሚል በ15 ቀናት ቆይታ የስቴሽነሪ ዕቃዎችን በመለየት ወደ ጨረታ እንደገቡ ይገልጻሉ፡፡

የንግድ ስራው ግን እየቆየ ሲሄድ እንደ አጀማመሩ አልጋ በአልጋ ሊሆንላቸው አልቻለም፡፡ ከተማ ውስጥ ያለው ውድድር በእጅጉ ፈተናቸው፡፡ በዚህ ምክንያትም ለንግድ ስራው ምቹ ባሏቸው ክልሎችና ወረዳዎች ላይም ሰርተዋል፡፡

ዶክተር መስፍን የፒኤችዲ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ቅጥር የመመለስ ፍላጎት አልነበራቸውም፡፡ ምክንያቱም ሳያስቡት የገቡበት የንግድ ሥራ አስተምረው ከሚያገኙት የወር ደመወዝ በብዙ እጥፍ ያደገና ባጭር ጊዜ ውስጥ ሃብት ማፍራት ያስቻላቸው ሥራ ሆኗል፡፡ የንግድ ሥራቸውን ብቻ ይዘው ቢቀጥሉ ብዙ ርቀት ሊጓዙ እንደሚችሉ ቢያውቁም፣ ከንግድ ስራው የሚያገኙት ገንዘብ ሥራውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚገፋፋ ቢሆንም፣ እሳቸው ግን አልቀጠሉበትም፡፡

> **የንግድ ሥራቸውን ብቻ ይዘው ቢቀጥሉ ብዙ ርቀት ሊጓዙ እንደሚችሉ ቢያውቁም፣ ከንግድ ስራው የሚያገኙት ገንዘብ ሥራውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚገፋፋ ቢሆንም፣ እሳቸው ግን አልቀጠሉበትም**

የንግድ ሥራው የቱንም ያህል ቢጣፍጣቸው በማስተማር ሥራ ውስጥ የሚያገኙት እርካታ ትልቅ እንደሆነ ዶክተር መስፍን ይናገራሉ፡፡ ‹‹በነጻ ያስተማረችኝ አገሬ ናት፤ የአገሬ ውለታ አለብኝ›› በማለት ወደ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ተመልሰው የማስተማር ሥራቸውን ለመቀጠልና የንግድ ሥራውንም ጎን ለጎን ለማስኬድ ወሰኑ፡፡

ከፒኤችዲ ትምህርታቸው በኋላ የዲላ ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና ስነ-ባህሪ ተቋም ዲን መሆን የቻሉት ዶክተር መስፍን፤ በወቅቱ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሰላምን ከማስፈን ጀምሮ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የትምህርት ተደራሽነትን በተለይም የማስተርስ ትምህርትን ማስፋትና የፒኤችዲ መርሃ ግብር እንዲጀመር ብርቱ ጥረት አድርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ የመምህራን የትምህርት ታሪክ ውስጥ መምህራንን በማሰልጠን ተጠቃሽ ከሚባሉት መካከል ዲላ ዩኒቨርሲቲ አንዱ ነው የሚሉት ዶክተር መስፍን፤ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባላቸው የ18 ዓመታት ቆይታ ሙሉ አቅማቸውን አሟጠው መጠቀማቸውን ጠቅሰው፣ በዩኒቨርሲቲው ለመጡ ለውጦች አሻራቸው እንዳለበትም አጫውተውናል፡፡

‹‹ያስተማረኝ ሕዝብ ነው፡፡ ስለዚህ ያስተማረኝን ሕዝብ በሙያዬ ሳገለግለው ነው ሕሊናዬ የሚረካው›› በማለት የንግድ ሥራውን በአብዛኛው በባለቤታቸው በኩል እየሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በንግዱ ማሕበረሰብ ዘንድ በጣም ጭካኔና ርህራሄ የሌለው ድርጊት እንደሚታይም ጠቅሰው፣ ግብር ከሚከፍለው ይልቅ የማይከፍለው የሚበልጥበት ሁኔታ እንዳለም ነው የተናገሩት፡፡ አጠቃላይ የንግድ ስርዓቱ የተበላሸ እንደሆነም መታዘብ መቻላቸውን ይገልጻሉ፡፡

በአሁኑ ወቅትም አዲስ አበባ ላይ ባሏቸው ወኪሎች አማካኝነት የስቴሽነሪ እቃዎቹን ለገጠር ከተሞችና ወረዳዎች እንደሚቀርቡ ጠቅሰው፣ ወረዳዎች ላይ በመስራታቸው የንግዱ ስራ ውጤታማ መሆን መቻሉንና ወደ ገጠር መሸሻቸው እንዳዋጣቸው አመልክተዋል፡፡ ‹‹የጨረታ ሥራ የተወሰነ ወቅት የሚያጣድፍና እጅግ በጣም አድካሚ ነው›› የሚሉት ዶክተር መስፍን፤ አሁን የንግድ ሥራ ዘርፋቸውን የመቀየር ሀሳብ እንዳላቸውም ይገልጻሉ፡፡

በንግዱ ስራ በኩል ከተማ ውስጥ ውድድር ሳይሆን መጠላለፍ ነው ያለው የሚሉት ዶክተር መስፍን፣ እንዲያም ሆኖ ከተማ መኖር ብዙ ጥቅሞች አሉት ብለዋል፡፡ ሙሉ ቤተሰቦቻቸውን አዲስ አበባ ማስገባታቸውንም ገልጸዋል፡፡

ዶክተር መስፍን በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውም ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ ይታወቃሉ። በእነዚህም የምርምር ሥራዎቻቸው አማካይነትም ባለፈው መስከረም ወር የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግን ማግኘታቸውንም ገልጸዋል፡፡ ይህ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ ያገኙት ዕውቅና በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እጅጉን የተደሰቱበትና የኮሩበት የልፋታቸው ፍሬ እንደሆነ ነው የገለጹት፡፡ ከትምህርት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ከሰሯቸው 11 የጥናትና ምርምር ሥራዎች ስድስቱ ለዚህ ማዕረግ ያበቋቸው መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

‹‹የሰው ልጅ ለምን ወደቅኩ እንጂ፤ ወደቅኩ ማለት የለበትም›› የሚሉት ዶክተር መስፍን፤ ማንኛውም ሰው ከደከመና ከጣረ ካሰበበት ይደርሳል፤ ሁሉም ሰው የወደቀበትን ምክንያት ለይቶ ለመነሳት ጥረት ማድረግ አለበት ይላሉ፡፡ በተለይም ወጣቶች ጊዜ፣ ዕውቀትና ጉልበታቸውን በአግባቡ መጠቀም ከቻሉ ውጤታማ የሚሆኑባቸው በርካታ ዕድሎች እንዳሉ ነው ያመለከቱት፡፡ ወጣቶች በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ሁሉ በርትተው እንዲሰሩና ተማሪዎችም ትምህርታቸውን ዋና ሥራቸው አድርገው ጠንክረው እንዲማሩ መክረዋል፡፡

በንግድ ሥራቸው ብዙ ሃብትና ንብረት ማፍራት የቻሉት ዶክተር መስፍን፤ በስቴሽነሪ እቃዎች አቅራቢነት ሥራቸውም የመንግሥትን ግብር በአግባቡ እንደሚከፍሉ ይናገራሉ፡፡ ቫት ብቻ በዓመት ከሁለት መቶ ሺ ብር በላይ እንዲሁም ከ170 እስከ 200 ሺ ብር ግብር እንደሚከፍሉ ገልጸዋል፡፡ ማሕበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር ሰው እንዲማር እንዲያድግና እንዲነግድ እመክራለሁ፤ አስተምራለሁ የሚሉት ዶክተር መስፍን፤ በዚህም አንዱ መንገድ ቢዘጋ ሌላ መንገድ እንዳለ አሳያለሁ ይላሉ፡፡


በርካታ ተማሪዎችን በትምህርት እንደሚያግዙ የሚናገሩት ዶክተር መስፍን፣ የተማሩትንም በተግባር ማሳየት እንደሚችሉ በማመላከት የሚያውቁትንና የሰሙትን ማንኛውንም ጠቃሚና ሰው የሚያድግበትን እንዲሁም የሚለወጥበትን መንገድ እንደሚያሳዩ ይገልጻሉ፡፡

ዶክተር መስፍን በኢትዮጵያ ትምህርት ዙሪያ ያልተደፈሩና ያልተጀመሩ ሥራዎችን መሥራት ያስደስታቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ትምህርት ብዙ ማነቆዎች እንዳሉበትም ይጠቁማሉ፡፡ የጥራት፣ የፍትሃዊነትና የተደራሽነት ችግሮቹን ነቅሶ ለማውጣት የተለያዩ ጥረቶች እያደረጉ እንደሆነ ነው የሚናገሩት፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ትምህርት ሁለት ጥቅሞች አሉት፤ አንደኛው በግለሰብ ደረጃ ጥሩ ኑሮ መኖር ያስችላል፡፡ ሁለተኛው ማሕበረሰብን ማገዝ፣ መጥቀምና ለውጥ ማምጣት ነው፡፡ ጥናቶቹም ይህንኑ የሚመላከቱ ናቸው፡፡

በቀጣይ አራት ዓመት ጊዜ ውስጥም ለሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ የሚያበቃቸውን ተጨባጭ ለውጥ የማምጣት ዕቅድ እንዳላቸው የገለጹት ዶክተር መስፍን፤ ያን ጊዜ ትልቁን ስኬታቸውን እንደሚያዩ ነው የተናገሩት፡፡

የኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት አድጎና ተሻሽሎ ማየት ትልቅ ምኞታቸው እንደሆነም ጠቅሰው፣ በተለይም የትምህርት ጥራት፣ ተገቢነት፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነት ተስተካክሎ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንደ ሌሎች አገራት ተማሪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ እኩል መወዳደር የሚችሉበት ጊዜ እንዲመጣ ምኞታቸው መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ለዚህም በብርቱ መሥራት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

# ስፖርት



# ዛሬ በሚካሄደው ሀገር አቋራጭ ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የአሸናፊነት ግምት አግኝተዋል

ብርሃን ፈይሳ

የፈረንጆቹ የክረምት ወራት የሀገር አቋራጭ ውድድሮችን ለማካሄድ ምቹ እና ተመራጭ ወቅት ነው። ምክንያቱ ደግሞ ተፈጥሯዊ መሰናክሎችን፣ ውሃማ እና አስቸጋሪ ጭቃማ ስፍራዎችን ለሚፈልገው ሀገር አቋራጭ ዝናባማው ወቅት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም በርካታ የአውሮፓ፣ እንዲሁም ጥቂት የአሜሪካ እና የአፍሪካ ከተሞች ይህንን ውድድር ያስተናግዳሉ፡፡ እነዚህ የዙር ውድድሮች በዓለም አትሌቲክስ ዕውቅና ያላቸው ሲሆኑ ከወርቅ እስከ ነሐስ ያሉ ደረጃዎች አሏቸው፡፡ ከሳምንታት በፊት በስፔን ሁለት ከተሞች የተጀመረው የዘንድሮው የዓለም ሀገር አቋራጭ የዙር ውድድርም ዛሬ ሦስተኛውን ፉክክር በካርዲፍ (በእንግሊዟ ዌልስ) የሚያከናውን ይሆናል፡፡

ካለፈው የፈረንጆቹ ወር አጋማሽ አንስቶ እስከ አዲሱ ዓመት ሁለተኛው ወር አጋማሽ ድረስ 15 ውድድሮች የሚደረጉ ሲሆን፤ ማጠቃለያውም የዓለም አትሌቲክስ በየዓመቱ የሚያዘጋጀው የዓለም ሀገር አቋራጭ ሻምፒዮና ይሆናል፡፡ ይህንን ተከትሎ እንዲሁም የጎዳና ላይ ውድድሮች ወቅት እስኪመጣ ድረስም ከመላው ዓለም በርካታ አትሌቶች በሀገር አቋራጭ የዙር ውድድሮች ላይ ይካፈላሉ፡፡ ዛሬ በካርዲፍ በሚከናወነውና በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ በተሰጠው ውድድር ላይም ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እንዲሁም ተቀናቃኞቻቸው ተካፋይ ይሆናሉ፡፡ በሀገር አቋራጭ ሻምፒዮናዎች የተሻለ የውጤታማነት ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር ላይም አትሌቶቿ እንደተለመደው ጠንካራ ተፎካካሪና አሸናፊ ይሆናሉ በሚል ይጠበቃል፡፡

ውድድሩ በወንዶች 9ነጥብ6 ኪሎ ሜትር እንዲሁም በሴቶች ደግሞ 6ነጥብ4 ኪሎ ሜትር በመሸፈን ንፉሳማ በሆነ ስፍራ ይካሄዳል፡፡ በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድም በተለይ በሴቶች ምድብ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አሸናፊ ይሆናሉ የሚለው ግምት አይሏል፡፡ ግምቱን በቀዳሚነት ካገኙ አትሌቶች መካከልም በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው የውድድር ዓመት በተለያዩ የ10 ኪሎ ሜትር ውድድሮች ላይ ተሳታፊ የነበረችው አትሌት ልቅና አምባው አንዷ ናት፡፡ አትሌቷ በአንድ የመም፤ እንዲሁም፣ በሦስት የ10 እና 15 ኪሎ ሜትር ሩጫዎች ላይ ተሳትፋ መልካም የሚባል ውጤት አስመዝግባለች፡፡ ከሳምንታት በፊት በስፔን በተደረገው ሀገር አቋራጭ ቱር በመካፈል 29:36 በሆነ ሰዓት አሸናፊ ነበረች፡፡ ጠንካራዋ አትሌት ልቅና በሌላ ውድድር ወቅት የሆድ ሕመም ቢገጥማትም በቀላሉ እጅ ሳትሰጥ ከሕመሟ ጋር እየታገለች አራተኛ ደረጃን ይዛ ማጠናቀቋም አስደናቂ ብቃቷን ያስመሰከረ ሆኗል፡፡ ይህ የሁለተኛ ጊዜ የመድረኩ ተሳትፎዋ በመሆኑም ለጠንካራ ተፎካካሪነት እንድትጠበቅ አድርጓታል፡፡

ሌላዋ ወጣት አትሌት አስማረች አንለይም በዚህ ውድድር ከሚሳተፉ አትሌቶች አንዷ መሆኗ ታውቋል። በዚህ ዓመት የአፍሪካ ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ በ3ሺ ሜትር የወርቅ፤ እንዲሁም፣ በ5ሺ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ ማጥለቅ የቻለችው አትሌቷ ተስፋ ከተጣለባቸው ተተኪ አትሌቶች መካከል አንዷ ናት። አትሌቷ ካለችበት ወቅታዊ አቋም አንጻርም በካርዲፍ ከፍተኛ የአሸናፊነት ፉክክር ያደርጋሉ በሚል ከተገመቱት መካከል አንዷ ሆናለች፡፡ ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት መሠረት የሻነህም ተመሳሳይ ግምት ከተሰጣቸው አትሌቶች መካል ትገኛለች፡፡ የ18 ዓመቷ አትሌት ባለፈው ዓመት በካሊ በተደረገው የወጣቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለሀገሯ በ3ሺ ሜትር መሰናክል የነሐስ ሜዳሊያ ማስመዝገቧ የሚታወስ ነው፡፡

በወንዶች በኩልም ሌላኛው የ17 ዓመት ወጣት ኢትዮጵያዊ አትሌት ዮሐንስ አስማረ በዚህ ውድድር ተሳታፊ እንደሚሆን አትሌቲክስ ዊክሊ በዘገባው ጠቁሟል፡፡ ባለፈው ዓመት አሰላ ላይ በተደረገው ከ20 ዓመት በታች የአትሌቲክስ ሻምፒዮና በ1ሺህ 500 ሜትር አሸናፊ የነበረው አትሌቱ፤ በዚህ ዓመት ደግሞ ናይሮቢ ላይ በተደረገ ውድድር ተሳትፎ 6ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀው፡፡ ከሳምንታት በፊት በሰሜን አየርላንድ በተካሄደው የሃገር አቋራጭ ቱር ውድድር ላይም አሸናፊ በመሆን ማጠናቀቅ ችሏል፡፡ ወጣቱ አትሌት በውድድሩ አሸናፊ ከመሆን በዘለለ ልምድ ያገኘበት መድረክ እንደመሆኑ በዛሬው ውድድር ላይ ተፎካካሪዎቹን በመርታት አሸናፊ ለመሆን እንደሚችል ተጠብቋል። ነገር ግን፣ በሁለቱም ጾታዎች የኬንያ፣ ብሩንዲ እና እንግሊዝ አትሌቶች ለኢትዮጵያውያኑ ፈተና ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡



አትሌት ልቅና አምባው በካርዲፍ የሃገር አቋራጭ ቱር ለአሸናፊነት ትሮጣለች፤